

«ሠላምን በአገር ሳይ መልሶ ለማምጣት ብቸኛውና አስተማማኝ መንገድ ፖለቲካዊ ምክክር ነው»
- ሬሚ ማሪሾ
በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር

ገጽ 6

የማህጸን ኢንፌክሽን

ገጽ 8

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
81ኛ ዓመት ቁጥር 309 ሐምሌ 9 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# «ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከሰቱ ጥፋቶች ጀርባ ህወሓት ይጠፋል ብለን አናምንም»

- አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ
የትግራይ ዲሞክራሲ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- ሁሌም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከሰቱ ጥፋቶች ጀርባ ህወሓት ይጠፋል ብለን አናምንም ሲሉ የትግራይ ዲሞክራሲ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ተናገሩ። ትግራይን መልሶ ለመገንባት የተያዘውን በጀት ህወሓት ለራሱ እኩይ አላማ እንዳያውለው ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባም አሳስበዋል።

የትግራይ ዲሞክራሲ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው ህወሓት በለውጥ ተቃራኒ መጓዝ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ በርካታ ግጭቶችን ፈጥሯል፤ አገርን የማፍረስ ሙከራዎችንም አድርጓል።

ህወሓት በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ሆነው ሀሳቡን ከሚደግፉ ኃይሎች ጋር በመተባበርና በማስተባበር ግጭቶችን ሲመራና ሲያስተባብር ነበር ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ ሁሌም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከሰቱ ጥፋቶች ጀርባ ህወሓት ይጠፋል ብለን አናምንም ብለዋል።

ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናይ ህወሓት ከሸኔ ጋር በይፋ ለመስራት መግለጫ ሲያወጡ ነበር ያሉት ኃላፊው፤ ሰሞኑን ባሉ ግጭቶችም ህወሓት ከበስተጀርባ እንዳለበት መገመት ይቻላል ብለዋል።

እንደ አቶ ሙሉብርሃን ገለጻ፤ ቡድኑ ወደ መቀሌ ከገባ በኋላ በርካታ የሽብር ሥራዎችን ሲሰራ እንደነበር ማስታወስ ይቻላል። ሼኔን ጨምሮ ከበርካታ የሽብር ቡድኖች ጋር በጋራ ሲሰራ ነበር፤ መስራት ብቻ ሳይሆን መቀሌ ላይ ቢሮ ከፍቶላቸው ሲንቀሳቀሱ

«ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## የክልሉ የደን ሽፋን 26ነጥብ 6 ከመቶ ደርሷል

# በኦሮሚያ በአንድ ጀምበር አራት መቶ ሚሊዮን ችግኝ ሊተከል ነው

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በዘንድሮ ክረምት ለመትከል ከታቀደው አራት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ችግኝ ውስጥ 400 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀምበር ለመትከል መታቀዱን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ በተከታታይ ዓመታት በተሰሩት የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብሮች እና የበጋ አፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ክልሉ ከነበረው 15 በመቶ የደን ሽፋን ወደ 26 ነጥብ 6 በመቶ ያደገ መሆኑም ተገልጿል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ አበራ ወርቁ ከትናንት በስቲያ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳሉት፤ በአንድ ጀምበር ችግኝ የመትከል መርሐ ግብር በዚህ ዓመት በክልሉ 400 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ እየተሰራ ነው።

ሐምሌ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ህብረተሰቡንና የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ለመተግበር በታቀደው በዚህ መርሐ ግብርም በተለያዩ አካባቢዎች የችግኝ ጉድጓዶች የተዘጋጁ ሲሆን የአካባቢዎችን ስነ-ምህዳር ባማከለ መልኩ የሚሰራ ተግባር መሆኑን አስታውቀዋል።

አቶ አበራ እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል በአረንጓዴ ልማት አሻራ መርሐ ግብር ችግኝ ለመትከል ከታቀደው ውስጥ እስካሁን 50 በመቶ መትከል ተችሏል። በክልሉ

በኦሮሚያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በሻሸመኔ ከተማ የአቅመ ደካሞችን ቤት እድሳት አስጀመረ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ከተጠሪ ተቋማት ጋር በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በሻሸመኔ ከተማ የአቅመ ደካሞችን ቤት እድሳት አስጀመረ።

ከሁለት ዓመት በፊት በጠላት ኃይሎች ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባት የነበረችው የሻሸመኔ ከተማ አሁን ላይ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ወደነበረችበት ተመልሳለች ሲሉ የሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ገለጹ።

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የሀገራዊ ፕሮጀክቶች ክትትል ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወርቁ ጓንጉል በመርሐ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ ሕዝብና መንግሥት ከተባበሩ የማይፈቱት ችግር የለም።

የጠቅላይ ሚኒስትር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ገጽ 9

“ጭጋግና ጠል”

# ተማሪ ቢኒያምና የጥቁር አንበሳ ጉዳይ

**ዳግማዊት ግርማ**

ሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያው አማካኝነት አጀንዳ ሆኖ ብዙኃኑን ሲያነጋግር ከከረሙ ርዕሰ ጉዳዮች አንዱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪው ቢኒያም ኢሳያስ ጉዳይ ነው።

አካል ጉዳተኞችን መደገፍና ማበረታታት እንጂ ሕልማቸው ማቀጨጭ አይገባም በሚል I stand with Biniyam!! የሚል የማህበራዊ ሚዲያ ንቅናቄ በማድረግ የተማሪ ቢኒያምን ጉዳይ ሰዎች እዚያና እዚህኛው ጫፍ ላይ ሆነው ሲከራከሩበት ከርመዋል።

የህግ ባለሙያዎችና የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ይመለከተናል ያሉ ሰዎች በሙሉ ጉዳዩን አንስተው ብዙ ብለውለታል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጁም ጋዜጠኞችን ጠርቶ በተማሪ ቢኒያም ጉዳይ ኃላፊነቱን እንደሚወስድ መግለጹም የሚታወስ ነው።



ለመሆኑ ተማሪ ቢኒያም ማን ነው ?፤ ወጣት ቢኒያም ኢሳያስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የ5ኛ ዓመት የሕክምና ትምህርት ክፍል ተማሪ ነው። ከልጅነቱም ጀምሮ ሐኪም የመሆን ሕልም የነበረውና በትምህርቱ ጎበዝና መልካም ስብዕና ያለው መሆኑን በቅርብ የሚያውቁት ጓደኞቹና መምህራኑ ይመሰክራሉ።

ተማሪ ቢኒያም በተፈጥሮ ምክንያት አካል ጉዳተኛ ቢሆንም፤ ብዙዎች በሙሉ አካል የሚከብዳቸውን የሕክምና ትምህርትም እስከ 5ኛ ዓመት በትጋት ከመማሩም ባሻገር በትምህርት ውጤቱም ሶስት ነጥብ ስምንት በማምጣት ጉብዝናውን ማስመስከር የቻለ ተማሪ ነው።

ነገር ግን ሊመረቅ ሁለት ዓመት የማይሞላ ጊዜ ሲቀረኝ በአካል ጉዳተኝነቴ ምክንያት ሐኪም መሆን አትችልም ተብዬ ትምህርቴን እንዳቋርጥና ሌላ ትምህርት እንድትጀምር የሚል አስደንጋጭ ውሳኔ ተላልፎብኛል የሚለው ወጣት ቢኒያም፤ ይህ በደል በእኔ ላይ መተላለፉ አግባብ አይደለም ሲል ዩኒቨርሲቲውን በአደባባይ ሞግቷል።

በዚህ ወቅት ነበር አካል ጉዳተኛነቱ ሳይበግረው ተምሮ ጥሩ ውጤት ሲያመጣ የከረመን ልጅ በዚህ መልኩ ከትምህርቱ ማራቅ ተገቢ አይደለም የሚሉ ድምፆች ከተለያዩ አቅጣጫዎች መሰማት የጀመሩት።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም የተማሪ ቢኒያምን ጉዳይ ምን ትላላችሁ ሲል ዩኒቨርሲቲውን ጠይቆ ነበር፤ ዩኒቨርሲቲው አመራሮችም በበኩላቸው ተማሪ ቢኒያም ጉዳይ ሕግና አሰራር እስከሚፈቅድ ድረስ መጓዙንና ላለፉት ስምንት ወራት ሲመለከቱ መቆየታቸውን ይገልጻሉ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አንዱአለም ደነቀ የትምህርት ተቋሙን በመወከል በሰጡት ምላሽ መሰረትም ተማሪ ቢኒያም የአራተኛ ዓመት ተማሪ እያለ የግራ እጁ ላይ በተፈጥሮ የአካል ጉዳት ያለበት መሆኑ በመምህራን መለየቱን ያስታውሳሉ። ከዚህ በኋላ ይህ ጉዳት በህክምና ትምህርቱ ላይ ያለው ተፅዕኖ እንዲለይ በሚል ጉዳዩ ወደ ዲን ጽህፈት ቤት ተመርቶት ነበር ይላሉ።

ቢያንስ አንድ የህክምና ትምህርት ተማሪ መለስተኛ ቁስል መስፋት፣ የቆመ የልብ ምት ማስነሳት፣ ኦክሲጅን መስጠት፣ ቱቦ በሰውነት ውስጥ ማስገባት እንዲሁም ወሊድ የመሳሰሉትን ሕክምናዎች መስጠት ግዴታ መሆኑንም ዶክተር አንዱ‍ለም ይናገራሉ።

እንደ ዶክተር አንዱለም ገለጻ፤ ኮሌጁ ባዋቀረው ኮሚቴ በቀረበለት ምክረ ሀሳብ መሰረት ተማሪ ቢኒያም ከጤና ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ትምህርቶችን እንዲማር ወስኗል። በህክምና ፋርማሲ፣ በህክምና ላብራቶሪ ሳይንስ እንዲሁም በህክምና ላቦራቶሪ በመረጠው ዘርፍ እንዲማርና ተጨማሪ ትምህርት ሳይማር ባችለር ኦፍ ባዮሜዲካል ሳይንስ እንዲሰጠው የሚል ውሳኔ እንደተላለፈም ያስታውሳሉ።

ተማሪው የአካል ጉዳት እያለበት ለህክምና ትምህርት ዘርፍ በመመደቡና ለደረሰው ችግር ዋነኛ ምክንያት የህክምና ኮሌጁ ተማሪዎችን ራሱ መመልመል ያለመቻሉ ነው ያሉት ዶክተር አንዱለም፤ የህክምና ኮሌጁ በተማሪ ቢኒያም ላይ ለተከሰተው ችግር ኃላፊነት እንደሚወስድ ገልጸው ነበር።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በቀጣይ የሚገቡ ተማሪዎች በቅበላ ጊዜ ሙሉ ምርመራ እያደረገ ለማስገባት እንደሚሰራም ነው የሚጠቁሙት።

የሆነ ሆኖ ተማሪ ቢኒያም ዩኒቨርሲቲው ባችለር ኦፍ ባዮሜዲካል ሳይንስ ዲግሪው ይሰጠው በሚል ባስተላለፈው ውሳኔ እንደማይስማማ በመግለጽ፤ የሕክምና ዶክትሬት ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ እንደሚፈልግ በግልጽ ነበር የተናገረው።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትላንትናው ዕለት በድጋሚ ባወጣው መግለጫ ደግሞ የተማሪ ቢኒያምን ዳግም ቅሬታ በመቀበል ውሳኔውንም መቀየሩንም ይፋ አድርጓል።

የተማሪ ቢኒያም ኢሳያስን ትምህርት በተመለከተ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና የሕክምና ትምህርት ቤት ለተማሪው የትምህርት ሂደት ይረዳሉ ያሏቸውን አማራጮች ማቅረባቸው ይታወሳል። ሆኖም ተማሪ ቢኒያም ብቸኛ ፍላጎቱ የሕክምና ትምህርትን መማር እንደሆነ በመግለጹ የሕክምና ትምህርቱን እንዲቀጥል መወሰኑን ነው ያሳወቀው።

ከዚህ ባለፈም እስካሁን የተቋረጡ ትምህርቶችንም በማካካስ ትምህርቱን ካቆመበት እንዲቀጥል ሲል ዩኒቨርሲቲው ምላሹን ሰጥቷል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የህግ ባለሙያው አቶ ገመቺስ መኮንንን ስለ ተማሪ ቢኒያም ኢሳያስ ምን ይላሉ ሲል አነጋግሯል።

የህግ ባለሙያው እንደሚሉት ፤ ይህ አይነቱ ችግር መጀመሪያም እንዳይፈጠር ጥንቃቄ መደረግ ነበረበት። አምስት ዓመታት ተገቢውን ክትትል ባለማድረግ ወይም በቸልተኝነት ተማሪው የህክምና ትምህርቱን እንዲከታተል ተደርጎ በመሃል አቋርጥ መባሉ ከመነሻው ሂደቱ ችግር እንዳለበት ነው የሚያሳየው።

ይህን አይነት መሰል ችግሮች ቀድሞውኑ የመከታተል ኃላፊነት ያለበት የመንግሥት አካል አለ፤ በተለይ በትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት

ተማሪው ላይ ያለውን ጉዳት በተመለከተ ቀድሞውኑ ክትትል ሳያደርጉ ለደረሰው መጉላላት ተጠያቂ መሆን አለባቸው፤ ለደረሰው ችግር እነዚሁ አካላት ኃላፊነት አለባቸው ይላሉ።

ከህግ አንጻር መመልከት ቢቻል ሕገ መንግስቱን እንዲሁም የፍትሐ ብሔር ሕጉ በመንግሥት የተጣለበትን ኃላፊነት ያልተወጣ አካል ተጠያቂ ማድረግ እንደሚቻል፣ ጉዳት የደረሰበት አካል ጉዳዩን የዳኝነት ስልጣን ላለው አካል የማቅረብ እና ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋሉ።

# በመጪው የትምህርት ዘመን ከመመሪያው ውጭ ወርሃዊ የትምህርት ቤት ክፍያ ጭማሪ ማድረግ በሕግ ያስጠይቃል

አዲስ አበባ፡- ትምህርት ቤቶች በ2015 የትምህርት ዘመን ከመመሪያው ውጭ ወርሃዊ የክፍያ ጭማሪ ማድረግና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያ እንዳይጠይቁ የአዲስ አበባ የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን አሳሰበ።

የባለሥልጣኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ፍቅርተ አበራ ለኢዜአ እንዳሉት፤ ከመመሪያው ውጭ የክፍያ ጭማሪ በሚያደርጉ የግል ትምህርት ቤቶች ላይ እርምጃ ይወሰዳል።መመሪያው በ2014 ዓ.ም ጭማሪ ያደረጉ የግል ትምህርት ቤቶች በ2015 የትምህርት ዘመን ምንም አይነት ጭማሪ እንዳያደርጉ ያዛል።

ነገር ግን መመሪያውን በመጣስ አንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች አስቀድመው በደብዳቤና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ጭማሪ እንደሚያደርጉ ለወላጆች መልዕክት እያስተላለፉ መሆኑ እንደተደረሰበት ገልጸው፤መመሪያውን በሚጥሱ ትምህርት ቤቶች ላይ ፈቃድ የመሰረዝና በሕግ የማስጠየቅ እርምጃዎች እንደሚወሰድ ከወዲሁ አሳስበዋል።

በከተማው ነሺህ 590 የግል ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን በ2014 የትምህርት ዘመን ነሺህ 77 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ወርሃዊ የክፍያ ጭማሪ ማድረጋቸውን አስታውሰዋል።

ቀሪዎቹ ትምህርት ቤቶች በሚያቀርቡት ፕሮፖዛል እና ከወላጅ ጋር በሚያደርጉት መግባባት ጭማሪ ማድረግ እንደሚችሉም መመሪያው ያዛል ።

ነገር ግን መመሪያው ጭማሪ ማድረግ በማይፈቅድላቸው ትምህርት ቤቶች ጭማሪ በመጠየቅና ሌሎቹ ደግሞ የተጋነነ ክፍያ አስቀድመው ለወላጆች በማሳወቅ ላይ መሆኑ ተደርሶበታል ብለዋል።

ማንኛውም ትምህርት ቤት ከመደበኛ የአገልግሎት ክፍያ ውጭ በአይነትም ሆነ በገንዘብ ክፍያ መጠየቅ እንደማይችሉ ምክትል ሥራ አስኪያጇ ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት በመዲናዋ ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶችን ሳይጨምር በወር እስከ 15 ሺህ ብር ክፍያ የሚጠይቁ ትምህርት ቤቶች እንዳሉም ጠቁመዋል።

ይህ የተጋነነ የትምህርት ቤት ክፍያ የሕብረተሰቡን የመክፈል አቅም እየተፈታተነ በመሆኑ መንግሥት የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ባለፈው ዓመት ወላጆች ባልተስማሙበትና ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ የተጋነነ ጭማሪ ያደረጉ ትምህርት ቤቶች ላይ ጭማሪውን ለወላጆች ከመመለስ ባሻገር እርምጃ የተወሰደባቸውም እንዳሉ አብራርተዋል።

ወላጆች እነዚህን ትምህርት ቤቶች በማጋለጥና የመማር ማስተማር ሥርዓቱ በአግባቡ እንዲመራ የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሕብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ ጫና ከግምት ውስጥ በማስገባት አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ላለፉት ሦስት አራት ዓመታት ምንም ዓይነት ጭማሪ ባለማድረጋቸው ምክትል ሥራ አስኪያጇ ምስጋና አቅርበዋል።



**ፍቅርተ አበራ**

በአዲስ አበባ የግል ትምህርት ቤቶች 400 ሺህ የሚጠጉ ተማሪዎችን የሚያስተናግዱ ሲሆን በከተማው የተማሪ ሽፋን 43 በመቶውን የሚይዝ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ዜና

# “ ለአዲስ አበባ ኢንተርፕራይዞች የስምንት ቢሊዮን ብር የገበያ ትስስር ተፈጥሯል”

**- ከንቲባ አዳነች አቤቤ**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ በበጀት ዓመቱ ለ19 ሺህ 207 ኢንተርፕራይዞች የስምንት ቢሊዮን ብር የገበያ ትስስር መፈጠሩን የከተማዋ ከንቲባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ። በከተማዋ በበጀት ዓመቱ ለ405 ሺህ 536 ዜጎች የሥራ እድል መፈጠሩን ተመልክቷል።

በሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር መፍጠርን በተመለከተ ለ21 ሺህ 62 ኢንተርፕራይዞች 6 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ፣ ለ19 ሺህ 207 ኢንተርፕራይዞች የ8 ቢሊዮን ብር የገበያ ትስስር ተፈጥሯልም ነው ያሉት።

የአካል ጉዳተኛ አ\sንቀሳቃሾችን በገበያ ትስስር ተጠቃሚ ለማድረግ ለ320 አንቀሳቃሾች የገበያ ትስስር ለመፍጠር የታቀደ ሲሆን፣ ለ378 የ10 ሚሊዮን ብር የገበያ ትስስር መፍጠር መቻሉን ከንቲባ አዳነች ጠቁመዋል።

ከ9 ሺህ 947 ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 8 ሺህ 323 ኢንተርፕራይዞች ወደሚቀጥለው ደረጃ እንዲሸጋገሩ መደረጉን ተገልጧል።

ከንቲባዋ የሥራ እድል ፈጠራን አስመልክቶ ባደረጉት ንግግር ፣ በበጀት ዓመቱ ለ350 ሺህ ዜጎች አዳዲስ አማራጭ የሥራ ዕድል መስኮችን ለመለየት ታቅዶ፣ ከ391 ሺህ በላይ (112 በመቶ) የሥራ እድል መፍጠር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የሥራ መስኮች መለየታቸውን ገልጸዋል።

ለ350 ሺህ ሥራ ፈላጊዎች የሥራ እድል ለመፍጠር በተደረገው ርብርብ 405 ሺህ 536 ዜጎች ሥራ ማግኘታቸውን ነው የተናገሩት።

ከነዚህ ውስጥ 380 ሺህ 720 ቋሚ የሥራ እድል ሲሆን ፣ 24 ሺህ 811 ጊዜያዊ የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ናቸው ብለዋል።

በተጨማሪም ለ597 አካል ጉዳተኞችና ለ820 ከስደት ተመላሾች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል ያሉት ከንቲባዋ ፣ የሥራ እድል ከተፈጠረላቸው መካከል 54 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ ፤ 76 በመቶ ወጣቶች፣ 16 በመቶ ከዩኒቨርሲቲና ቴክኒክና ሙያ የተመረቁ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን 568 ለማድረስ ታቅዶ፣ 831 ማድረስ መቻሉንም ነው ያስረዱት።

ከንቲባዋ አክለውም ፣ በሁለተኛው ዙር በምግብ ዋስትናና በልማታዊ ሴፍቲኔት መርሐ ግብር በመዲናዋ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት 109 ሺህ 918 ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን ከከንቲባ ጽህፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በአንድ በኩል በከተማዋ ነዋሪዎች ላይ የኑሮ ውድነት ያስከተለውን ጫና ለመቅረፍ፣ በሌላ በኩል የሥራ አጥነትን ችግር ለመቀነስ የሚያስችል ሥራ ከመሰራት በተጨማሪ የሥራ ባህልን ለማጐልበት ጉልህ አስተዋፅኦ ያለው ተግባር ተከናውኗል ብለዋል ከንቲባ አዳነች።



# የመጀመሪያው የዲጂታል ሎተሪ ገበያ ላይ ዋለ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በቴሌብርና በአጭር የጽሁፍ መልዕክት አማካኝነት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሕጋዊ የዲጂታል ሎተሪ ገበያ ላይ መዋሉን ኢትዮ ቴሌኮምና የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር አስታወቁ።

ኢትዮ ቴሌኮምና የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የሎተሪ ትኬት በዲጂታል አማራጭ ለማቅረብ የሚያስችል ስምምነት ትናንትና አድርገዋል።

በወቅቱ ስምምነቱን የፈረሙት የኢትዮ ቴሌኮም ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ እንዳስታወቁት፤ ከብሔራዊ ሎተሪ ጋር በተደረገ ስምምነት በቴሌብርና በአጭር የጽሁፍ መልዕክት አማካኝነት ሎተሪ መቁረጥ የሚያስችል ዲጂታል ሥራ ተጀምሯል።

ዲጂታል ሎተሪው “አድማስ” የተሰኘ መሆኑን ጠቁመው፤ ደንበኞች በቴሌ ብር አማካኝነት ሎተሪውን ለመቁረጥ ሲፈልጉ *127# በመደወል ከሚመጡ ዝርዝሮች መካከል 7 ቁጥርን በመምረጥ የብሔራዊ ሎተሪን አገልግሎት ማግኘትና የሎተሪ ክፍያ መፈጸም እንደሚችሉ ገልጸዋል።

በተጨማሪ በ605 አጭር የጽሑፍ መልዕክት ላይ A አሊያም የሚፈልጉትን ፊደል በመላክ ከተመዘገቡ በኋላ የሎተሪ ዕጣ ቁጥር ማግኘት ይቻላል ያሉት ወይዘሪት ፍሬ ሕይወት፤ ዲጂታል ሎተሪው ዘመናዊ እንዲሁም ወጪና ጊዜ ቆጣቢ በመሆኑ እንደአገር አዋጭ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም አሰራሩን በማዘመን ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመጣመር በርካታ አገልግሎቶችን በቴሌብር አማካኝነት እያቀረበ ይገኛል። ቀደም ብሎ ግብር ክፍያና የትራፊክ ህግ መተላለፍ ቅጣትን በቴሌብር አማካኝነት መክፈል የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ተደርጓል። አሁን ደግሞ ሎተሪን በቀላል መንገድ ማግኘት የሚቻልበት አሰራር በእያንዳንድ የእጅ ስልክ ላይ በመቅረቡ ለአገልግሎቱን ፈላጊ ህብረተሰብ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ብለዋል።

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ገረመው ጋርጂ በበኩላቸው፤ ዲጂታል ሎተሪ አገልግሎቱን ለማስጀመር ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ለረጅም ዓመታት ውይይት ሲደረግ መቆየቱን አስታውሰዋል።

አሁን ላይ ያሉት የቴሌ አመራሮች ለዲጂታል ኢኮኖሚ ያላቸው መልካም አስተሳሰብና ጥረት ለአገልግሎቱ ዕውን መሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ምስጋና



ይገባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር ተግባራዊ በሆነው የዲጂታል ሎተሪ አገልግሎት በርካታ ደንበኞች እንደሚገኙ ይጠበቃል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ዲጂታል ሎተሪ አገልግሎቱን በአጭር ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ዘንድ እንዲዳረስ ጥረት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር 14 ዓይነት የሎተሪ ዕጣዎች እንዳሉት የገለጹት አቶ ገረመው፤ አድማስ የተሰኘው ዲጂታል ሎተሪ 15ኛ የሎተሪ አይነት ሆኖ መቅረቡን አስታውቀዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ዲጂታል ሎተሪው ተግባራዊ ቢደረግም በሎተሪ አዟሪዎች አማካኝነት ደንበኞች ጋር የሚደርሱ የወረቀት ሎተሪዎች እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ገበያ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

በመሆኑም በቀጣይ ዓመታት የህትመት ወጪን ለመቀነስ የዲጂታል ሎተሪዎች የወረቀት ሎተሪዎችን እንዲተኩ መደረጉ ስለማይቀር ሎተሪ አዟሪዎች ከወዲሁ ሌሎች የሥራ አማራጮችን ማሰብ ይኖርባቸዋል ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በ1954 ዓ.ም በ50 ሺህ ብር መደበኛ ዕጣ ሥራውን የጀመረው የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ከአጠቃላይ ገቢው 10 በመቶ ለሎተሪ ህትመት ወጪ እንደሚያውል አስታውቋል።

ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር የሚቀርበው የዲጂታል ሎተሪ ዕጣ የህትመትና የአገልግሎት ወጪ ስለሌለው ተመሳሳይ ዲጂታል ሎተሪዎችን እያስፋፋ እንደሚሄድ ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደሩ ጠቁሟል።

# ስትራቴጂው በትራፊክ አደጋ የሚደርሰውን ሞት በግማሽ የመቀነስ ግብ እንዳለው ተገለጸ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የብሄራዊ የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂ በትራፊክ አደጋ የሚደርሰውን ሞት በግማሽ የመቀነስ ግብ እንዳለው የኢፌዴሪ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ገለጸ።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከብሉምበርግ ኢኒሼዬቲቭ ፎር ግሎባል ሮድ ሴፍቲ ጋር በመተባበር እ.ኤ.አ. ከ2021 እስከ 2030 ተግባራዊ እንዲሆን ያዘጋጀውን የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂ በትላንትናው እለት ይፋ አድርጓል።

ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ እንደገለጹት፤ የብሄራዊ የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂ በትራፊክ አደጋ የሚደርሰውን ሞት በግማሽ የመቀነስ ግብ አለው።

የአገራት ልምድ እንደሚያሳየው የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂን ተግባራዊ በማድረግ በትራፊክ አደጋ የሚደርሰውን ሞት እና የከባድ አካል ጉዳት ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ ችለዋል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ኢትዮጵያም ውጤታማ የብሄራዊ የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂን ተግባራዊ በማድረግ በትራፊክ አደጋ የሚደርሰውን ሞት በግማሽ የመቀነስ ግብ ተይዟል ብለዋል።

የትራፊክ ግጭት ዋነኛ የዓለም አቀፍ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የጤና ችግር እንደሆነም ቀጥሏል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር፣ ጠጥቶ ማሽከርከር፣ ሄልሜት (የደህንነት ቆብ) አለማድረግ እና የደህንነት ቀበቶ ወይም የህጻናት ግጭት መከላከያ ማቀፊያ አለመጠቀም ቁልፍ የመንገድ ትራፊክ መንስኤዎች እንደሆኑ ጥናቶች እንደሚያመለክቱም ገልጸዋል።

ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግ እና አንግቦ የተነሳውን ግብ ለማሳካት የመንገድ ደህንነት ተቋማዊ ብቃት እና የአስተዳደር ዘዴ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ ፍጥነት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ መሰረተ ልማት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ተሽከርካሪ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ ተጠቃሚ፤ ድህረ አደጋ የህክምና አገልግሎት መስጠት የተሰኙ ስድስት የመንገድ ደህንነት ምሰሶዎች እንዳሉት ጠቅሰዋል።

“የስትራቴጂው ዋና ዋና ምሰሶዎች ከዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ እስታንዳርዶች እና ከገባናቸው ስምምነቶች እንዲሁም ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ



ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ

ጋር እንዲናበቡ ተደርገው ውጤት በሚያመጡ መልኩ የተቀረፁ ናቸው። ” ያሉት ሚኒስትሯ ስትራቴጂው ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ ደህንነት ስርዓት መዘረጋትን እና ለመንገድ ትራፊክ ጉዳት ተጋላጭ የሆኑ መንገድ ተጠቃሚዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው ብለዋል።

የትራፊክ አደጋን ለመከላከል ለተወሰኑ ተቋማት ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉንም ባለድርሻ አካላት እና አጋር ድርጅት ቅንጅታዊ ሥራ የሚጠይቅ ነው ያሉት ሚኒስትሯ ፤ ስትራቴጂውን ተግባራዊ በማድረጉ ሂደትም የህብረተሰቡ ተሳትፎም ወሳኝ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የመንገድ ደህንነት ልዩ መልእክተኛው ሚስተር ዣን ቴድ በበኩላቸው፤ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የመንገድ ደህንነትን ለማስጠበቅ የሰራቸውን ተግባራት በማድነቅ በቀጣይም ለሚከወኑት ሥራዎች ከኢትዮጵያ ጎን እንደሚቆሙም ቃል ገብተዋል።

ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የተገኘ የትፊክ አደጋ መረጃ እንደሚያሳየው በአገር ደረጃ በመንገድ ትራፊክ ግጭት ሳቢያ በየቀኑ በአማካይ ከ11 የማያንሱ ሰዎች ሕይወት የሚቀጠፍ ሲሆን በ2013 በጀት ዓመት አራት ሺህ 161 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸውን ማጣታቸው ይታወቃል።

# ደንቡ ከፌዴራል መንግሥቱ የሚሰጡ ድጎማዎች ለምዝበራና ብልሹ አሰራሮች እንዳይዳረጉ እንደሚረዳ ተገለጸ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**



አዲስ አበባ፡- በፌዴሬሽን ምክር ቤት የፀደቀው ደንብ ከፌዴራል መንግስቱ የሚሰጡ ድጎማዎች ለምዝበራና ብልሹ አሰራሮች እንዳይዳረጉ እንደሚረዳ ተገለጸ። መሠረተ ልማት ስርጭቶች ፍትሐዊነትና ግልፀኝነት እንዲኖራቸው ጉልህ ሚና እንዳለው ተመልክቷል።

ውስን ዓላማ ያላቸው የድጎማ በጀትና የፌዴራል መሠረተ ልማት ስርጭት ፍትሐዊነት የክትትል ሥርዓትን ለማስፈጸም የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ትናንት አፅድቋል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስድስተኛ የፓርላማ ዘመን 1ኛ ዓመት የሥራ ጊዜ 2ኛ መደበኛ ስብሰባውን ባደረገበት ወቅት ውስን ዓላማ ያላቸው የድጎማ በጀትና የፌዴራል መሠረተ ልማት ስርጭት ፍትሐዊነት የክትትል ሥርዓትን ለማስፈጸም የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ላይ ሰፋ ያለ ውይይት አድርጓል።

ከዚህ በፊት በተለያዩ ምክንያቶች ከፌዴራል መንግሥቱ የሚሰጡ ልዩ አላማ ያላቸው ድጎማዎች ለምዝበራና ብልሹ አሰራሮች የተጋለጡ በመሆናቸው ግልፅ የሆነ አሰራር ሊበጅላቸው የሚገባ መሆኑን የምክር ቤቱ አባላት ተናግረዋል።

ደንቡም ከፌዴራል መንግሥት የሚሰጠው ልዩ ዓላማ ያላቸው ድጎማዎች የፌዴራል መሠረተ ልማቶች በፍትሐዊነት እንዲከፋፈል እንዲሁም ግልጽና ፍትሐዊ አሰራር እንዲሰፍን የሚያደርግ መሆኑን የምክር ቤቱ አባላት አመልክተዋል።

በሙሉ ድምፅ የፀደቀው ደንብ በክልሎች መካከል የሚስተዋለውን ኢፍትሐዊነት የመልማት ጥያቄ በዘለቄታነት የሚፈታ ደንብ መሆኑና የተመጣጠነ ልማትና መንግሥታዊ አገልግሎት እንዲኖር ያደርጋልም ተብሏል።

በሌላ በኩል ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለሕገ መንግሥት ትርጉም የቀረቡ የውሳኔ ሃሳቦች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አስተላልፏል።

የምክር ቤቱ የህገ መንግሥት ትርጉም ክትትልና ውሳኔ አፈፃፀም ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ዶክተር ሰማ ጥሩነህ እንደገለጹት፤ ዜጎች በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ህገ መንግሥቱን መሰረት ተደርገው የተሰጡ ውሳኔዎች አይደሉም። የፌዴሬሽን ምክር ቤት የህገ መንግሥት ትርጉም ሊሰጠው ይገባል በሚል 87 የሚደርሱ ጉዳዮች ለቋሚ ኮሚቴው መቅረቡን አንስተው፣ ጉዳዮቹ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች በቂ ክርክር ተደርጎባቸው ዜጎች በዚህ ውሳኔ ባለመርካት የተለያዩ አንቀፆችን በመጥቀስ ህገ መንግሥታዊ አይደሉም ብለው ያቀረቧቸው መሆናቸውን አንስተዋል።

በዚህም መሰረት በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አማካኝነት የታዩና ለህገ መንግሥት ትርጉም ክትትልና ውሳኔ አፈፃፀም ቋሚ ኮሚቴ የቀረቡ ሰባት ርዕሰ ጉዳዮች ለምክር ቤቱ በዝርዝር ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

ለምክር ቤቱ ከቀረቡ ሰባት ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥም ስድስቱ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንደማያስፈልጋቸው እና አንድ ጉዳይ ደግሞ የሕገ-መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል የሚለውን የቋሚ ኮሚቴን የውሳኔ ሀሳብ ምክር ቤቱ በአብላጫ ድምፅ አፅድቋል።

# በኦሮሚያ በአንድ ጀምበር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በዘንድሮው የአረንጓዴ ልማት መርሐ ግብር ለመትከል ከታቀደው አራት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ችግኝ ውስጥ እስካሁን ድረስ ከሁለት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን በላይ ችግኝ ተተክሏል።

በ2013 ዓ.ም በክልሉ ከአራት ቢሊዮን በላይ ችግኝ የተተከለ መሆኑን አስታውሰው፣ ከተተከሉት ችግኞች 84 ነጥብ 7 በመቶ የሚሆኑት መጽደቅ መቻላቸውን ተናግረዋል።ለዚህ ውጤትም የአካባቢው ማህበረሰብ፣ ተቋማት እንዲሁም ችግኞችን እንዲንከባከቡ የተመደቡ አካላት ለችግኞቹ ተገቢውን እንክብካቤ በማድረጋቸው መሆኑን ጠቅሰዋል።

በዓለማችን ብሎም በሀገራችን እየታየ ባለው የአየር ንብረት ለውጥ በዝናብ ስርጭትና በአካባቢ ስነ ምህዳር ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ በመምጣቱ ይህን ዓለም አቀፋዊ የአየር ንብረት ጫና መቆጣጠር ተገቢ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑን በመግለጫቸው አመልክተዋል።

ባለፉት ሶስት ዓመታት በክልሉ ከዘጠኝ ቢሊዮን በላይ ችግኝ የተተከለ መሆኑን አመልክተው፤ በተከታታይ ዓመታት በተሰሩት የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብሮች እና የበጋ አፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ክልሉ ከነበረው 15 በመቶ የደን ሽፋን ወደ 26 ነጥብ 6 በመቶ ያደገ መሆኑንም ገልጸዋል።

በክልሉ ለተከታታይ ዓመታት የአረንጓዴ ልማት ሥራ መሰራቱም የተጎዳ መሬት እያገገመ፣በደን እየተሸፈነና የውሃ ሀብት ሽፋን እየጨመረ መምጣቱን ገልጸው፤በእስካሁኑ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብሮች ከ58 ሺህ በላይ ወጣቶች የሥራ እድል የተፈጠረላቸው መሆኑን ተናግረዋል።

በበጋው ወቅት ከ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ የማህበረሰብ ክፍል በተሳተፈበት የመሬትና ውሃ ሀብት ጥበቃ ሥራም በተያዘው ክረምት ደግሞ ለማህበረሰቡ ኢኮ-ቱሪዝም በሚውል መልኩ፣ ለደን፣ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንዲሁም ለጥምር እርሻና ደን አገልግሎት በሚውል መልኩ ችግኝ የመትከል ሥራ እንደሚሰራም አብራርተዋል።

# ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከሰቱ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ነበር። በቅርቡም አላማውን የሚደግፉ በርካታ የሽብር ቡድኖችን እንዳሰለጠነ መረጃዎች አለን፤ የሚመስሉትን በማስተባበር አገር ለማተራመስ እየሰራ ነው።

ሰላምና ድርድር ከህወሓት ተፈጥሯዊ ባህሪ ጋር የማይሄዱና ለጊዜ መግዣነት የሚጠቀማቸው ስልቶቹ ናቸው ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ ችግሮችን በድርድር የመፍታት ባህሪ ህወሓት የለውም፤ ችግሮችን በድርድር መፍታት የሚችል ቢሆን ኖሮ ጦርነት የሚያስገባው ጉዳይ ሳይኖር ጦርነት አይጀምርም ነበር ብለዋል።

አቶ ሙሉብርሃን እንደተናገሩት ህወሓት ፍላጎቱ አንድ ነው፤ እሱም በጉልበት ስልጣን መያዝ ነው። በጉልበት ኢትዮጵያን የማይመራ ከሆነ ደግሞ ማፍረስ ተቀዳሚ አላማው በመሆኑ በየቦታው ግጭቶችን እየፈጠረ ይገኛል።

“አገር የሚገነባው በኢኮኖሚ ብቻ አይደለም፤ የዳበረ አዕምሮና አስተሳሰብ ከሌለ ትርጉም የለውም” ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ የህወሓት አመለካከትና አስተሳሰብ አውዳሚ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

ኃላፊው እንደተናገሩት፤ ትግራይ ውስጥ የነበሩ መሰረተ ልማቶችን ያፈረሳቸው ህወሓት ነው። በዚህ ሁኔታ ትግራይን መልሶ መገንባት ይቻላል ብለን አናምንም። ይህ አሸባሪ እስካለ ድረስ ትግራይን መልሶ ለማቋቋም የተያዘው 300 ሚሊዮን ዶላር በጀትም በጥንቃቄ ለህዝቡ ጥቅም እንዲውል ካልተደረገ ህወሓት ለራሱ እኩይ አላማ እንደሚያውለው ግልጽ ነው ብለዋል።

በትግራይ ክልል በትክክል የመልሶ ግንባታ ሥራ ለመስራት፣ ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ፍትህና እኩልነት እንዲሰፍን ከተፈለገ የህወሓት ኃይል ከክልሉ መውጣት መቻል አለበት። ካልሆነ ግን በጀቱ ለመሰረተ ልማት ግንባታ ሳይሆን ለህወሓት አላማ መጠቀሚያ ይሆናል፤ እንዲሁም ዘላቂ ልማትና መልሶ ግንባታ ይመጣል ተብሎ አይታሰብም። ልማት ያለው የለማ አስተሳሰብ ላይ ነው፤ ህወሓት ደግሞ ሰላምና ልማት የሚባሉ ነገሮች የሉትም። አሁንም በማሸነፍና በመሸነፍ ትርክት ውስጥ ያለ ቡድን ነው፤ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ተጨማሪ ችግሮችን ለመፍጠር እየተዘጋጀ ያለ ኃይል በመሆኑ ይህ ኃይል እስካለ ድረስ ትግራይን ወደ ልማት መመለስ አይታሰብም ብለዋል።

# የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በሻሸመኔ ከተማ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት በሻሸመኔ ከተማ የ35 አቅመ ደካሞች ቤቶችን በማደስ ለማስረከብ ሥራ ጀምሯል።

በቀጣዮቹ ሁለት ቀናትም በምዕራብ አርሲ ዞን ሁለት ወረዳዎች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የሰባት ሚሊዮን ብር የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ እንደሚደረግ ተገልጿል።

በቤት እድሳት ማስጀመር መርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አመራሮች በሰጡት አስተያየት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አህመድ ያስጀመሩትን የአረንጓዴ አሻራና የአቅመ ደካማ ቤቶች እድሳት ለአገር ጠቃሚ የሆነ ፕሮጀክት ነው። የአቅመ ደካማ ቤቶችን ማደስ፣ አብሮነታችንና ህብረ ብሄራዊ አንድነታችን ለማጠናከር ወሳኝ ነው። ይህን በጎ ተግባር አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉ ተናግረዋል።

የሻሸመኔ ከተማ ከንቲባ አቶ ወሾ ከድር በበኩላቸው ፤የፌዴራል ተቋማት አስታዋሽ ላጡና በከፋ ድህነት ውስጥ ለሚገኙ አረጋውያን ቤት ለመስራት ከተማዋን በመምረጣቸውን አመስግነዋል።



ከሶስት ዓመት በፊት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ የተጀመረው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ብዙ ጧሪ ያጡ አባቶችና እናቶችን ከመንገድ ላይ በማንሳት የቤት ባለቤት እያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለያዩ ከተሞች በመስጊድ፣ በቤተክርስቲያንና በመንገድ ላይ የሚገኙ በርካታ የሆኑ አቅመ ደካሞች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ሆነዋል። የቤት እድሳት ፕሮግራሙ ሌሎች በርካታ ዜጎችን ለመታደግ ትልቅ የበጎ አድራጎት ጥሪ ነው ሲሉ ከንቲባው ተናግረዋል።

በሌላ በኩልም ከሁለት ዓመት በፊት በጠላት ኃይሎች ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባት የነበረችው የሻሸመኔ ከተማ አሁን ላይ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ወደነበረችበት ተመልሳለች ያሉት ከንቲባው፤በህዝብ ተሳትፎ ብቻ 800 ቤቶች በላይ ተመልሰው ተገንብተው አሁን ነዋሪዎቿ በፍቅርና በመቻቻል እየኖሩባት መሆኑን ገልጸዋል።

በወቅቱ እንደ ቢቢሲ ያሉ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ሳይቀር ከተማዋ ከደረሰባት ውድመት አንጻር ወደ ነበረችበት ለመመለስ ከ50 ዓመት በላይ ይወስዳል ብለው ሲዘግቡ እንደነበር አስታውሰው፣ የሻሸመኔ ከተማ ህዝብና መላ ኢትዮጵያውያን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሻሸመኔ ከተማ ወደነበረችበት ለመመለስ ያሳዩት ትብብር ኢትዮጵያዊ አንድነታችን ያሳየ መሆኑን ገልጸዋል።

በቤት እድሳት ማስጀመሩ መርሐግብር የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አመራሮችና የምዕራብ አርሲ ዞን ዋና አስተዳዳሪና ሌሎች አመራሮች መገኘታቸው ታውቋል።ቤት በማደስ በመርሐ ግብሩ ላይ 16 የፌዴራል ሴክተር መስሪያ ቤቶች እንደሚሳተፉ ተመላክቷል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሄት



ለቢሊዮኖች ዶላር ገቢ እየተንደረደረ ያለው አረንጓዴ ወርቅ

ገጽ 13



መልካም ተሞክሮዎች የታዩበት የመንገድ ፕሮጀክት

ገጽ 14



## «ሠላምን በአገር ላይ መልሶ ለማምጣት ብቸኛውና አስተማማኝ መንገድ ፖለቲካዊ ምክክር ነው»

- ሬሚ ማሪሾ
በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር

ገጽ 6



አግኝቶ ማጣትን - ከራስ የማስታረቅ ሩጫ

ገጽ 16

በውስጥ ገጾች

ታታሪዋን እማወራ ለመግደል ያልሳሳው አባወራ ገጽ 10

የክረምት ትጋት ለበጋ እረፍትና ሐሴት ገጽ 11

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «ሠላምን በአገር ላይ መልሶ ለማምጣት ብቸኛውና አስተማማኝ መንገድ ፖለቲካዊ ምክክር ነው»

- በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሬሚ ማሪሾ

ማህሌት አብዱል

**ኢትዮጵያ አንድ ክፍለ ዘመን በላይ ታሪካዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ካላቸው የአውሮፓ አገራት መካከል ፈረንሳይ በግንባር ቀደም ትጠቀሳለች። አገራቱ በተለይም ካለፉት 125 ዓመታት ጀምሮ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ብሎም በህዝብ ለህዝብ ትስስር ጠንካራ የሚባል ግንኙነት ያላቸው ወዳጅ አገራት ናቸው። በዚህ ግንኙነትም በዋናነት ኢኮኖሚያዊ ትብብር በመፍጠር የጋራ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎችን አከናውነዋል። ለአብነት ያህልም በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የተሰራው የመጀመሪያው የባቡር መስመር ዝርጋት በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀስ ነው። የፈረንሳይ የኪነ-ህንፃ ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ከተሞች እድገት ያሳረፉት አሻራም ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው።**

**የለውጡ መንግስት መምጣቱን ተከትሎ ደግሞ የሁለቱ አገራት ሁለንተናዊ ግንኙነት ይበልጥ እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን በተለይም ፈረንሳይ በወታደራዊ መስክ ያላትን ልምድና የቴክኖሎጂ ተሞክሮ ለኢትዮጵያ ማካፈል የምትችልበትን እድል የሚፈጥር ስምምነት ፈፅመውም ነበር። በዚህም የስምምነት ማዕቀፍ በዋናነት የኢትዮጵያን ባህር ኃይል ዳግም ለማደራጀት በሚደረገው ጥረት ፈረንሳይ ቃል መግባቷን እናስታውሳለን። በዚህና ለአንድ ዓመት ያህል እየተከበረ ባለው 125ኛ ዓመት ዲፕሎማሲ ግንኙነት ዙሪያ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሆነው እየሰሩ ካሉት አምባሳደር ሬሚ ማሪሾ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።**

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያና ፈረንሳይ የዲፕሎማሲ ግንኙነት 125ኛ ዓመት እየተከበረ እንደሆነ ይታወቃል። እስቲ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የተገኙ ዋና ዋና ስኬቶች ምን እንደሆኑ ያብራሩልንና ውይይታችንን እንጀምር ?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** በቅድሚያ በአፍሪካ የፖለቲካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ተመድቤ በመስራቴ ያለኝን ታላቅ ደስታ ለመግለፅ እወዳለሁ። ፈረንሳይና ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ጋር ሲነፃፀር ረጅም እድሜ ያስቆጠረ እና ጠንካራ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ነው ያላት። ኢምባሲያችን በእድሜው ረጅሙ ሲሆን የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ተቋቁሞ የሁለቱን አገራት ወዳጅነት የበለጠ እንዲጠናከር ለበርካታ ዓመታት ሲሰራ ቆይቷል። በጣም አስፈላጊው ነገር ደግሞ አገራቱ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ሲፈጥሩ ገለልተኛ እና ሉዓላዊ ሆነው መቀጠሉ ነው።

ከዚህ በመነሳት ከኢትዮጵያ ጋር ያለንን የዲፕሎማሲ ግንኙነት የተለየና የህዝብ ለህዝብ ትስስሩም ጠንካራ ነው ማለት ይቻላል። ይህንን በዓል ማክበራችንም የሁለቱንም አገራት የዲፕሎማሲ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር እና ለመገንባት ብሎም በጋራ ለምንሰራቸው የልማት ፕሮጀክቶች የጀርባ አጥንት ሆኖ ያገለግላል ብለን እናምናለን። ለዚህም ነው የዚህን ዓመት እያንዳንዱን ወር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ሰይመን ስናከብር የቆየነው። ለአብነት ያህልም በትምህርትና ቋንቋ ዘርፎች በጋራ በምንሰራባቸው ሊሴ ገብረማርያምና በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም በአገር ፍቅር ቲያትር ቤት የሙዚቃ ኮንሰርት በማዘጋጀት አክብረናል። በቅርቡም በአርቴክቸሩ ዘርፍ የፈረንሳይ ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ኪነ-ህንፃ ላይ እንዲሁም ከተማዋን በማዘመን ረገድ ያላቸውን አበርክቶ የሚዳስስ ዘጋቢ ፊልም ታይቷል።

በተጨማሪም በሥነ-ቅርስ ጥበቃ ሥራዎችም አገራችን ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገች እንደሆነ ይታወቃል። ከእነዚህም መካከል በላሊበላ ውቅር አብያተ-ክርስቲያናት እድሳትና በእንጦጦ ፓርክ ግንባታ ላይ ፈረንሳይ ከኢትዮጵያ ጎን በመሆን የልማት አጋርነቷን በማረጋገጥ ላይ ትገኛለች። በቀጣይ ወራትም የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያጎለብቱ መርሃ ግብሮች በዓሉ የሚከበር ነው የሚሆነው። በመስከረም ወር የላሊበላ ስሪ-ዲ ኤግዚቢሽን በእንጦጦ ፓርክ ይከፈታል። ስለዚህ ይህንን የጋራ ስኬት ወደፊት ለጋራ ፕሮጀክት ለመገንባት የሁለትዮሽ ግንኙነቱን አንድ ገጽታ በሚያሳይ መልኩ በየወሩ እያከበርን እንቀጥላለን።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ በዓይነቱ ልዩ የሆነ የፈረንሳይ የብቅል ፋብሪካ በአዲስ አበባ መቋቋሙ ይታወሳል። በእናንተ እይታ ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ምን ያህል ተስማሚ ናት?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት ያላት አገር ነች። በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ መዋዕለንዋያቸውን ለማፍሰስ የሚመጡ የፈረንሳይ ኩባንያዎች ቁጥርም ከጊዜ ወደ ጊዜ ጨምሯል። ለዚህም ቀደም ብለን ያነሳነው የብቅል አምራች ፋብሪካ ኢንቨስትመንት ጥሩ ማሳያ ነው። ይህንን ፕሮጀክት የሚተገብረው የፈረንሳይ ኩባንያ ከኢትዮጵያ የልማት ስትራቴጂ ጋር መጣጣም መቻል አለበት። የዚህ ብቅል ፋብሪካ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ከውጭ የሚያስገባውን ለመተካት ያስችላል ተብሎ ትልቅ ቦታ የተሰጠው ነው።

በተመሳሳይ እህት ኩባንያ የሆነው ቦልት ማልት ከተሰኘውና ደብረብርሀን ላይ የተቋቋመው ፋብሪካም አገሪቱ ለብቅል የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ይቀንሳል ተብሎ ይታመናል። በዚህ ረገድ የመንግስት ስትራቴጂ ግልፅ ነው። ስለዚህ ቢራ ፋብሪካዎች ከውጭ ከማስመጣት ይልቅ በአገር ውስጥ የሚመረተውን ብቅል እንዲገዙ የግብር ማበረታቻም አለ። ስለዚህ ይህ ለኢንቨስትመንት በጣም ተስማሚ ነው ማለት ይቻላል።.

ይሁንና ሊፈቱ የሚገቡ ብዙ ችግሮች አሉ፤ እነዚህ ኩባንያዎች በዋናነት በውጭ ምንዛሬ እጥረትና በተንዛዛ አሰራር ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ እየተፈተኑ ነው ያሉት። እንደሚታወቀው ኩባንያዎቹ መለዋወጫ እቃዎችንና ወሳኝ ግብዓቶቹን ለፋብሪካው ከውጭ ማስመጣት አለባቸው። ሆኖም የውጭ ምንዛሬ እጥረት በመኖሩ ስራቸውን በአግባቡ ለመከወን ተቸግረዋል። በእርግጥ ይሄ ችግር የፈረንሳይ ኩባንያዎች ላይ ብቻ ያጋጠመ ሳይሆን እንደአገር የሚታይ ነው። በግሌ እንዲሰመርበት የምፈልገው ነገር ግን ይህ ኢንቨስትመንት ለዚህች አገር እድገት ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ እነዚህን ችግሮች መፍታት ወሳኝ መሆኑን ነው።

በነገራችን ላይ በቅርቡ ቱሉ ሞዬ ጂኦ-ተርማል 150 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የሚያስችል ፕሮጀክት ለማቋቋም ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ውል የተፈራረምን ሲሆን ለፕሮጀክቱ ተፈጻሚነት ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየሰራን ነው። በመሆኑም 100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ የሚደረግበት ይሄው ኢንቨስትመንት ኢትዮጵያ ከታዳሽ ኃይል የምታገኘውን የኤሌክትሪክ ኃይል መጠን በእጅጉ ይጨምራል ተብሎ የሚታመንበት ነው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ባላት እምቅ ሀብት የፈረንሳይ ኩባንያዎች ተሳትፏቸውን እንዲያጎለብቱ በቀጣይነት እንሰራለን።

**አዲስ ዘመን፡- እርሶ እንዳነሱት ምንም እንኳን ኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ችግር ቢኖርባትም የብቅል ፋብሪካው በኢትዮጵያ መገንባት ሌሎች የፈረንሳይ ባለሃብቶችን ለመሳብ አያስችልም ብለው ያምናሉ?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** ትክክለኛ ጥያቄ ነው ያነሳሽው፤ ደግሞ ይህንን ብዙዎቻችንን የምንስማማበት ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ባለሀብቶች እድሉን ፈልገው ሲመጡ ኤምባሲያችን ከኢትዮጵያ ባለስልጣናት ጋር የማገናኘት ሥራ የሚሰራው። ምክንያቱም አቅም ያለው አንድ ኩባንያ ወደ አገር ውስጥ መምጣቱ ለሌሎች በር ከፋች ነው የሚሆነው። እዚህ ጉዳይ አሳማኙም ነገር የሚሆነው ቀድሞ የገባውን ስራ የጀመረው ኩባንያ ተሞክሮ ነው ሌሎችን ለመሳብ የሚያስችለው። ይህ የቀደመው ድርጅት ያሳለፈው ውጣ ውረድና የደረሰበት ስኬት ለሌሎች አርዓያ ለመሆን እድል የሚሰጠው ነው የሚሆነው። አንቺም እንዳልሽው የፈረንሳዩ ብቅል አምራች ኩባንያ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ለሌሎች አለምአቀፍ የፈረንሳይ ኩባንያዎች ትኩረትን የሚስብ ነው የሚሆነው።

**አዲስ ዘመን፡- በተያዘው ዓመት ግንቦት ወር ላይ ለአቅም ግንባታ እና ለቅርስ ጥበቃ 19 ሚሊዮን ዩሮ የሚሆን ስምምነት መፈረሙ ይታወሳል። ይህ ስምምነት መቼ ነው ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** አጠቃላይ ወጪው ለሁለት የተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚውል ነው። አንደኛው ለኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ማሰልጠኛ ማዕከል ግንባታ የሚውል ነው። ቀሪው ደግሞ የብሔራዊ ቤተመንግስትን ወደ ሙዚየምነት ለመቀየር ለታቀደው ፕሮጀክት የተመደበው ነው። በመሰረቱ እኛ በኢትዮጵያ ሁለት ወሳኝ የቅርስ ጥበቃ ስራ የምናከናውንበት ፕሮጀክቶች አሉን። የመጀመሪያው ላሊበላ ውቅር አብያተ-ክርስቲያናት ጥበቃና እድሳት ስራ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አስቀድሜ ያነሳሁት የብሔራዊ ቤተመንግስቱ ወደ ሙዚየም የመለወጥ ስራ ነው።

በነገራችን ላይ ይህ የሙዚየም ግንባታ ስራ ትልቅና 14ሺ ካሬ ቦታ የሚሸፍን ነው። የሲቪል ስራው ተጀምሯል፤ የአቅም ግንባታው ስራው ደግሞ የሚቀጥል ነው የሚሆነው። ሙዚየሙን የሚያስተዳድሩ ባለሙያዎችን የማሰልጠኑ ስራ በፈረንሳይ ታዋቂ የሆነው ቬርሳይ ሙዚየም አስተባባሪነት የሚመራ ሲሆን የዚህ ሙዚየም ከፍተኛ ባለሙያዎች ለኢትየጵያውያን ባለሙያዎች የቴክኖሎጂ ሽግግርና ድጋፍ የሚደረጉ ነው የሚሆነው። ይህም የሚደረገው የኢትዮጵያ ታሪክና ቱፊት በጠበቀ መልኩ ነው። የሙዚየም መገንባት ለኢትዮጵውያውያን የታሪክ አሻራ የሚያንፀባርቅ ከመሆኑም ባሻገር ቱሪስትን የሚስብ ነው የሚሆነው። እንዲህ አይነቱ መስህብ በተለይ ቱሪስቶች በከተማዋ ለረጅም ቀናት እንዲቆዩ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። ምክንያቱም የሁለቱም ፕሮጀክቶቻችን ዋነኛ አላማ ቅርሶችን ማሥጠበቅ ብቻ ሳይሆን የቱሪስቱን ቁጥር መጨመርና የስራ እድል መፍጠር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ጋር ተያይዞ በየዘርፉ የምታደርጉትን ድጋፍ እንዴት ነው የምትገመግሙት ?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** በኢትዮጵያ ለምንደግፋቸው እያንዳንዱ ፕሮጀክት ክትትል የሚያደርግ ቋሚ ኮሚቴ አዋቅረናል። ይህንን የክትትል ሥራ የምናከናውነው ግን ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በመተባበር ነው። በዚህ ኮሜቴ አማካኝነት በየጊዜው የፕሮጀክቶቹን አተገባበር ሪፖርት ይቀርብና እንገመግማለን። ፕሮጀክቶቹ እስከሚጠናቀቁ ድረስ በዚህ መልኩ የመጡ ለውጦች የሚፈተሹና ችግሮች እንዲታረሙ የሚደረግበት አሰራር አለን።

**አዲስ ዘመን፡- የለውጡ መንግስት መምጣቱን ተከትሎ ኢትዮጵያና ፈረንሳይ በጋራ ለመስራት ከተስማሟቸው ሥምምነቶች አንዱ ወታደራዊ ድጋፍ ነበር። ሆኖም በዚህ ማዕቀፍ ያሉ ስምምነቶች በታሰበው ልክ እየተተገበሩ አይደለም። ለመሆኑ ምክንያቱ ምንድን ነው?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** በነገራችን ላይ ስምምነቱ አሁንም እንዳለ ነው፤ ይህም ስምምነት እንዳልሽው



ፎቶ፡- እዮብ ተፈሪ

# የዘመን እንግዳ



ወታደራዊ ትብብር ላይ የተመሰረተ ሲሆን ለጊዜው እንዲዘገይ ተደርጓል። ግን በተቻለ ፍጥነት እንዲቀጥል ይደረጋል። ይህም የሚሆነው ግን በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ግጭት ሲቆምና በተሻለ መልኩ ለውጥ ማምጣት ሲችል ነው። ስለዚህ ይህ የወታደራዊ ስምምነት ተግባራዊ እንዳይሆን የተደረገው በቀጥታ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተፈፅሟል ተብሎ በመታመኑ ነው። ይህንንም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽኑ የተገለፀ ሲሆን በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ መንግስት ጠንካራ የሆነ ቁርጠኝነት አሳይቷል። በተለይ ተፈፅመዋል በተባሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በመርመርና ሪፖርቶችን በማጣራት ረገድ ያሳየው ተነሳሽነት የሚደነቅ ነው። እኛም ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር ተቀራርበን የምንሰራ በመሆኑ የመጡ ለውጦችን ለማየት ችለናል። ይህ ግን ወደ ፖለቲካዊ ውይይት ማደግ አለበት ብለን እናምናለን። እነዚህ ሁኔታዎች እንደተስተካከሉ ግን በተቻለ ፍጥነትና ሁኔታ በስምምነቱ መሰረት ድጋፎቹ የሚቀጥሉ ነው የሚሆኑት። በተለይም የኢትዮጵያ ባህር ኃይል እንዲጠናከር አገራችን በጋራ የምትሰራ ነው የሚሆነው።

**አዲስ ዘመን፡- እርሶም እንዳሉት የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ ብሔራዊ መግባባት እንዲመጣ የምክክር ኮሚሽን እስከማዋቀር ድረስ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው የሚገኘው። እርሶ ይህንን የመንግስትን ጥረት እንዴት ይመለከቱታል?**

**አምባሳደርሬሚ፡-** ለእኔ ይህ ትልቅና የሚበረታታ ዜና ነው። የእኔ መንግስትም ይህንን የኢትዮጵያ መንግስት እያደረገ ያለውን ጥረት በይፋ አድንቋል። ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ መግለጫ ባናወጣም በቀጥታ ግን ከኢትዮጵያ መንግስት የሚመለከታቸው አመራሮች ጋር ውይይት አድርገናል። በወቅቱ በዚህ ጦርነት ኢትዮጵያ የምታተርፈው አንዳች ነገር እንደሌለ አቋማችንን አስታውቀናል። ምክንያቱም ይህ ጦርነት ዋነኛ ተጎጂ የሚያደርጋቸው ንፁሃንን በመሆኑ ነው። ሠላም ለማስፈን ደግሞ ብቸኛው አማራጭ በፖለቲካዊ መረጋጋት መፈጠሩ ነው።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ መንግስት ሠላም እንዲሰፍን ሲል የተናጠል ተኩስ አቁም ከማድረግ ጀምሮ እስረኞችን በመፍታት የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የውይይት መድረክ ለመፍጠር የተጀመረው በጣም የሚበረታታ ነው። ሠላምን በአገር ላይ መልሶ ለማምጣት ብቸኛውና አስተማማኝ መንገድ ፖለቲካዊ ምክክር ነው። እኛ ከራሳችን ተሞክሮ በመነሳት በሌሎች አካባቢዎች ያሉ ቀውሶች ልምድ፣ ፖለቲካዊ መፍትሄ ብቻ ዘላቂ ሰላም ሊያመጣ ይችላል ብለን እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ለህዝቦቿ ልማትን ማምጣት ብቻ ሳይሆን ጎረቤቶቿን ተጠቃሚ ማድረግ እንዳለባት እየጠቆመች ያለች ሲሆን ከዚህም ባሻገር ታላቁ ህዳሴ ግድብ አንዱ ሲሆን ይችላል። ነገር ግን የተሳሳተ መረጃ በኢትዮጵያ ላይ ፈተና የሆነባት ይመስላል። ይህ እንዴት ነው የተስተናገደው ብለው ያስባሉ?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ለማንኛውም አገር እድገት የኤሌክትሪክ ሃይል የማምረት አቅም ማሳደግ ቁልፍ ነው ብዬ አስባለሁ። በዚህ ረገድ አሁንም ቢሆን የመብራት አገልግሎት የማያገኝ እጅግ በጣም ብዙ ኢትዮጵያዊ አለ። ከዚህ ባሻገርም በመንግስት የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ሁሉ ልክ እንደ ኢንደስትሪ ፓርኩ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልጋቸዋል። ስለሆነም የኤሌክትሪክ ኃይል የማምረት አቅምን በተለይም በታዳሽ ሀይል አቅም ማሳደግ በጣም አስፈላጊ መሆኑም አገራችን ታምናለች። ለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት ፈረንሳይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የጂኦተርማል ኤሌክትሪክ ምርትን ለማሳደግ ከኢትዮጵያ መንግስት ጎን ሆኖ እየሰራች ያለችው። በዚህ አጋጣሚ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ የማምረት አቅምን ማሳደግን በተመለከተ አገራችን ምንም ጥያቄ የሌላት መሆኑን መግለፅ እወዳለሁ።

በመሆኑም የአባይ ውሃም ሆነ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሁሉም የተፋሰሱ አገራት ትስስር እንጂ የክርክር ጉዳይ መሆን የለበትም። በዚህ ረገድ በአውሮፓም ሆነ በአፍሪካ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ወንዞችን በጋራ በሰላም መጠቀምና ማስተዳደር ላይ አገራት ጥሩ ተሞክሮ አላቸው። ለአብነት ያህልም በአውሮፓ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ኔዘርላንድስ እና ቤልጂየም መጥቀስ ይቻላል። በምዕራብ አፍሪካ የሚገኘው የሴንጋል ወንዝም ላይም ማሊ፣ ሴኔጋል እና ሞሪታኒያ የወንዙን ተፋሰስ በጋራ ለማስተዳደርና ለመጠቀም ተስማምተው እየሰሩ ነው የሚገኙት። በመሆኑም በአባይ ወንዝ ላይም በተመሳሳይ ኢትዮጵያ፤ ሱዳንና ግብፅ በጋራ ለመጠቀምና ለማስተዳደር መስማማት አለባቸው የሚል እምነት አለኝ። በዋናነትም በአፍሪካ ህብረት አደራዳሪነት የሚደረገው ውይይት መቀጠልና የጋራ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ እየተገበረች ያለችው የአገር በቀል ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ምን ያህል አዋጭ ነው ብለው ያምናሉ?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** አገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት እየተገበረች ያለችውን የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያም ሆነ ኢኮኖሚ ፕሮጀክቶችን ትደግፋለች። በተለይም በፈረንሳይ መንግስት የልማት ኤጀንሲ ባለሙያዎች አማካኝነት የኢኮኖሚ ማሻሻያ በመደገፍ የልማት አጋርነቷን እያረጋገጠች ነው ያለችው። እንዲሁም የመንግስት ኩባንያዎችን አስተዳደር ለማሻሻል እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ መርሃ ግብር በአገሪቱ እንዲተገበር አገራችን ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገች ነው። በዋናነትም በገንዘብ እና ባለሙያዎች በማሰባሰብ ኢትዮጵያ ያሰበችው የልማት ግብ ከስኬት እንዲደርስ በጋራ እየሰራን ነው የምንገኘው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ የቱሪስት አቅሟን በተሻለ ሁኔታ ማሳደግ አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን። በዚህረገድ በፈረንሳይ ውስጥ የቱሪዝም ሃብቷን በአግባቡ መጠቀም በመቻሏ ዘርፉ ለኢኮኖሚዋ ዋነኛ የጀርባ አጥንት ከመሆኑም ባሻገር አገሪቱ በዓለም የመጀመሪያዋ የቱሪስቶች መዳረሻ መሆን ችላለች። ይህ ብቻ ሳይሆን በዘርፉ ለበርካታ ፈረንሳውያን የስራ እድል መፍጠር ተችሏል። በአንፃሩ ግን ኢትዮጵያ ምንም እንኳን እምቅ የቱሪዝም ሃብት ቢኖራትም ከዘርፉ የሚገባውን ያህል ተጠቃሚ እየሆነች አይደለም። በመሆኑም ዘርፉን ለማሳደግና ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት አለበት። በተለይም ቱሪስቱ በአዲስ አበባ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆዩ ተጨማሪ ምክንያት የሚፈጥር ማንኛውም ፕሮጀክት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። የአገራችን መንግስትም በሙዚየሙና በላሊበላ ላይ የሚያደርገው ድጋፍም ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሰላም፣ ልማትና ሁለንተናዊ ክብር መረጋገጥ ያበረከተችውን አስተዋፅኦ እንዴት ያዩታል?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** በመግቢያዬ ላይ እንደገለፅኩት አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን መቀመጫ ሆና እያገለገለች ነው። አዲስ አበባም የአህጉሪቱ መዲና ሆና የተመረጠችው ኢትዮጵያ ለአህጉሪቱ ሰላምና አንድነት ባበረከተችው አስተዋፅኦ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። ከዚህ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ወታደሮች በሰላም ማስከበር እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፍ ለአካባቢው ሰላምና ደህንነት ያበረከቱትን አስተዋፅዖ የምንገነዘበው ነው። ስለዚህ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን። የፓን-አፍሪካን እንቅስቃሴ እና የፓን አፍሪካን ውህደት መገንባትን በተመለከተ ዋናው ነገር በተጨባጭ ፕሮጀክት ላይ መስራት ነው። ይህንን ያልኩት ከራሳችን የአውሮፓ ህብረት ልምድ በመነሳት ነው። እንደሚታወቀው እኛ ባለፈው ክፍለ ዘመን በነበሩት ጦርነቶች የተከሰቱት እና አገራዊ ጥቅማችንን በማቀናጀት ከብሄራዊ ጥቅም አልፈን የጋራ ጥቅምን ለመገንባት ወስነናል። በኢኮኖሚ ውህደት ያደረግነውም በዚሁ ምክንያት ነው። አሁን ደግሞ የአውሮፓ ህብረት ለአህጉሩ እጅግ ረጅሙን የሰላምና የብልጽግና ጊዜ የሰጠበት ወቅት ነው። ስለዚህ ከአፍሪካ ውህደት ጋር በተያያዘም በተለይም በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ማጠናከር ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ እናምናለን። ኢኮኖሚያዊ ውህደቱን እውን ለማድረግ በተጨባጭ ለመስራት ነፃ የንግድ ቀጠናው አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም።

እንደሚታወቀው ደግሞ የማዳበሪያ ዋጋም ሆነ የእህል ዋጋ እየጨመረ ያለው በዩክሬንና በሩስያ ጦርነት ምክንያት ነው። በዚህ ረገድ አፍሪካ የተቀናጀ አህጉራዊ ገበያን ብትጨምር አብዛኛው ችግር ሊቀረፍ ይችላል ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም ነፃ የንግድ ቀጠናው ከተፈጠረ ከሌሎች የአፍሪካ አገራት እህልና ማዳበሪያ ለማስገባት ቀላል ይሆናል። ስለዚህ የአፍሪካ ውህደት የመጨረሻ ግብ ልንደግፈው የምንችለው ይህንን በአውሮፓ ስላጋጠመን እና በዕለት ተዕለት ህይወታችን ለሁሉም ዜጎች የሚሰጠውን ጥቅም ስላሳለፍን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የለውጡ መንግስት መምጣቱን ተከትሎ የመናገር ና የመፃፍ ነፃነት በተጨባጭ ተግባራዊ እንዲሆን ተሰርቷል። በዚህ ረገድ በተለይም የመገናኛ ብዙሃን አቅም እንዲጎለብት የተሰራውን እንዴት ይመለከቱታል?**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** ልክ ነው፤ ይህ ጉዳይ አስቀድሜ ይህ ያልጠቀስኩት ኢትዮጵያና ፈረንሳይ በጋራ የሚሰሩበት አንዱ ገጽታ ነው፤ ለ125ኛ ዓመት የምስረታ በዓልም ትኩረት ከተሰጡ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ይሄ ነው። በነገራችን ላይ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው ጋዜጣ በፈረንሳይኛ ቋንቋ መታተሙ ይታወሳል። አሁንም ድረስ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ጋር ኤምባሲያችን ጠንካራ ግንኙነት ነው ያለው። ከዚህም ባሻገር በየጊዜው ለኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ስልጠና እና ድጋፍ እንሰጣለን።

ወደጥያቄሽ ስመጣ እንዳልሽው በተለይ ለመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች የመናገርና የመፃፍ ነፃነት እንዲከበር በመንግስት በኩል የተሰሩ መልካም ስራዎች አሉ። ሆኖም አገሪቱ ከሁለት ዓመታት በላይ ከዘለቀው ግጭት ጋር ተያይዞ ለመገናኛ ብዙሃኑ ባለሙያዎች አስቸጋሪ ነገር ሊኖር እንደሚችል ግልፅ ነው። በተለይም ገለልተኛ ሆኖ መዘገብ ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ ሊኖር እንደሚችል ግልፅ ነው። በመሰረቱ በቅርቡ በኢትዮጵያ ስላለው የፕሬስ ሁኔታና ስለቀጣይ አቅጣጫዎች ለመወያየት ከሁሉም የሚዲያ ሥራ አስኪያጅ ጋር ኮንፈረንስ አድርገን ነበር። ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሌሎች አገሮች ጦርነት እንደሚገጥማቸው ጋዜጠኞች ግንባሩ ላይ ለመድረስ ሁኔታውን ሙሉ በሙሉ ለመዘገብ አስቸጋሪ መሆኑን እናውቃለን። እንዲሁም በሁለቱ ወገኖች ፕሮፓጋንዳ ምክንያት ባለሙያዎቹ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ እንደሚሆኑ እንገነዘባለን።

በመሆኑም የራሱን የሥነ-ምግባር ደንብ ለመፍጠር ከኢትዮጵያ ሚዲያ ምክር ቤት ጋር በጋራ እየሰራን ነው። ይህ ደግሞ የጋዜጠኝነት ሙያ መንግሥት እንዲሠራው ከመጠየቅ ይልቅ የራሱን ሥነ-ምግባር፣ የጋዜጠኞችን የሥራ አካባቢ ማስተዳደር እንዲችል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን እምነት ተይዟል። በአጠቃላይ ግን በተለይ ካለፈው አንድ ዓመት ወዲህ አገሪቱ ያጋጠማት የፖለቲካ እና ወታደራዊ ቀውስ ጋዜጠኞች በነጻነት ለመስራት ምቹ ሁኔታ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ማንሳት የሚፈልጉት ሃሳብ ካለ እድሉን ልስጥዎት?**


**አምባሳደር ሬሚ፡-** ጥያቄሽ ሁሉንም ሃሳብ የሚሸፍን ይመስለኛል። ይሁንና ሰሞኑን ኤምባሲያችን የፈረንሳይን ብሔራዊ የነፃነት ቀን እያከበረ ነው ያለው። የጭካኔ ቀን የሆነውን ብሔራዊ ቀን እያከበርን ነው። ስለዚህ ቀኑ የፕሬዚደንታችን ልደት አይደለም፣ የነጻነት ቀን አይደለም፣ የሕገ መንግሥት ቀን አይደለም፣ አብዮት እያከበርን ነው። እንደሚታወቀው ይህ «ባስቲል ቀን »በመባል በየዓመቱ የምናከብረው በዓል የፈረንሳይ ህዝብ ከጭቆና ቀንበር ለመላቀቅ ብርቱ ተጋድሎ ያደረጉበትና የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉበት በመሆኑ በመላው ህዝባችን ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው። በመሆኑም ለመላው ህዝባችን ለዚህ የድል ቀን እንኳን አደረሳችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ውድ ጊዜዎትን ሰውተው ከእኛ ጋር ቆይታ ስላደረጉ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አምባሳደር ሬሚ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## ማህደረ ጤና

# የማህጸን ኢንፌክሽን




**እፀገነት አክሊሉ**

ሴቶች ለተለያዩ ማህበራዊና የጤና ችግሮች ውስጥ የማለፍ እድላቸው ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ሰፋ ያለ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በርካታ ምክንያቶችን ማንሳት ቢቻልም ዋናው ግን ተፈጥሯዊና ባህላዊ ጫናዎች ናቸው። ተፈጥሯዊውን እንኳን ብንመለከት በማርገዝ። በመውለድ ኋላም ልጆች በማሳደግ በኩል በሚያልፏቸው ሂደቶች እንዲሁም ሰውነታቸው ላይ በሚፈጠሩ የተለያዩ ለውጦች ለበርካታ አይነት ህመሞች ድካም የመጋለጥ እድላቸው ሰፊ ነው። አንዲት እናት መጸነሷን ካወቀችበት ጊዜ አንስቶ እስክትወልድ ድረስ አስፈላጊውን የአመጋገብ ሂደት ካልተከተለች ብሎም ተገቢውን የህክምና እርዳታ ማግኘት ካልቻለች የሚከሰቱ የጤና ችግሮች በርካታ ናቸው። እነዚህ ችግሮች ደግሞ በወቅቱ ተገቢውን ትኩረት ካላገኙ ከወሊድ በኋላም ተጠናክረው በመቀጠል ምናልባትም ሴቲቱን ለከፋ የጤና አደጋ የማጋለጣቸው ሁኔታ እጅግ በጣም ሰፊ ነው።

በሌላ በኩልም ሴቶች ቤተሰብ በማስተዳደር የሚሸከሙት ሀላፊነት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ይህ ደግሞ ለራሳቸው ጊዜ እንዳይሰጡ ያደርጋል። እራሳቸውን መንከባከብ ብሎም ሲያማቸው "ይሻለኛል" ከማለት ባለፈ ጠንከር ያለ ህክምናን በመውሰድ በኩል ክፍተቶች ይስተዋላሉ። እዚህ ላይ ግን ቁጥራቸው ብዙ ባይሆንም ያለቻቸውን ጊዜ አብቃቅተው ጤናቸውን የሚንከባከቡ ሴቶች የሉም ማለትም አይደለም። ነገር ግን አብዛኞቹ ሴቶች የሚያልፉበት የሕይወት መንገድ ለራስ ከመኖር ይልቅ ሌሎችን ማስቀደም ነውና በትንሹ ሊያልፉት በሚችሉት በሽታ ሁሉ ዋጋ ስከፍሉ ይስተዋላል።

ሴቶች በቀላሉ ሊድኑ በሚችሉ በሽታዎች ለሞት የመዳረግ መጠናቸው ላቅ ያለ መሆኑን ብዙ ጥናቶች ያመለክታሉ። ከዚህም መካከል የማህጸን ኢንፌክሽን ብዙ ሴቶች ላይ የሚከሰት በዛው መጠን ደግሞ ትኩረት ባለመስጠታቸው ምክንያት ከፍ ላለ የጤና ችግር የሚጋለጡበት የህመም አይነት ሆኖ ተመዝግቧል።

የማህጸን ኢንፌክሽን መከሰቻ ምክንያቱ፣ ከተከሰተም በኋላ ሊደረግ ስለሚገባው ህክምናና ተያያዥ ጉዳዮች በዚህ ጽሁፍ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

### የማህጸን ኢንፌክሽን ምንድን ነው?

በጥቅል መጠሪያው የማህጸን ኢንፌክሽ (Pelvic Inflammatory Disease (PID)) የሚባለው የሴቶች የመራቢያ አካላትን (ስርዓትን) የሚያጠቃ በሽታ ሲሆን የሴቶች የመራቢያ አካላት ስንል የሚከተሉትን ያቀፈ ነው፣ ማሕፀን፣ ሴት ልጅ ነፍሰ ጡር ስትሆን ልጅ የሚሸከመው አካል፣ አቫሪ በየወሩ እንቁላል የሚያዘጋጁ አካላት፣ የፉሎፒያን ቱቦዎች አቫሪዎችን ከማህፀን ጋር የሚያገናኙ ቱቦዎች፣ ብልት ማህፀን ከውጭ ጋር የሚያገናኘው ክፍል ናቸው ።

የማህጸን ኢንፌክሽን ሲከሰት መለስተኛ የሆኑ ምልክቶች ሊታዩ አሊያም ምንም አይነት ምልክት ላይታይ ይችላል። በዚህም ምክንያት አንዲት ሴት ይህ የጤና ችግር እንዳለባት ሳታውቅ ልትቆይና ችግሩ እየቆየ ውስጥ ውስጡን ተባብሶ ለማርገዝ እስከመቸገርና ከፍተኛ ለሆነ የዳሌ ህመም እስከማጋለጥ ሊያደርሳት ይችላል።

### የማህጸን ኢንፌክሽን ምልክቶቹ ምንድናቸው?

አንዲት ሴት የማህጸን ኢንፌክሽን አጋጥሟታል ለማለት የተለያዩ ምልክቶችን ማሳየት ይኖርባታል። ነገር ግን ከላይ እንዳልነው አንዳንድ ጊዜ ምንም ምልክት ሳያሳይ ውስጥ ውስጡን ችግሩ አድጎ ከፍ ወዳለ የጤና ችግር ሊደርስ ይችላል።

ከምልክቶቹ መካከል ማህፀን እና የወገብ ህመም፣ በወሲብ ጊዜ የሚያጋጥም ህመም፣ ከብልት የሚወጣ ፈሳሽ (ሽታ ያለው)፣ ሽንት በሚሸናበት ጊዜ የሚያጋጥም ህመም፣ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለት፣ ድካም፣ ማቅለሽለሽ፣ ማስመለስ፣ በወር አበባ ጊዜ የሚመጣ ህመም መጨመርና ሌሎችም መሆናቸውን ባለሙያዎች ይናገራሉ።

**የማህጸን ኢንፌክሽን ምልክቶች ከታዩ በአፋጣኝ ሀኪም ጋር በመቅረብና አስፈላጊውን ህክምና በማድረግ በመራቢያ አካላት ላይ በማህጸን ኢንፌክሽን ምክንያት ሊፈጠር የሚችልን ጠባሳ መከላከልም እንደሚቻል መረጃዎች ያሳያሉ**

### የማህጸን ኢንፌክሽን በምን ምክንያት ይከሰታል?

ሁሉም አይነት ህመሞች የመከሰቻ መንገዳቸው የተለያየ ነው። የማህጸን ኢንፌክሽንም ብዙ ዓይነት መከሰቻ ምክንያቶች ያሉት ሲሆን ዋናው ግን ባክቴሪያዎች የማህጸን ኢንፌክሽንን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ በዋነኝነት ደግሞ የዚህ በሽታ መንስዔ ተደርገው የሚጠቀሰው ግኖሪሃን ( gonorrhea) የሚባለው የባክቴሪያ ዓይነት ነው።

ይህ ባክቴሪያ ጥንቃቄ በጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ወደ ሴቷ ማህጸን ሊገባና በሽታው እንዲከሰት ሊያደርግ እንደሚችልም መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከዚህም በተጨማሪ በወር አበባ ጊዜ፣ በወሊድ ወቅት እንዲሁም በማህጸን ውስጥ በሚቀመጡ የእርግዝና መከላከያዎች አማካይነት ባክቴሪያው ወደ ሰውነት ሊገባ የሚችልበት እድልም ሰፊ መሆኑ ይነገራል። ይህ ባክቴሪያ ደግሞ እንደዚህ ባሉት ጊዜያት በሚፈጠሩ የጥንቃቄ ጉድለቶች ወደ ማህጸን ሊገባና በሽታውን ሊያስከትል ይችላል።

### የማህጸን ኢንፌክሽን የሚያስከትለው ጉዳት

የማህጸን ኢንፌክሽን በጊዜ ካልታከመ ብዙ የጤና መቃወሶችን ሊያስከትል ይችላል። ከነዚህም መካከል ከማህጸን ውጪ እርግዝና (Ectopic pregnancy)። የማህጸን ኢንፌክሽን በሽታ በፉሎፒያን ቲዩብ ውስጥ ጠባሳ እንዲፈጠር ማድረግ፤ ይህም ጠባሳ ደግሞ ለጽንሰት የደረሰው የሴቷ እንቁላል ጽንስ ወደሚፈጠርበት ማህጸን እንዳይሄድ በማገድ ጽንሱ ከማህጸን ውጭ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል። መሃንነት (infertility) በማህጸን ኢንፌክሽን በተደጋጋሚ የተጠቃች ሴት የመራቢያ አካላቷ ስለሚጎዱ ለመሃንነት የመጋለጥ እድሏ ከፍተኛ ነው ። የተራዘመ የዳሌ ህመም (chronic pelvic pain) ሌላው በኢንፌክሽኑ ምክንያት የሚከሰት ችግር ነው።

### የማህፀን ኢንፌክሽን ህክምና

አንዲት ሴት የማህፀን ኢንፌክሽን እንደያዛት የሚታወቀው ወደ ሃኪም ሄዳ አስፈላጊ የሆኑ ምርመራዎች ከተደረጉላት በኋላ ነው። ከነዚህ ምርመራዎች መካከል የሽንትና የደም ምርመራ፤ የማህፀን ምርመራ ወይም አልትራሳውንድ ሲሆኑ ከምርመራዎቹ በኋላ ሃኪሙ አስፈላጊ የሆኑ ፀረ-ባክቴሪያ መድሃኒቶችን ሊያዝ ይችላል።

የሚታዘዘውን መድሃኒት በትክክልና በሰዓቱ ካልተወሰደ ግን የማህፀን ኢንፌክሽንን ማዳን በጣም ከባድ ነው የሚሆነው ። እዚህ ላይ አንዲት ሴት የማህጸን ኢንፌክሽን እንዳጋጠማት ከታወቀ የፍቅር ጓደኛዋ አልያም የትዳር አጋሯ አብሯት እንዲታከም ቢደረግ ችግሩን በዘላቂነት መፍታት ይቻላል።

እንዲሁም መድሃኒቱን በትክክል ከወሰዱ በኋላ እንደገና ተመርምሮ ነፃ መሆን አለመሆን እስኪታወቅ ድረስ ወሲብ አለመፈጸም ህክምናው ውጤታማ እንዲሆን ያግዘዋል።

### የማህጸን ኢንፌክሽን ያለባት ሴት ማርገዝ ብትፈልግ?

በአንዲት ሴት ላይ የማህጸን ኢንፌክሽን ተከስቶ ከነበረ ምናልባት ለማርገዝ ልትቸገር ትችላለች። ምክንያቱም በሽታው በፉሎፒያን ቱቦዎች ላይ ጠባሳ ሊያስከትል ስለሚችል ነው። ምናልባት እርግዝና እንኳን ቢፈጠር ከማህጸን ውጭ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው። በመሆኑም ሴትየዋ ለማርገዝ በምትሞክርበት ጊዜ በማህጸን ኢንፌክሽን ተጠቅታ እንደነበር ለሃኪሟ መንገር በጣም አስፈላጊ ብሎም የጽንሱንም የእናትየዋንም ጤና ለመጠበቅ በጣም ወሳኝ በመሆኑ ለሀኪም መንገር ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

የማህጸን ኢንፌክሽን ምልክቶች ከታዩ በአፋጣኝ ሃኪም ጋር በመቅረብና አስፈላጊውን ህክምና በማድረግ በመራቢያ አካላት ላይ በማህጸን ኢንፌክሽን ምክንያት ሊፈጠር የሚችልን ጠባሳ መከላከልም እንደሚቻል መረጃዎች ያሳያሉ።

### የማህጸን ኢንፌክሽን እንዳይከሰት እንዴት እንከላከል

የማህጸን ኢንፌክሽን እንዳይከሰት የሚከተሉትን ማድረግ ያስፈልጋል። ወሲብ በሚያደርጉበት በማንኛውም ጊዜ የላቴክስ ኮንዶም መጠቀም፣ የአባላዘር በሽታ ምልክቶች ካለው ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ መቆጠብ፣ ህመሙ ከተፈጠረ በኋላ ወሲብ ላለመፈጸም (መታቀብ) ከመከላከያ መንገዶቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

**የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።**

# «ጭጋግና ጠል»

የክረምቱ አገባብ አስደስቶናል፤ ከብዶናልም፡፡ ደስታው ፈጣሪ ራርቶልን በቂ “ሰማያዊ ጠል” አግኝተን ተፈጥሮና ፍጡራን በጋራ መፈንደቃችን ሲሆን፤ በርካታ አካባቢዎች በጭጋግ ተሸፍነው እስከ እኩለ ቀን ድረስ መዋላቸው ደግሞ ክረምቱን ትንሽ ጠነን ሳያደርግብን እንዳልቀረ በብርዱ ማንቀጥቀጥ እየመዘንነው ነው፡፡

እትት እያሰኘ ወፍራም አልባሳት እንድንለብስ ያስገደደንን የክረምቱ መግቢያ ብርድ “አጥንት ዘልቆ ይገባል” በማለት መግለጽ የጀመርነው ሰኔ ጣጣውን ጨርሶ ከሐምሌ ወር ጋር ርክክቡን ለመፈጸም ቀናት ሲቀሩት እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡ “ቀድሞ የገባ ክረምት ለእሸት” እንዲሉ የሰኔና የሐምሌ ባህርይ መለዋወጥ እጅግም አላስከፋንም፡፡

ለዘመናት ተጣብቶን የኖረው የድርቅ መርገምት እንደለመደው ድንገት አድፍጦ በመከሰት በአገራችን የበጋ ወራት ያደረሰው የጉዳት ጠባሳ ገና ስላልጠገገ፤ “ዝናቡና ብርዱ በረታብን” እያልን ማማረራችንን ፈጣሪ እንደ አፍ ወለምታ እንዲቆጥርልን እንጂ የምር አድርጎት ባይቀጣን እንወዳለን፡፡ አንዳንድ ውለታ አስታዋሽ ዜጎች ለተያያዝነው መልካምና ተመጣጣኝ የዝናብ ወቅት ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ለተተገበረው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር “ገለታ” ሲያቀርቡ እያደመጥን ነው፡፡ ጸሐፊውም ከአመስጋኞቹ ጋር ይተባበራል፡፡

የክረምቱን መግባት ተከትሎ “ችግኝ ተከላ” የሚለው ሀረግ ወትሯዊ የዜጎች ሁሉ የተለመደ መግባቢያ ወደ መሆን ደረጃ ከፍ ማለቱ ትልቅ የባህል ለውጥ ውጤት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ የአረንጓዴ አሻራ ትሩፋት ወጣኙ፣ ጎትጓቹ፣ ቀዳሚ አስተባባሪውና ተግባሪው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ከወንበራችን ከፍ ብለን ብናመሰግናቸው ይገባቸዋል ባይ ነን፡፡

መቼም ግራ ገቡ ዲሞክራሲያችን በአመለካከታችን ግራና ቀኝ እንድንረግጥ አንዴ አወፍፎናልና “ምሥጋናው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አይገባም!” በማለት የፖለቲካ አክርማ የሚሰነጥቁና “አመስጋኞችን” የሚኮንኑ ዜጎች የሚኖሩም ከሆነ መሟገቻ ሃሳባቸውን ብናደምጥላቸው ክፋት የለውም፡፡

አብዛኛው የማሕበረሰብ ክፍል አባላት በተባበረ ድምጽ በጎነትን አመስገኖ ክፋትን ለመኮነን ለምን አቅም እንዳጣና ሞራሉ እንደወደቀ ተመራማሪዎች ጥናት አድርገው ችግሩንና የመፈወሻውን ዘዴ ቢያመላክቱን አንጠላም፡፡ ያለበለዚያ በዚህ የተሳከረ የማሕበራዊ ሚዲያ ሜዳ እየፈነጩ የጎሊናቸውን ጨርቅ ጥለው ያበዱ ውሱን ዜጎች ወደ ቀልብያቸው ተመልሰው ካልተፈወሱ በስተቀር ነገም ለከፋ ጭጋግ ተጋላጭ መሆናችን አይቀርም፡፡ መመስጋገን፣ መደናነቅ፣ መከባበር ወደፊት የታሪካችን አካል እንጂ የኑሯችን መገለጫዎች ከመሆን እንዳይደበዝዙ ስጋት ገብቶናል፡፡

አነሳሳችን ስለ ክረምቱ ጭጋግና ስለሚያለመልመን ጠል ጫን ብለን በዝርዝር ለመተረክ አይደለም፡፡ ይልቁንስ “ጭጋግና ጠል” የሚለው አባባል ወቅታዊውን የዕለት ተዕለት አኗኗራችንን በሚገባ ይገልጽልን ስለመሰለን ሀረጉን የተዋስነው ለተመሳስሎ እንዲረዳን ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት የተፈጥሮ ክስተቶች አማካይነት የየግላችንን ፈተና ብቻ ሳይሆን የአሁናዊ አገራዊ ኑሯችን መልክ ብንፈትሽበት

**የክረምቱን መግባት ተከትሎ «ችግኝ ተከላ»የሚለው ሀረግ ወትሯዊ የዜጎች ሁሉ የተለመደ መግባቢያ ወደ መሆን ደረጃ ከፍ ማለቱ ትልቅ የባህል ለውጥ ውጤት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም**

ጥሩ ገላጭ ይሆናል ብለን በማመን ጭምር ነው፡፡

ጭጋግ በደቃቅ የውሃ ነጠብጣብ ወይንም በብናኝ ቁሶች አለያም በአቧራዎች የተሞላ ሲሆን ለአደጋ የማጋለጥ አቅሙም ከፍ ያለ ነው፡፡ ሰሞኑን እንኳን በተለይ ማለዳ ማለዳ አዲስ አበባን እንደ ብርድ ልብስ እየሸፈና ያለው ጭጋግ ለብዙ ትራፊክ ነክ አደጋዎች መንስዔ ሲሆን ደጋግመን አስተውለናል፡፡

በአየር በረራ ላይም ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሮ ጥቂት የማይባሉ አውሮፕላኖቻችን ሳይቀሩ የግድ ስለሆነባቸው በጎረቤት አገራት የአየር መንገድ ተርሚኖሎች እስከ ማለፍ የደረሱ መሆናቸውን ከዜናዎች ተከታትለናል፡፡ በሰማያዊ ጠል የመሰልነው የዝናብ በረከት የመወደዱን ያህል የጭጋግ ክስተትም ባይኖር እያልን መመኘታችን ስለዚሁ ነው፡፡

### በጠል የሚመሰሉና እንደ በረከት ሲቆጠሩ የሚገባቸው አገራዊ ስኬቶች፤

የአገራችን ርእይ በእጅጉ የሚያማልል ነው፡፡ “ሃሴት እያደረግንና” በሃሌሉያ ዝማሬ እያደነቅናቸው ያሉት የተጠናቀቁና በመጠናቀቅ ላይ ያሉ የልማት ጅምሮች እንኳንስ ለእኛ ለባለጉዳዮቹ ዜጎች ቀርቶ ለባእዳንም ቢሆን “በመጎምዠት ምራቅ የሚያስውጡ” መሆናቸው አልጠፋንም፡፡ ሰሞኑን ብስራቱ ሊናኝ ቋፍ ላይ የደረሰውን የሦስተኛ ዙር የህዳሴ ግድባችንን የውሃ ሙሌት እንደ አንድ “ጠል” ወይንም በረከት የምንቆጥረው የዘመናችን ትውልድ አሻራ ያረፈበት ታላቅ ስኬት ስለሆነ ነው፡፡

በገበታ ለአገር ፕሮጀክት እየተፋጠኑ ያሉት ፕሮጀክቶች ከጥቂት ዓመታት በኋላ ተጠናቀው ወደ ስራ ሲገቡ አስተዋሽ አጥተው ሲያንጎላጅጁ የከረሙት አካባቢዎች ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ ማሰብ በራሱ ውስጥን ያረሰርሳል፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ “ከስንዴ ለማኝነት ወደ ስንዴ ላኪነት እንሸጋገራለን” የሚለው እቅድ ወደ ተግባር ሊለወጥ ጫፍ ላይ መድረሱን ከእኛዎቹ ብቻ ሳይሆን ከባእዳን አፍ ጭምር “ተግባራዊ እንደሚሆን” ማረጋገጫውን ስንሰማ ውስጣችንን አንዳች ልዩ የደስታ ስሜት ሲወረን ይታወቀናል፡፡

በዘርፈ ብዙ የማዲያት ደዌ የጠወለገው የአዲስ አበባ መልኳ በተለያዩ መገለጫዎች እየወዛ መሆኑን በድፍረት ባንገልጽ ኩነኔው እንኳን ቢቀር በውስጥ ጎሊናችን መገሰጻችን ግን አይቀርም፡፡ ከድህነት ወለል በታች እንዲማቅቁ የተፈረደባቸው ዜጎች ከዝናብና ከብርድ የማያስጥላቸውና ለወጉ ያህል ብቻ ቤት እየተባለ የሚጠቀሰው ደሳሳ ጎጂቸው እየፈረሰ ወደ ተሻለ መኖሪያ ሲሸጋገሩ መመልከት ኑሮውን ላልቀመስነው ለብዙዎቻችን ተራ ጉዳይ ቢመስልም የመከራውን ገፈት ሲጎነጩ ለኖሩት ግፉዓን ግን እንደ ዳግም ልደት መቆጠሩ ከልባችን ጠልቆ ባናመሰግን ኃጢያቱ ለእኛ በረከቱ ለእነርሱ መሆኑ አይቀርም፡፡

“በጠል” የሚመሰሉ እነዚህና መሰል በርካታ አገራዊ ስኬቶችንና ተስፋዎችን ባሰብን ቁጥር የዛሬያችን ጭጋግ ከብዶ ግራ እያጋባ ቢያንገዳግደንም ነገ አንዳች የብርሃን ጨረር እንደሚፈነጥቅና ጭለማችን እንደሚገፈፍ ማረጋገጫ ስለሚሆነን በእፎይታ መተንፈሳችን አይቀርም።

### ፈራን! ለምን ፈራችሁ አትበሉን!?

ከላይ የተዘረዘሩ መሰል ደስታዎችን አጣጥመን ባጨበጨብንላቸው አገራዊ ስኬቶች ገና ፈንድቀን ሳንጨርስ እያጋጠሙን ያሉት በጭጋግ የሚመሰሉ መከራዎቻችን ፍርሃት ላይ እየጣሉን እንደሚያንዘፈዝፉን ባንገልጽ አይበጅም፡፡ ስለዚህም ውስጣችንን ብርድ ብርድ እያለው መንቀጥቀጡ የዘወትር ተግባራችን እስኪሆን ድረስ ለምን መከራችን እንደከበደ ምክንያቱን ለማወቅ ግራ ተጋብተናል፡፡ “ለምን ፈራችሁ?” ተብለን እንደማንሞገት ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ምክንያቱም በምናያቸውና በምንሰማቸው ብቻ ሳይሆን እየገጠሙን ያሉ እጅግ ውስብስብ ችግሮች ሲበዙብንና ሲበረቱብን ዛሬያችንንም ሆነ ነጋችንን ከመጠራጠር ውጭ ምን አማራጭ ይኖረናል፡፡

አንዳንድ ጥናቶች ከሰው ልጆች፣ ከእንስሳትም ሆነ ከማንኛውም ቁስ የሚወጣው ድምጽ እስከ ምጽዓት ቀን ድረስ በከባቢ አየር ላይ እየተንሳፈፈ (Hovering) ይኖራል እንጂ “ብን ብሎ እንደ ደመና አይጠፋም” በማለት በሳይንሳዊ ግኝታቸው ሲያስገርሙን ባጅተዋል፡፡ የውስብስቡን ሳይንስ ግኝትና ትንተና በአግባቡ ለማሳየት የጸሐፊው እውቀት አናሳ ስለሆነ በእንዴታው ላይ እጅግም ዝርዝር ማብራሪያ ለመስጠት አይዳፈርም፡፡

ሳይንሱ እውነቱን ከሆነና ድምጻችን በኖ የማይጠፋ ከሆነ “የአገራችንን አየር እንደ ጭጋግ የሞላውና የወረረው ድምጽ የበረከት ነው ወይንስ የእርግማን?” ብለን ብንጠይቅ ከመራቀቅ ሊቆጠር፣ ከተስፋ መቁረጥ ጋርም ሊያያዝ አይገባም፡፡ አንደ ማጋነን አይቆጠር እንጂ የአገራችንን ዳመና የሞላውና ከጭጋጉ ጋር ተዳምሮ እንደ ዳፍንት ቁልቁል የተጫነን አንዳች እርግማን ሳይኖርብን እንደማይቀር እንጠረጥራለን፡፡ አየራችን ተበክሏል፡፡ ዳመናችን ጠቁሯል፡፡ እንዴታው ግራ ቢያጋባንም ልንፈወስና ልንፈታ ግን ግድ ይለናል፡፡

ግፈኞች ከፈጸሙት የጦር ሜዳ እልቂትና ውድመት ገና አላገገምንም፡፡ ማገገም ብቻም ሳይሆን ወደፊት ለአገሪቱ የሚተርፈውን መዘዝ ለመተንበይ እየተቸገርን ብንፈራም ሊፈረድብን አይገባም፡፡ በተለየ ሁኔታ ግን ሰሞኑን በግላጭ የምንሰማውና በተግባርም የምንመለከታቸው አንዳንድ ዘግናንኝና ሰቅጣጭ የውንብድናና የዘረፋ ድርጊቶች ከማሳፈርም አልፈው አገርን አንገት ያስደፉ እንደሆኑ ለመረዳት ብዙ ምርምር አይጠይቅም፡፡

በቅርብ ሳምንታት ውስጥ በነዳጅ አቅርቦት ላይ የተፈጸመውን የጎሊና ቢሶች ተግባር “ጉድ! ጉድ! እንደምን የነዳጅ ቦቴ ከነተሳቢው ቁጥቋጦ ውስጥ ለመደበቅ ይሞከራል? ተደብቆስ እስከመቼ ይቆያል? ይደበቅ እንኳን ቢባልስ ከሰው ዓይን መሰወር ይቻል እንደሆን እንጂ እንዴት ከኢትዮጵያ ከራሷ ይሰወራል?” እየተባባልን ስንተክዝና ስንቆዝም መክረማችን አይዘነጋም፡፡

“ክፉ ቀን አያምጣብን እንጂ ቢመጣ ዛሬ ቦቴ ከነተሳቢው የደበቁ ነገ በደበቁት ነዳጅ አገር ለማቃጠል የማያመነቱ ስግብግቦች ምን ያደርጉን ይሆን?” የሚለውን ጥያቄ ገና ጠይቀን መልስ ሳናገኝ ሰሞኑን የተፈጠሩት የከፉ ክስተቶች ይበልጥ በፍርሃት መናጣችንን መሸሽግ አይቻልም፡፡

ለስደተኞች፣ ለተፈናቃዮች፣ ከጦርነት እሳት በተአምር አምልጠው ነፍሳቸው ለተረፈችውና ጊዜ ከድቷቸው የወገኖቻቸውን እርጥባንና የመንግሥትን እጅ ነጋ ጠባ እየተጠባበቁ በመከራ ውስጥ ካሉ ዜጎች አፍ የእርዳታ እህላቸው ተሸጦ በጥቂት ስግብግብ ግለሰቦችና ቡድኖች አገር ስትራቆት መስማት እንኳን ለእኛ ለመከረኞቹ ዜጎች ቀርቶ ለረጂዎቻችንና ለልማት አጋሮቻችን ሳይቀር እንቆቅልሽ እንደሚሆን አይጠረጠርም፡፡

ለካስ አንዳንድ ሰው ልብስ ለብሶ በሰው መሃል የሚመላለሰው “በሰብዓዊነት ክብር” ሳይሆን በአውሬ ፍጥረቱ ነው ብለን እስከ ማመን ደርሰናል፡፡ እኒህን መሰል የሙት ጎሊና ባለቤቶችና የግፍ ብልቃጦች (Lords of poverty እንዲሉ) የከፋትና የጭካኔ ጥግ ስንሰማ ብንፈራ ይፈረድብናል? “አትፍሩ” ተብለን ብንጽናናስ በርግጡ መንፈሳችን ያርፍልናል?

በጋራ ቤቶች እጣ አወጣጥ ላይ የተፈጸመውን “በመዋቅር የተውጠነጠነ ወንብድናና የወንበዴዎች ትራጄዲ” እያየንና እየሰማን ፍርሃት ቢያርደንስ ያስወቅሰናል? የገበያውን እብደት፣ የአገራዊ ኢኮኖሚውን ሕመም፣ በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ከራሳቸውም፣ ከሰዎችም፣ ከፈጣሪም፣ ከማሉለት ሥነ ምግባርም ጋር በተጣሉ አንዳንድ ራስ ወዳድ የፍትሕ ሥርዓቱ ቤትኞች እየተፈጸሙ ያሉትን እርኩሰቶች ስንሰማ ፍርሃት ብቻ ሳይሆን “ኤሌሄ! ኤሎሄ!” እያልን ወደ ፈጣሪ ብንጮኽ “አምላክ አርፎ ይኑርበት አትረብሹት?” ተብለን በሃይማኖት አባቶች ልንወገዝ ይገባል? በጭራሽ ሊታሰብ አይገባም፡፡

ቀስ በቀስ እየተጋለጡ ያሉት በአገርና በሕዝብ ላይ የተፈጸሙት የዛሬዎቹ በደሎች ትናንት ምን ሲሰራ እንደኖረ ፍንጭ ስለሚሰጡ የምንፈራው ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለትናንቱና ለነገውም ጭምር ነው፡፡ ፈራን፣ ተፈራራን፣ አስፈራን እኮ ምን እንበል? ምንስ እንሁን!? ኢትዮጵያ ሆይ እግዜር ያጽናሽ!

## ተናጋሪው ዶሴ

# ታታሪዋን እማወራ ለመግደል ያልሳሳው አባወራ

**ምሕረት ሞገስ**

ታታሪ ናት፤ ደከመኝ ማለትን አታውቅም። በዚህ ጥንካሬዋ የማይወዳት የለም።ገና በልጅነቷ በሰሜን ጎንደር ከቤተሰቦቿ ጋር ስትኖር ከማጀት ወጥታ እየሠራች ቤተሰቧን ለማስተዳደር የምትባዝነዋ ታታሪ ሴት ለትዳር የማይፈልጋት አልነበረም።ከፈላጊዎቿ መካከል ዕድል ቀንቶት ጎሹ አከላት ፈቃድ አገኘ።በደስታ ትዳር መሰረቱ፤ ነገር ግን የሚወዳት ብዙ ነውና ቅናት እያንገበገበው ኑሮን መግፋት ከበዳቸው።

ልጅቷ ታታሪናትና ጥንካሬዋ አቆያቸው።ትዳራችን ከሚበተን ልጅ እንውለድ ብላ አሰበች።ቀናት እና ከአንድም ሁለት ልጆችን ወለዱ።ተፈላጊዋ ልጃገረድ እማወራ ሆነች።ሆኖም ልጆች ወልዳም ጎሹ ቅናቱ አልለቀቀውም።የጎሹ ጭቅጭቅ ስላማረራት አንድ የመፍትሔ ሃሳብ አቀረበች።ቅናቱ እንዲለቀው ‹‹ከሚያውቁን ሰዎች እና ከአካባቢው ብንርቅ ይሻል ይሆናል›› አለች።ወደ ደቡብ ወሎ እንዲሔዱ ጥያቄ አቀረበች።ጎሹ በደስታ ተስማማ።

ወደ ደቡብ ወሎ ሔዱ።እማወራዋ ደቡብ ወሎ ቢሔዱም ንግዷን እያጧጧፈች ተወዳጅነትን አተረፈች።አሁንም ኑሮ ተመሳሳይ ሆነ።እማወራዋ ትታትራለች።ጎሹ በበኩሉ ከሥራ ይልቅ አዕምሮውን የሚያደክመው እርሷን በመከታተል እና በመቅናት መሆኑን ተከትሎ ክፋት እና ተንኮል ልቡን አደነደነው።

ታታሪዋ እማወራ የጎሹ ፀባይ አለመሻሻሉ እያደማት ነው። እርሷ ደክማ እየነገደች በምታመጣው ገንዘብ አንድ እና ሁለት ብቻ ሳይሆን ሶስተኛ ልጅንም ለማሳደግ ተገደደች።በተጨማሪ ደቡብ ወሎ ላይም ኑሯቸው ‹‹ከወንድ ጋር አየሁሽ›› በሚል የጎሹ ጭቅጭቅ እና ንትርክ ትዳራቸው አደጋ ላይ ወደቀ።ትዳር እንዳይበተን ፅኑ ፍላጎት የነበራት ታታሪዋ እማወራ በድጋሚ ትዳሯን ለማዳን ሌላ አካባቢ እንዲሄዱ ወሰነች።ድሬዳዋ ከተማን መኖሪያቸው እንዲያደርጉ ሃሳብ አቀረበች።

### የድሬዳዋ ኑሮ

እንደገና መላ ቤተሰቡ አካባቢ ለመቀየር ተገደደ።ድሬዳዋ ገቡ።ሆኖም የጎሹ ሁኔታ ምንም ለውጥ አላመጣም።ለተወሰነ ጊዜ መልካም ይሆንና መልሶ ይቀያየራል።በቅናት ቤቱን በመበጥበጥ ልጆቹን እና ሚስቱን ያውካል።ከመሥራት ይልቅ በወሬ እና በአሉባልታ በመጠመድ እማወራዋን በገባች በወጣች ቁጥር ይነዘንዛል።እማወራዋ ግን እንደተለመደው የእርሱን ጭቅጭቅ ችላ እየተሯሯጠች እየነገደች ልጆቻቸውን ማሳደግ ቀጠለች።

ድሬዳዋ የተለያዩ ቀበሌዎች እና መንደሮች የተለያዩ ነገሮችን በመነገድ ታዋቂነትን አተረፈች።ከሰዎች ጋር ትግባባለች፤ ትሠራለች፤ ትደክማለች።የያዘችው ደግሞ ይባረክላታል።ባለቤቷ እየበጠበጠ አላስቆም አላስቀምጥ ቢላትም፤ በጤና ውላ መግባቷን አመስግና ለልጆቿ ስትል ሁሉን በመቻል ኑሮዋን ገፋች።

ደከመኝ የማትል ታታሪ እና ጠንካራ በመሆኗ በዛው በድሬዳዋ ከተማ ዜሮ ሁለት ጎሮ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ሶስት ልጆቿን ማሳደግ ለእርሷ እጅግ ከባድ አልነበረም።እማወራዋ ብርድ እና ፀሃይ ሳትል ልባሽ ጨርቅ በመሸጥ ልጆቿን ለማስተማር ብትደክምም አልከፋትም።የጎሹ ቅናት እና ጭቅጭቅ ግን ሰላም እየነሳት ጤናዋን እስከማቃወስ ደረሰ።በዚህ መልኩ ከአቶ ጎሹ ጋር 22 ዓመታት አለፉ።ልጆቹ አደጉ ትልቅየዋ 20 ዓመት ሞላት።

### የትዳር መበተን

አሁን ታታሪዋ እማወራ የአባወራው ጎሹ ጭቅጭቅ አሰልችቷታል።እርሱ በበኩሉ የእርሷ ተወዳጅነት አሁንም ያንገበግበዋል። እንደጎረምሳ እምቡር እምቡር እያለ ‹‹ዘራፍ ለምን ተደፈርኩ?›› በማለት ቤተሰቡን ያምሳል።ቅናት ጭንቅላቱን ስለተቆጣጠረው የሚናገረውን እና የሚያደርገውን አያውቅም። የአካባቢው ሰው እስከሚታዘበው ቤተ ሰቡን ያሰቃያል።

ልጆች የአባታቸው ክፋት ቢያበሳጫቸውም ምንም ማድረግ አልቻሉም።በዝምታ ይታዘቡታል። ሲሰድባቸውከማዳመጥውጪየሚሉትነገርአልነበረም። እናታቸው ለፍታ ባገኘችው ገንዘብ የሚገዛው ቀለብ ለጎሹ በስሎ እና ጣፍጦ ይቀርብለታል።ከእማወራዋ ገንዘብ ነጥቆ ጠጥቶ አምሽቶ ይገባል።ይህን አታድርግ የሚለው የለም።የሚቃወመው ባለመኖሩ በድጋሚ ይበሳጫል።እንደተለመደው እየደነፋ ይሳደባል፤ ካልተደባደብኩ እያለ ሰው ያስቸግራል።እማወራዋ ከእርሱ በተቃራኒው እርሱ ሰነፍ ሲሆን እርሷ ጎበዝ፤ እርሱ ወደ ኋላ ሲል እርሷ ወደ ፊት፤ እርሱ ትዳሩን ለማፍረስ ሲሞክር እርሷ እያባበለች ትዳሯን ለማቃናት በዝምታ ስታልፍ፤ እርሱ ሲቀና እርሷ ስትታገስ ጭራሽ የበታችነት ስሜት እየተሰማው ሌላ ነገር ለመፈፀም ተነሳሳ።



አንድ ነገር አሰበ።2008 ዓ.ም ድሬዳዋ ላይ ክረምቱ አልበረታም።እንደውም አልፎ አልፎ ሙቀት አለ።የድሬዳዋን ሙቀት ትቶ በጨለማው ሃምሌ በክረምቱ ዝናብ አምርሮ በሚዘንብበት ጊዜ ያሰበውን ለመፈፀም ወደ ትውልድ አካባቢው ሰሜን ጎንደር ሔደ።ሚስቱን የሚያስቀናበትን መንገድ አውጠንጥኖ ባሰበው መንገድ በቅናት አሳብዳታለሁ ብሎ ደመደመ።

ለሰዎች የልጆቹን እናት ከፈታ መቆየቱን ነግሮ ሚስት እንዲፈልጉለት አብሮ አደጎቹን ጠየቀ።በክረምት ለማግባት እንደተጣደፈ ጎረምሳ ታታሪዋን ሚስቱን ለማስቀናት ሁለቱም ከሚያውቋቸው ሰዎች የተወለደችውን የአካባቢያቸውን የሰሜን ጎንደር ጉብል በአደባባይ አገባ።ጋብቻውን የፈፀመው በወረሃ ነሐሴ 2008 ዓ.ም ነበር።ዓላማው ሚስቱን ማስቀናት በመሆኑ ብዙም ሳይቆይ ጥቅምት 2009 ዓ.ም አዲስ ሙሽራውን ይዞ ወደ ድሬዳዋ ተመለሰ።

ጎሹ እንዳሰበው አልሆነም።እማወራዋ ትዳሯ መበተኑን፤ ጎሹ አዲስ ሚስት ከሰሜን ጎንደር ማምጣቱን ሰማች።ከመቅናት ይልቅ ‹‹ተገላገልኩ›› ብላ ፈነደቀች።‹‹አንድ አይደለም አስር ሚስት ማግባት ይችላል።የምኖረው በጉልበቴ፤ ልጆቼን የማሳድገው በላቤ ነው ›› አለች።ጎሹ የፈፀመው ድርጊት ምንም አላስከፋትም።ለጎሹ ይሔ ያልተጠበቀ ምላሽ በመሆኑ አለመቅናቷ አበሳጨው።

ብስጭቱ እንደበፊቱ በቅናት እንደሚበሳጭበት ጊዜ ቀለል ያለ አልነበረም።እጅግ በጣም ማሰብ እና መብሰክሰክ ጀመረ።ነገር የሚፈልግበትን መንገድ አስመልክቶ ማውጠንጠን ያዘ።የአሁኑ ትዳር እንደቀደመው ትዳር እንደማይቆይለት ገምቷል። ቀድሞም ያገባው ይዘልቅልኛል ብሎ ሳይሆን ታታሪዋን ቤተሰብ ወዳድዋን ሚስቱን ለማስቀናት አስቦ ነበር።ነገር ግን እንደገመተው አልሆነም፤ ተስፋ ቆረጠ።ዝንጀሮ ገደል አካባቢ ቤት ተከራይቶ ያስቀመጣት አዲሷ ሚስቱ እንደታታሪዋ ሴት የሚበላውን እያቀረበች እንደማትንከባከበው አረጋግጧል።ስለዚህ ወደ ድሮዋ ሚስቱ ለመሔድ ከቤት ወጣ።

### አስከፊው ጥቅምት

የጥቅምት ወር ከጀመረ አስር ቀናት አለፉ።ድሬዳዋ ላይ ለሊት ለሊት እንደሌላው አካባቢ ቅዝቃዜው እና ውርጩ የበረታ ባይሆንም በተወሰነ መልኩ የዛን ቀን ቀዝቃዛ ነበረ።ከጠዋት ጸሀይ ጋር ማልዶ የተከሰተው ውርጭ እስከ ቀትር ዘልቋል።ለወትሮ በወበቅ የምታስጨንቀዋ ድሬዳዋ የዛን ቀን አየሯ የመቀዝቀዝ ዝንባሌ ታይቶበታል።በርካቶች ከድሬዳዋ ሙቀትን እንጂ ቅዝቃዜን የማይፈልጉ በመሆናቸው ብዙዎች ቤታቸው ክትት ብለው ውለዋል።የባሰበት ካልሆነ በቀር ብዙሃኑ ከቤት አልወጣም።

ታታሪዋ እማወራ ግን አልተኛችም።አምላኳን ለምና ፀሎቷን አድርጋ ከቤቷ ማልዳ በመውጣት እንደልማዷ ቀን የምትሸጠውን ልባሽ ጨርቅ በለሊት ተጫርታ ገዝታለች።ሲረፋፍድ ደግሞ ቋጠሮዋን ፈታትታ እና የገዛችውን በየፈርጁ ለይታ የምታነጥፈውን አነጣጥፋ፤ የምትሰቅለውን ሰቃቅላ ንግዷን ጀምራለች።

ጎሹ በበኩሉ በጠዋት ነገር ነገር ብሎቷል።በሰላም ቁርስ ከመብላት ይልቅ ከአዲሷ ሚስቱ ጋር ተነታርኳል።የነገር ዛሩን ከአዲሷ ሚስቱ ጋር አረፋፍዶ ካሟሟቀ በኋላ ወደ ታታሪዋ የቀድሞ ሚስቱ አመራ።ከሩቅ አያት።እንደለመደው ቀጥታ ወደ ስድብ አልገባም።ሲጠጋት እርሷ ልብ አላለችውም።ወደ እርሷ ወደምትሰራበት መደብ ተጠግቶ መቆፈሪያ እና ሸራ እንዲሁም ማዳበሪያ እንድትሰጠው ጠየቃት።

የተገላገለችው ጎሹ ንግድ ቦታዋ ላይ መምጣቱ አበሳጭቷታል።የሚፈልገው ዕቃ እርሷ ጋር እንደሌለ ስትገልፅ፤ ጎሹ እንደለመደው ሰበብ አግኝቶ መሳደብ ጀመረ።ከመሳደብ አልፎ ለማዋረድ ሲል አስከፊ ቃላትን ያዥጎደጉደው ጀመር።ምስኪኗ እማወራ መልስ አልሰጠችውም።ይበልጥ ተበሳጨ እርሱ መጥፎ ነገር ሲያደርግ እርሷ ምላሽ አለመስጠቷ ሁልጊዜም እጅግ ያበሳጨዋል።ስድቡን ሲጨርስ ራቅ ብሎ ተቀመጠ።በኋላ ተመልሶ ከገበያው ወጣ።

በጎሹ ድርጊት የተማረረችዋ እማወራ ቀኑን እንደነገሩ አሳልፋ ወደ ቤቷ ለመሔድ ተሰነዳዳች።ጎሹ ተመልሶ መጥቶ ነበር። እርሷ ግን አላየችውም።ምሽቱ እየቀረበ በመሆኑ ትኩረቷን ዕቃዋን በሥርዓት ማስቀመጥ ላይ አድርጋለች።ጎሹ በበኩሉ ድርጊቷን በሙሉ እየተከታተለ ነበር። ወደ ቤቷ ስትሔድ እንዳ ታየው እየተጠነቀቀ ተከተላት። ቤት ስትገባ ተከትሏት ገባ።

በቤት ውስጥ የ20 ዓመቷ የመጀመሪያ ልጃቸው ምግብ አብስላ የእናቷን መምጣት በጉጉት እየተጠባበቀች ነበር።አባቷ ከእናቷ ኋላ ተከትሎ መግባቱ ክፉኛ አስደነገጣት።እማወራዋም ጎሹን ስታይ ፈራችው።ሚስቱን እና የልጆቹን እናት ለመጉዳት ሆነ ብሎ የተዘጋጀው ጎሹ የያዘውን ቢላዋ ሰነዘረ።እጇን ወጋት፤ ለመታገል ስትሞክር በድጋሚ እጇን ወጋት።ከቤት ውስጥ ወጥታ ለማምለጥ ሮጠች ሆኖም የበሩ ደፍ አደናቀፋትና በደረቷ ወደቀች።ጎሹ ተከተለ። ልጃቸው ራሷን መቆጣጠር አቃታት።ኡኡታዋን አቀለ ጠችው።

ጎሹ እማወራዋ እንደወደቀች እላይዋ ላይ ተከመረ።የልጅቷን የድረሱልኝ ከፍተኛ ጩኸት የሰሙ ጎረቤቶች ብቻ ሳይሆኑ በቅርብ የነበሩ ፖሊሶችም ወደ ቤቱ ተንደረደሩ።ሆኖም መድረስ አልቻሉም።ጎሹ ጊዜ አላባከነም በፍጥነት የእማወራዋን ጭንቅላቷን ጎትቶ እንደዶሮ አረዳት።ይህንን ድርጊት ሲፈፅም ፖሊስ አየ።የቅርብ ጎረቤትም ተመለከተ።ሁሉም ተጯጯኸ፤ ሰፈርተኛ ተሰበሰበ፡፡

የታታሪዋ እማወራ ደም በወፍራሙ በቤቱ ደጃፍ ተንጣለለ።አይኗ አይታይም፤ ግንባሯ ከመሬቱ ጋር ተገናኝቷል፤ በደረቷ ተደፍታለች።ልጇ ራሷን መቆጣጠር አቅቷት ተጠግታ እናቷን ለመንካት ፈርታ ጩኸቷን ታቀልጠዋለች። መሬት ላይ ትንከባለላለች። ሰዎች የተፈፀመው ድርጊት ዘግንኗቸዋል። ግማሹ ይንቀጠቀጣል፤ ግማሹ እንባው ይወርዳል። ቀናተኛው ጎሹ፤ አማራጭ የሌለው ጎሹ እጅ ከፍንጅ ተይዟልና እጁን ሰጠ፡፡

### የፖሊስ ምርመራ

የወንጀል ድርጊቱ ሲፈፀም በስፍራው የተገኘው ፖሊስ የሟቾችን አስከሬን አነሳ።ተገቢውን ምርመራ አጠናቆ ለጥያቄ የሚሻቸውን ምስክሮች ለየ።ምስክሮቹ በተደጋጋሚ እየቀና አምባጓሮ ሲፈጥር እንደነበር፤ ክረምት ላይ በቤት እንዳልነበር እና ድርጊቱን በፈፀመበት ማለትም ጥቅምት 10 ቀን 2009 ዓ.ም ጎሹ የታታሪዋ እማወራ የሥራ ቦታ ተገኝቶ ሲሰድባት እንደነበር ገለፁ።አመሻሽ ላይ ከፍተኛ የድረሱልን ጩኸት ሲሰሙ ወደ ቤት መጠጋታቸውን ሆኖም ደጃፍ ላይ ሟችን ጎሹ በቢላዋ ሲያርዳት ማየታቸውን እና በመጨረሻ በግንባሯ ደም ላይ ተደፍታ ፖሊስ አስከሬኑን ማንሳቱን መሰከሩ።

ፖሊስ የሰው ምስክር ብቻ ሳይሆን የህክምና ማስረጃ አቀረበ።በተጨማሪ እጅ ከፍንጅ ድርጊቱን ሲፈፅም የተያዘ መሆኑን በመጥቀስ ክሱን ለፌዴራል ፍርድ ቤት አሟልቶ አቀረበ፡፡

### ውሳኔ

ታህሳስ 11 ቀን 2009 ዓ.ም በችሎቱ የተሰየመው የድሬዳዋው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሳሽ ጎሹ አከላት ላይ የተከፈተውን ክስ ለማየት ተሰየመ። ዕለቱ ለመጨረሻ ውሳኔ ቀጠሮ የተሰጠበት ቀን ነበር፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በፈጸመው ዘግናኝ የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ እንዲከላከል ዕድል ሰጥቷል፡፡ ተከሳሹ ለፈጸመው ወንጀል መከላከያ እንደሌለው አሳውቋል፡፡ ፍርድ ቤቱ በዕለቱ በሰጠው ውሳኔ ጎሹ አከላት የልጆቹን እናት የሰው ልጅ ላይ ሊፈፀም የማይገባ እጅግ በጣም ዘግናኝ አገዳደል የፈፀመባት በመሆኑ እና አገዳደሉም የግለሰቡን ጭካኔ ስለሚያሳይ ለሌሎችም ትምህርት ይሆናል ብሎ በማሰብ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 149 መሠረት በ20 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወሰነ፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የክረምት ትጋት ለበጋ እረፍትና ሐሴት

**ይቤ ከደጃች.ውቤ**

ያለንበት ወቅት የክረምት መባቻ ነው። ለገበሬው የመከራ ጊዜ ቢሆንም እየከበደውም ቢሆን የሚናፍቀው ወቅት ነው። ለከተሜዎች ግን ዝናባማና ብርዳማ ወቅት ስለሆነ መጣብን እንጂ መጣልን የሚሉት አይደለም። ወቅቱን የሚጠሉትን እንጂ የሚናፍቁት ባለመሆኑ በከተሜዎች ክረምት ብዙም አይወደድም። እንደውም በገጠር ፍየልና ከተሜ ክረምት ይፈራሉ ተብሎ ይነገራል። ክረምት የዝናብ፣ የሣር፣ የዘር፣ የአረም ወቅት፤ በአገራችን ከፍተኛው የግብርና ተግባር የሚከናወንበት ነው።

ክረምት ከሌለ የቀረውን የዓመቱ ወራት የመከራ ወራት ስለሚሆንበት፤ የመከራ ጊዜውን ብርድና ዝናቡ እየወረዱበት ገበሬው እያረሰና እየዘራ ቀሪዎቹን ዘጠኝ ወራት በፍስሐ በደስታ ያሳልፍበታል። የሦስቱን የክረምት ወራት በእንዝህላልነት የሚያሳልፍ ሰነፍ ገበሬ ቀሪውን ዘጠኝ ወራት መንከራተት ይጠብቀዋል። ድህነትና ስደት የመሳሰሉ መከራዎች ከፊቱ ይጋረጡበታል።

መጽሐፍ ቅዱስም ‹‹በለቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ›› እንደሚለው ሁሉ ገበሬውና ቤተሰቡ ክረምቱን ከንጋት እስከ ምሽት ብርዱ እየመታቸው ዝናብ እየወረደባቸው አልፎ አልፎም በረዶ እየቀጠቀጣቸው እያረሱ ዘራቸውን እየዘሩ ይውሉበታል። እናም የክረምቱን ብርዳማ ዝናባማ ነጭናጫ ወራት፤ ካላረሱበት ካልዘሩበት ድርቅና ልመና ያንጋጥጡበታል፤ ስደትና የመከራ ወቅት ይጠብቁታል። ተረቱም ‹‹ለሞኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ›› ይለዋል።

የሰኔ ወር እንደ ክረምት መለማመጃ ተደርጎ ይቆጠራል፤ ዋናው ክረምት ገባ የሚባለው ሰኔ 25 ቀን ነው። ለዚህም ነው ትምህርት በሰኔ 30 ማጠናቀቂያ የሚሆነው። ነፍስ ሔር ደራሲና ጋዜጠኛ ካህሳይ ገብረ እግዚአብሔር በኅብረ ብዕር መጽሐፋቸው እንደጠቀሱት ክረምት ሐምሌ፣ ነሐሴ፣ የጳጉሜና የመስከረም ወራቶች ናቸው። የደስታ ተክለወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላትም ክረምት የሚለውን ቃል ሲፈታው ሦስት የዝናብ ወር፤ ከሰኔ 25 እስከ መስከረም 26 የሚቆጠር ይለዋል። የዓመቱ አራት ወቅቶች ክረምትን ጨምሮ መጪው፣ በጋ እና ጸደይ ተብለው ይከፈላሉ። ክረምቱ 95 ቀናት ሲኖሩት ሦስቱ ቀሪዎቹ ወቅቶች ዘጠና አንድ፣ ዘጠና አንድ ቀናት አላቸው።

በተለይ ገጠራማ አካባቢዎች ክረምት ሰው በእርሻ የሚሠማራበትና ዘሩን የሚዘራበት ወቅት ስለሆነ ዘመድ ወዳጅ ለመጠየቅ ጊዜ አይኖርም። ጊዜ ቢኖርም እንኳ ወንዞች ስለሚሞሉ መሻገር አይቻልም። ወንዞች ባይሞሉም እንኳ ከሌላ አካባቢ የዘነበ ዝናብ ደርሶ ወንዙን እየተሻገሩ ሳለ ፈረሰኛ የሚባለው ወንዝ መጥቶ ሊወስዳቸው ይችላል። ጭቃውም በየዕለቱ የሚዘንበው ዝናብም ዘመድ ለመጠየቅም አዳጋች ነው።

ክረምት ለሰው፣ ለእንስሳቱ፣ ለእጽዋቱ ብሎም ለአዝዕርቱ የቀጣይ ሕልውና መጣያ ወቅት ነው። እንዲህም ሆኖ ብዙዎች ግን ወቅቱን በጨለማና በመከራ ይመስሉታል። ይህም በገበሬው ዘንድ በክረምት ጎተራው ባዶ የሚሆንበት፣ ሌማቱ (ማዕዱ) የሚጎድልበት የችግር ግዜ በመሆኑና በረዶው፣ ብርዱ፣ ዝናቡ፣ ውሽንፍሩ፣ ጎርፉ በሰውና በእንስሳ ብሎም በምድሪቱ ጉዳት የሚያደርሱበት ነው። የዐፄ ቴዎድሮስ ጸሐፊ የነበሩት አለቃ ዘነብ ‹‹ክረምት ሲመጣ ከሞት እንዲከብድ ጠላትም ሲመጣ እንደዚያ ይከብዳል›› ይላሉ።

የክረምት ስም ገንኖና ገዝፎ የሚታየው በሐምሌ ወር ነው። ሐምሌ የክረምት ንጉሥ ነው የሚሉ አሉ። የምድሪቱ ልምላሜ የሚታየው በሐምሌ ወራት ነው። ሐምሌ እንደ ንጉሥ አጃቢው ብዙ ነው፤ ጉሙ፣ ጭጋጉ፣ ደመናው፣ ዝናቡ፣ ጎርፉ፣ ውሽንፍሩ አውሎ ንፋሱና በረዶው ሁሉ ነው። ሲያሻውም ሰማይን ሰንጥቆ መሬትን ነቅንቆ ፍጡራንን አስደንግጦ፣ አስጨንቆና አስበርግጎ የመብረቅ ነጎድጓድ ወርዶ የፈለገውን ይመታል።

የአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሐምሌን ሲፈታው የወር ስም ባለ ቅጠል፣ ቅጠል ያለው የልምላሜ ወር ማለት ነው ይለዋል። እንደፍቺው ከሔድን ሐመልማል የሚለው ቃልም ከልምላሜ ጋር የተዛመደ ስለሆነ ከሐምሌ የወጣ ሊሆን ይችላል። በትግርኛ ሐምሊ የሚለው ቃል ጎመን ማለት መሆኑም የልምላሜ ማሳያ ነው። ጎመን የሚበላውም በዚሁ ወቅት ነው፤ ሐምሌ ከወራት በደፋርና በጀግና ይመሰላል። በአጃቢ ገብቶ በአጃቢ የሚወጣ ስለሆነ አንዳንዶች በክረምት አይናውጣ ይመስሉታል። እየፎከረ እያቅራራ መጥቶ እየሸለለ እየዘመረ የሚመለስ ዓዘ ብዙ ወር ነው።

ጀግና ጀግናን ያፈቅራል ደፋር ደፋርን ይወልዳል፤ በሐምሌ ዝናብ ረሀቡም ያይላል፤ ወሩ ቢከብድም ገበሬው ይወደዋል። አንዳንዶቹ የሐምሌ ወር በራሱ ገበሬውን ስለሚወደው ይፈትነዋል፣ ይገራዋል ይላሉ። ለገበሬው ውጤት፣ ፍሬ፤ በሥራ እንጂ በወሬ እንደማይገኝ ያስተምረዋል። የሚሰጠው ትምህርትም እንደወታደራዊ ሥልጠና በተግባር የታጀበ ነው። ወራቱን ለእንስሳም ይከብዳሉ፤ አይጥ፣ ከአውላላ ሜዳ ሰዎች ቤት ገብታ የምትሸሸግበት ነው። ለእባብም ይከብደዋል። ውሃ ባይገለውም መርዙን ቢረጭ በውሃ ምክንያት ስለማይጎዳ ትጥቅ እንደሌለው ወታደር የሚሆንበት ነው። እንደውም በክረምት እባብና እንቁራሪት በአንድ ኩሬ ያሳልፋሉ ይባላል። ለዓሣዎችም በወንዞች ማዕበል የሚወሰዱበት ስለሆነ ይከብዳቸዋል። ዕድለኞቹ ዓሣዎች ግን በውሃ ውስጥ ባሉ ትልልቅ ድንጋዮች ውስጥ ተሸሽገው ያሳልፉታል። መጽሐፍ ቅዱስ ወቅቱን ‹‹ ዘይገለብቦ ለሰማይ በደመና ወያተስዴሉ ክረምት ለምድር ዘያበቁል ሣዕረ ውስተ አድባር ›› በዳዊት መዝሙር 146፡8 ሲል ይገልጸዋል። ፍቺውም ሰማዩን በደመናት ይሸፈናል፤ ለምድርም ዝናብን ያዘጋጃል ሣርን በተራሮች ላይ ያበቅላል። ገበሬዎች በግጥምም ሲያንጎራጉሩ፡-

**ሐምሌ ወንዱ መጣ ሁለት ወር ክረምት**
**ለጎኔ መኝታ ሳልፈልግለት**
**ሐምሌ ወንዱ መጣ ጎመን ደረደረ**
**የወር ቀለብ የለኝ ቤቴ አልተከደነ**
**ሾረ ተወኝ ሐምሌ ጉምህን አትደርድር**
**ቀለቤን ልሸምት ቤቴንም ሳስከድን**

እረኛውም ጅራፉን እያስጮኸ እንዲህ ሲል ይዘፍናል።

**ክረምቱ ክረምቱ**
**የገበሬው ሞቱ**
**የባልቴት ወዘቱ (ወዘና?)**
**የቀንጆ ማጀቱ**
**የእረኛ ወተቱ**

እረኛው የገበሬው ሞቱ ሲል ከፍተኛ ውጣ ውረድና ሥራ እንዳለበት ለማመልከት ነው። የእረኛ ወተቱ ሲልም በሰኔና በሐምሌ በብዛት ላሞች የሚወልዱበት ለእረኛው ከሌላው ወቅት የተሻለ መሆኑን ለማመልከት ነው። በክረምት እረኛ ሲሰማራ እሪጦ ማለትም በኑግ ወይም በተልባ የታሸ አነባበሮ ወይም ቂጣ በትኩሱ በልቶ ይሰማራል። ገሳውን ለብሶ (ዝናብ መከላከያ) ከብቶቹን ሲያሰማራ የሐምሌን ብርድ ይንቀዋል። በአጠቃላይ የክረምት ትጋት የበጋ እረፈትና ሐሴት ነው። በዚህም ገበሬዎችም ተግተው አርሰውና ዘርተው ለከተሜዎች ጭምር እረፍትና ሐሴትን ይፈጥራሉ።

# ዓለም አቀፍ

## የኬንያ መንግሥት የነዳጅ ዋጋን ለማረጋጋት 140 ሚሊዮን ዶላር መደበ

ዓለም አቀፉ ገበያ የነዳጅ ዋጋ ቢጨምርም በኬንያ ያለውን የነዳጅ ዋጋ ባለበት እንዲቀጥል የአገሪቱ መንግሥት አዲስ የነዳጅ ድጎማ አደረገ።

ይህም ኬንያውያን በሌሎች መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች ላይ ካጋጠማቸው የዋጋ ጭማሪ በተጨማሪ ከሌላ የዋጋ ንረት ጋር ትግል ውስጥ እንዳይገቡ ያደርጋል ተብሏል። መንግሥት ከወርሃዊ የዋጋ ማሻሻያ በፊት በነዳጅ ላይ ያደርግ የነበረውን ድጎማ ሊያነሳ እንደሚችል ፍንጭ ሰጥቶ ነበር።

ይሁን እንጂ የአገሪቱ መንግሥት የውሳኔ ለውጥ በማድረግ አሁን ያለውን የነዳጅ የችርቻሮ ዋጋ ለተጨማሪ 30 ቀናት ባለበት እንዲቀጥል የ141 ሚሊዮን ዶላር ድጎማ አድርጓል። በሰኔ ወር የአገሪቱ ባለስልጣናት አሁን እየተደረገ ያለው የነዳጅ ድጎማ ‘’ዘላቂነት የሌለው ነው’’ ሲሉ አስተያየት ሰጥተው ነበር።

ባለፈው ዓመት ኬንያ በዓለም ገበያ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ መከሰቱን ተከትሎ ለነዳጅ ድጎማ ከ860 ሚሊየን ዶላር በላይ ወጪ አድርጋለች። የኢትዮጵያ ጎረቤት ምሥራቅ አፍሪካዊቷ አገር ኬንያ በቀጠናው ካሉ አገራት ነዳጅ በውድ የምታቀርብ አገር ነች። ድጎማው ባይኖር ኖሮ በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ አንድ ሊትር ቤንዚን 1.80 ዶላር ይደርስ ነበር። አሁን ላይ ዋጋው 1.34 ዶላር ነው።




ከኬንያ በመከተል በአካባቢው በከፍተኛ ዋጋ ነዳጅ የሚገዛባቸው አገራት ሱዳን እና ኡጋንዳ ሲሆኑ፤ ነዳጅ የምታመርተው ሱዳን ለአንድ ሊትር 1.50 ዶላር ስታስከፍል፣ በቅርቡ የነዳጅ ዘይት ያገኘችው ኡጋንዳ ደግሞ አንድ ሊትር በ1.6 የአሜሪካ ዶላር ታቀርባለች።

በአፍሪካ ነዳጅ በከፍተኛ ዋጋ ከሚሸጡባቸው አገራት መካከል ደቡብ አፍሪካ ተጠቃሽ ናት። በመረጃው መሠረት በደቡብ አፍሪካ አንድ ሊትር ነዳጅ የሚሸጠው በ1.48 ዶላር ነው። በዓለም ላይ ዜጎቿን አነስተኛ የነዳጅ ዋጋ የምታስከፍለው ነዳጅ አምራች የሆነችው እና ምጣኔ ሀብቷ ክፉኛ የተጎሳቆለባት ቬንዙዌላ ነች።

እንደ ግሎባል ፔትሮል ፕራይስ ከሆነ በቬንዙዌላ በ1 የኢትዮጵያ ብር (0.02 የአሜሪካ ዶላር) አንድ ሊትር ነዳጅ መሸመት እንደሚቻል ቢቢሲ ዘግቧል።

## ለዓመታት የታሰረው ግለሰብ 40 ሚሊዮን ዶላር ካሳ ጠየቀ


ሰብዓዊ መብት ተሟጋቹን ማልኮም ኤክስን ገድለሃል ተብሎ በስህተት ጥፋተኛ ተብሎ 20 ዓመታትን በእስር ያሳለፈው ሙሃመድ አዚዝ ኒው ዮርክ ከተማ 40 ሚሊዮን ዶላር እንዲከሰው ጠየቀ።

ሙሃመድ አዚዝ የማልኮም ኤክስን ግድያ ተከትሎ ከታሰረ ከ20 ዓመታት በኋላ ከእስር የተለቀቀው በ1985 ነበር። በ2021 ዐቃቤ ሕግ አዲስ ማስረጃ አግኝቻለሁ በሚል ሙሃመድ አዚዝ ወንጀሉን አልፈጸመም ብሏል። የቀድሞ የባሕር ኃይል አባሉ ሙሃመድ አዚዝ በ1965 ሲታሰሩ የ6 ልጆች አባት እና የ26 ዓመት ወጣት ነበሩ።

የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ ማልኮም ኤክስ የአደባባይ ንግግር ለማድረግ ዝግጅት ላይ እያለ በታጠቁ ሦስት ሰዎች በጥይት ተደብድቦ ነበር የተገደለው። በወቅቱ በግድያው ተጠርጥሮ ሙሃመድ አዚዝ ከካህሊል ኢስላም ጋር ነበር የታሰረው። 22 ዓመታትን በእስራት ያሳለፈው ኢስላም በ2009 ሕይወቱ አልፏል። ዐቃቤ ሕግ ተጨባጭ ማስረጃ ሳያቀርብ፤ የሚጣረስ ሃሳብ የሰጡ ምስክሮችን አሰምቶ በሁለቱ ግለሰቦች ላይ ብይን ያሰጠው።

ግድያው በተፈጸመበት ቦታ በቁጥጥር ሥር የዋለው እና ማልኮም ኤክስን መግደሉን ያመነው ታለማደግ ሃዬር፤ በሁለቱ ግለሰቦች የፍርድ ሂደት ላይ ቀርቦ በወንጀሉ እጃቸው የለበትም ሲል ምስክርነቱን ሰጥቶ ነበር። በ1970ዎቹ ደግሞ በግድያው ሌሎች አራት ሰዎች መሳተፋቸውን ሃየር የጽሑፍ ቃለ መሃላ ፈጽሟል።

በ2020 የእነ ሙሃመድ ጉዳይ ተጣርቶ ንጽህናቸው እንዲረጋገጥ ክሱን እንደገና ማየት ተጀምሮ ነበር። የሁለቱን ተጠርጣሪዎች ጥብቅና የያዘው ዴቪድ ሻኒስ፣ በመንግሥት ግዴለሽ አሰራር ምክንያት ሁለቱ ሰዎች በስሕተት 42 ዓመታትን እስር ቤት እንዲያሳልፉ ተደርገዋል ብሏል።



“የዘገየ ፍርድ እንደተነፈገ ይቆጠራል። ሙሃመድ አዚዝ 84 ዓመታቸው ነው። ኢስላም ደግሞ እንዳለመታደል ሆኖ ንጽህናቸው ሳይረጋገጥ ሕይወታቸው አልፏል” ብሏል ጠበቃው ዴቪድ። ባለፈው ዓመት የማልኮም ኤክስ ልጅ የአባቴ ጉዳይ እንደገና ይታይልኝ በማለት አመልክታ ነበር።

የማልኮም ኤክስ ሴት ልጅ በግድያው ወቅት ፖሊስ የነበረ ሰው ጽፎ አስቀምጦታል ያለችውን ደብዳቤ በመጥቀስ ግድያውን ያቀነባበሩት ኤፍቢአይ እና የኒው ዮርክ ፖሊስ ናቸው ብላለች። እነዚህ ማስረጃዎች ተደማምረው 20 ዓመታትን በእስር ያሳላፉት የ84 ዓመቱ ሙሃመድ አዚዝን በኒው ዮርክ ከተማ ላይ ክስ እንዲመሰርቱ አድርጓቸዋል። ያላአግባብ እና በመንግሥት ግዴለሽ አሰራር ምክንያት ለታሰሩበት ለሁለት አስርት ዓመታትም 40 ሚሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

## የጊዜ ቀለበት

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**



ሰርጋቸውን በቅርቡ ሊያደርጉ እቅድ ያደረጉ ጥንዶች ቀለበት ሊገዙ ከወርቅ ቤቶች በር ላይ ናቸው። አንዱን ቤት አይተው ወደ ሌላኛው፤ ከዚያም ወደ ሌላኛው እያሉ እያማረጡ። የሚገዛው ቀለበት አይነትና የገንዘብ አቅማቸውን ለማስታረቅ ያወጣሉ ያወርዳሉ ደጋግመው ያሰላስላሉ። በመጨረሻም ከውሳኔ ደርሰው ቀለበታቸው ገዙ። ተቻጋግረው የገዙትን ቀለበት ይዘው በታክሲ ተሳፍረው ከሙሽሪት ሰፈር ደረሱ። ሁለቱም ወደ የራሳቸው ቤት ከመግባታቸው በፊት ሻይ ቡና እያሉ መቆየት ፈልገው ወደ አንድ ካፍቴሪያ ጎራ አሉ። እንደተለመደው ፍቅሬ አካላቴ ወዘተ ሲባባሉ ቆይተው ወደየቤታቸው አቀኑ። ቀኑ መሸ፤ የቀለበት መግዢያው ቀንም ያለፈ ሆነ።

ሁለቱም ቤታቸው ሲደርሱ ግን የገዙት ቀለበት እነርሱ ዘንድ አልነበረም። ተደዋወሉ፤ አንተ ጋር ነው፤ አንቺ ጋር ነውም ተባባሉ፤ ከቀልባቸው ሆነው ሲያስቡት ለካንስ ቀለበቱን ታክሲው ውስጥ ጥለውት ወርደዋል። በድንጋጤ ውስጥ ወደቁ፤ በብዙ የገንዘብ እጥረት የገዙት ቀለበት ነበርና ሃዘናቸውን አከፋው። ታክሲውን ለማስታወስ ሞከሩ፤ በጨለማም ወጥተው ይፈልጉትም ጀመር፤ ፍለጋውም ሳይሳካ ቀረ ቀለበቱም መጥፋቱን አምነው ተቀበሉ። ሙሽሪት ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ አባት ይመለከቱና የነገሩን ጭራ ለማግኘት ወደ ልጃቸው ጠጋ ይላሉ። ልጃቸውም ሁሉንም ነገር ለአባቷ ትናገራለች፤ አባትም የአባትነት ምክር ሊነግሯት ወደዱና፤ "ልጄ የወርቁ ቀለበት ከአንቺ ዘንድ የለም፤ ነገር ግን የጊዜ ቀለበት አንቺ ጋር አለ። የጊዜ ቀለበት ደግሞ የወርቁን ቀለበት ይገዛዋል።" ሲሉ ምክራቸውን ሰጡ።

አባት በመቀጠልም፤ "ልጄ በጊዜ ቀለበት ውስጥ የሚዘራው መልካም ዘር አለ፤ እንዲሁም ያልተገባውም። በጊዜ ውስጥ ሁሉ ነገር ይዘራል። ጊዜን ገንዘብ ለመስሪያ ማዋል ይቻላል፤ ጊዜን ችግርን ለመፍቻ መጠቀም ይቻላል፤ ጊዜን የተራቡትን ለማብላት ይጠቅማል፤ ጊዜን የተጣሉትን ለማስታረቅ፤ ጊዜን ትምህርት ለመማር፤ ጊዜን የጠፉን ለመፈለግ፤ ጊዜን ከራስ ጋር በጥሞና ለመሆን፤ ጊዜን ትላንትን መርምሮ ትምህርትን ለመውሰድ፤ ጊዜን ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ ያሰቡትን ለማድረግ፤ ...፤" ወዘተ ብለው የጊዜ ቀለበትን አስረዱ።

እኛም እንላለን በጊዜ ቀለበት ውስጥ መልካምን በመዝራት መልካምን ማጨድ ይቻላል። በጊዜ ውስጥ ክፉን በመዝራት ክፉን ማጨድ ይቻላል። ለነገሮች የደረሰውን ጊዜ አውቆ ነገሮችን በጊዜ ማድረግ አስተውሎትም ነው። ይህን አስተውሎት ማግኘት ይቻል ዘንድ ጠቢብ ሰው በብዙ ይደክማል።

ጊዜን በአግባቡ የሚመረምሩ በዘመናት መካከል ከጊዜ ጋር የታረቀን ተግባር አድርገው ማለፍ ይችላሉ። በዓለማችን ውስጥ በታሪክ መዝገብ ውስጥ ስማቸውን በደማቁ ጽፈው ያለፉ ጀግኖች የጊዜን ቀለበት በአግባቡ የያዙ ናቸው። ከወርቅም ሆነ ከእንቁ ቀለበት በላይ ለጊዜ ቀለበት ቦታን የሰጡ። የጊዜ ቀለበት ራሳችን ለራሳችን የምናጠልቀው ታላቁ ኪዳን ነው፤ ራስን ፈልጎ ራስን በትክክለኛው አቅጣጫ ውስጥ በጊዜ ውስጥ የማራመድ ኪዳን። የእርምጃው መነሻ ደግሞ፤ አንድ!

### መነሻው አንድ ነው

የጊዜ ቀለበት መነሻው ሁለት አይደለም፤ አንድ ነው። መነሻው አመታት አይደለም ሽርፍራፊ ሰከንድ ነው። አንድ ብለን መቁጠር ጀመርን። አንድ ብለን መቁጠር ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ ወደ ኋላ በምናብ ብንሄድ ወራቱና ቀናቱ ትዝታ ሆነው ከኋላችን ናቸው። የዘመናችንን ታሪክ ለመስራት የተገለጡ አዳዲስ ቀናት ደግሞ ከፊታችን። በውስጣዊ ሰውነት በአዲስነት ለሚቀበለው ትርጉም የሚሰጥ። የለውጥ መንገድን የራሱ ላደረገ ሰው ትርጉም የሚሰጥ የጊዜ ቀለበት።

በዘመን መለወጫ ወቅቶች በአመቱ ውስጥ ሽልማት የተገባቸውን ለይቶ እውቅና የመስጠት ባህል እየተለመደ ያለ ባህል ሆኗል። በዘርፉ ላይ ጎላ ብለው የወጡና አስተዋጽኦ ያደረጉትን መርጦ የመሸለም ተግባር በአገራችንም በመላው ዓለምም የተለመደ ተግባር ነው። ሰዎች በአደባባይ የሚሸልሟቸው ወደ ደረጃው ከመውጣታቸው በፊት ራሳቸውን የሸለሙ መሆናቸውን አስበን እናውቅ ይሆን? ለራሳችን ከራሳችን በላይ የሚቀርብ ስለሌለ ራሳችንን ለመሸለም ማንም ሊቀድመን አይገባንም ብሎ የሚያምን ሰው የሚያደርገው። ለራስ ትርጉም በመስጠት የሕይወት ቅኝት ውስጥ የሚመዘዝ ሰበዝ።

አዲስ አመትን ለማብሰር የሰፈሩ ልጃገረዶች አበባይሆሽ ይላሉ። በየቤቱ ደጃፍ ሄደው እየቆሙ ዜማቸውን አሰምተው የሚሰጣቸውን እየተቀበሉ ከአንድ ቤት ወደ ሌላ ቤት የሚደረግ፤ ሁሌ የማይደረግ በልጅነት ወራት በጊዜ ቀለበት ውስጥ የሚሆን። ለልጃገረዶቹ ቤት ያፈራው ሲቀርብ እነርሱም በዜማ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ። በጊዜ ቀለበት ውስጥ ከአንድ ምእራፍ ወደ ሌላኛው ምእራፍ ለመሸጋገር ቆሞ ማመስገን የተገባ ነው።

### በምሥጋና ከአንድ ምዕራፍ ወደ ሌላ

ለምዱብን በአንደበታችን አመሰግናለሁ ከማለት ባሻገር በጊዜ ቀለበት ውስጥ ትላንትን ስንመለከት አስቀድመን ምስጋናን ብንከፍት እጅግ የተሻለ ነው። በአገራችን የትላንት ታሪክ ውስጥ ወቀሳ ይቀድመናል። እከሌ እንዲህ ሆኖ፤ እከሌ እንዲህ አድርጎ ወዘተ እንላለን። ትላንት ላንቀይረው እንዳለፈ ውሃ ነውና ለነገ ትምህርት የሚወሰድበት እንዲሆን በአመስጋኝነት ገጾቹን መመልከት በብዙ ይመከራል።

የምስጋና ባህል አዎንታዊ መንፈስን በመፍጠር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። በእኛ በኢትዮጵያን ዘንድ የምሥጋና ባህላችን ጠንካራ የሚባል አይደለም። በአጠገባችን ምሥጋና የሚገባቸው የበረከቱ ሰዎች ኖረው እንኳን አጠገባችን ሳሉ መመልከት ሳንችል ቀርተን እለተ ሞታቸውን እንጠብቃለን። አንዳችን በአንዳችን ሕይወት ውስጥ ያለን ቦታ ትርጉሙ ትልቅ ነው። ዛሬ ላይ የሆንበትን ቦታ ተመልክተን ወደኋላ ስንመለከት በሕይወታችን ውስጥ ትርጉም ያለው ተጽዕኖቻቸውን ያሳደሩ መልካም ሰዎችን እናገኛለን።

መልካም ሰዎችን ለማመስገን የሚደፍር ባህል መልካም ሰዎች እንዲበዙ የሚያደርግ ነው። መልካም ሰዎችም የጊዜ ቀለበት ውጤቶች ናቸው። የተዘራው ዘር ለሌላ ለሚዘራ ዘር እንዲሁ የሚቀርብ መሆኑን መረዳትም ይገባናል። አስተውለን ማየት ከቻልን መልካም ሰዎች በዙሪያችን አሉ። መልካም ሰዎች ግን መልካምነታቸውን ማየት የሚቻለው የተከፈተ አይን ስናይ ብቻ ነው።

የለቅሶ ስርዓታችን የሚወስደው ቀንና በለቅሶ ጊዜ የምናወጣው ጥልቅ ሃዘን ምንጩ የሟች መልካምነት ትውስታ ሆኖ ይታያል። ሟችን በጊዜ ቀለበት፤ ነዋሪውም እንዲሁ። አንዳችን በአንዳችን ውስጥ ያለን ቦታ የጨመረ በሆነ ቁጥር የለቅሶ ቀን ትርጉሙ ሌላ ነው። ለአንዳንዱ ለቅሶ መድረስ የሆነውን ግቡን ለመምታት ወደ ለቅሶ ቤት ይሄዳል። ሌላው ከልቡ አዝኖ ሲያጽናናም ይገኛል። ለሃዘንተኛው ግን ጉዳዩ ሌላ ነው። በሕይወት ዘመኑ መልካም ነገር የሆነለትን ሰው ማጣት፤ ጊዜ ሰጥቶ ጊዜ የወሰደውን። በመልካምነት ትዝታው ውስጥ ሆኖ ሃዘኑን ማስተናገድ። ከመልካም ሰው ትዝታ ውስጥ የሚወጣ፤ ጥልቅ ሃዘን።

የማመስገን ሕይወትን አቅጣጫ ስለማስተካከል ስናነሳ ቅደም ተከተሉን ከምንወደው ሰው ማድረጉ ምቾት የማይሰጣችሁ አንባብያን መፈጠራችሁ አይቀርም። ምክንያቱም "እንዴት ከፈጣሪ ቀድሜ ሰውን ስለማመስገን ላስብ" ልትሉ ስለምትችሉ። በእርግጥ አሳማኝ ምክንያት ነው። ነገር ግን በአጠገባችን ያለውን በአካል የምናውቀውን ሰው ሊመሰገን ሲገባው ያላመሰገንን እንዴት በአካል የማናውቀውን ፈጣሪን እናመሰግናለን? ይህን አመክንዮ በልባችን ይዘን ንባባችንን አስተካክለን መቀጠል እንችላለን።

በምሥጋና በጊዜ ቀለበት ውስጥ ከአንድ ሁኔታ ወደሌላው ስንሸጋገር አስቸጋሪው ሰውን በጠንካራ ጎኑ እንዲበረታ ባደረግነው ቁጥር ደካማ ጎኑን እየቀነሰ የመሄድ እድልን ይፈጥራል። አበባየሁሽ ብለው የሄዱ ልጆች በየቤታቸው ያሉትን አስቸጋሪ ሰዎችን አስበው ይህን ቢተገብሩ በቤታቸው ለውጥን ማየት መቻላቸው እሙን ነው። ሂደቱ አስቸጋሪው ሰውን መርዳት ብቻም ሳይሆን የራስን ደስታ የመፍጠር ሂደትም አካል ነውና። በጊዜ ቀለበት ውስጥ በምስጋና በር ውስጥ ያለንበትን ከባቢ የመቀየር። የአዎንታዊ ተጽእኖን ድባብ የመፍጠር። ራሳችን ጋር ባለው ነገር የሌላውን ውስጥ ለመቀየር የሚደረግ ጥረት።

### ምሬትን ማስወገድ

በጊዜ ቀለበት ውስጥ የሚጠፉና የሚጎድል ይኖራል። ጥንዶቹ በብዙ ድካም የገዙትን ቀለበት በጠፋባቸው ጊዜ የተፈጠረባቸውን የስሜት መጎዳት ማሰብ ከባድ አይደለም። በጊዜ ቀለበት ውስጥም መውጣትና መውረድ አለ። ደስታችንን በሚነጥቁን አያሌ ምክንያቶች ሰው ብዙ ጊዜ ደስታውን የሚያጣው በራሱ ሳይሆን በሌሎች ነው። በሌባ የተሰረቀ ሰው በሌባው ምክንያት ደስታውን የተነጠቀ መሆኑን ያነሳል። በሕይወቱ ውስጥ መከዳት የገጠመው ሰው እንዲሁ የደስታው መነጠቅ ምክንያት ከዳተኛው ግለሰብ መሆኑን ጠቅሶ ይነሳል። ይህ እይታ እንዴት ስህተት ሊሆን ይችላል? ተብሎ ቢጠየቅ ምላሹ "እንደየትም ሊሆን አይችልም" የሚል ይሆናል።

በተቃራኒው ግን አደገኛው ልማድ መኖሩን መካድ አይቻልም። ሌሎች የደስታችን መደፍረስ ምክንያት ናቸው ብሎ መቀበል ሕይወታችን የተረጋጋና ወጥ የሆነ ድባብ ሳይኖረው ሁልጊዜ በውጫዊ ነገር እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል። ውጫዊው ነገር ሁልጊዜ ተቀያየሪ ነው። በተቀያያሪው ነገር ላይ የሕይወትን መስመር ለመበየን መነሳት አሳሳች የሕይወት አቅጣጫን ያስይዛል። በተቃራኒው ያለው አደገኛው ልማድም ይህ ነው። በውጫዊው ነገር ምሬትን አርግዞ መኖር።

ሕይወትን በውስጣዊ እንጂ በውጫዊው ሁኔታ እንድትመራ መፍቀድ አይገባም የሚለው አተያይ ደጋግሞ ማሰላሰል የሚገባ ነው። አንባቢው በሕይወቱ ተጎዳሁ የሚልባቸውን ክስተቶች ለማሰብ ይሞክር። ምን ያህሉ ከውጫዊ አካል በኩል በመጣ ተጽእኖ የተፈጠረ እንደሆነ ያስባል? ሁሉም የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው። ከጉዳቱ ለመውጣት የተሄደበት ነገር "ውጩን በመቀየር" ወይንስ "ውስጥን በመቀየር" የሚለውን አስከትሎ እንዲሁ ይጠይቅ። ምሬት ውስጥ የሚከርሙ ሰዎች ውስጥን ለመቀየር አንድ እርምጃ መራመድ የከበዳቸው ሆነው ስለሚገኙ።

ምሬትን አስወግዶ በጊዜ ቀለበት ውስጥ አትራፊ ለመሆን የሚተላለፈው መልእክት በውስጣዊ ጥንካሬያችሁ ውጩን ተቆጣጠሩት የሚል ነው። ውጫዊው ነገር በየወቅቱ የሚቀያየር ነው። በመሆኑም የተረጋጋ ሕይወትን ከመምራት የሚከለክለው እርሱ ነው። መፍትሄው ውስጥን መገንባት፤ በተለዋወጭ ውጫዊ ተጽእኖ ውስጥ እየቀዘፈ ወደ መዳረሻው መሄድን ግቡ ያደረገ ጉዞ።

ምሬትን አስወግደው በጊዜ ቀለበት ውስጥ አትራፊ ሆነው የሚወጡ ሰዎች የመሰጠት ቁርጠኝነት፣ ትእግስት፣ ፍቅር፣ ተስፋ፣ ራእይ፣ ማካፈል፣ ወዘተ በውስጣቸው ያሉ ናቸው። በመሰጠት የታነጸ ሰው በዝናብ በቸነፈሩ ውስጥ አልፎ ማሳካት የሚፈልገውን ለማሳከት ስለሚሄድ የውጫዊው አየር መቀያየር ከጉዞው አይመልሰውም። አትሌቶቻችን ለእዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ትእግስትን የለበሰ ሰው ተስፋ አስቆራጭ የሆኑ ከመስመር የሚያወጡ ጉዳዮች በገጠሙ ልክ እየተጋፈጠ ተጨማሪውን አንድ ቀን በደስታ የሚቀበል በስተመጨረሻ የድል ማለዳውን ከማየት የማይመለስ ነው። ሌሎቹም እሴቶች ድምር ውጤታቸው የተረጋጋ፣ የሚያደርገውን የሚያውቅ፣ አካሄዱ ከዓላማው አንጻር የተቃኘን ሰው ያደርጋሉ።

ምሬት በምሬት ይባዛል። በምሬት ውስጥ ያለን ሰው ለማውጣት መሞከር ተገቢነት አለው፤ ነገር ግን ምሬቱ ተጋብቶብን የጊዜ ቀለበታችን በምሬት የተገመደ እንዲሆን ማድረግ ግን አስፈላጊ አይደለም። ውሏችንን እንደ ህልማችን ማድረግ ተገቢነት ይኖረዋል። ህልሙ እግር ኳስ ተጫዋቾች የሆነ ሰውና ለእዚያ እየኖረ ያለሰው ውሎውን ተመሳሳይ ራእይ ከሚጋራው ጋር ቢያደርግ ጥቅሙ ለእርሱ መሆኑ እሙን ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ከፈጣሪያችን ጋር ጊዜን ማሳለፍ። ከፈጣሪ ጋር እና አብረውን ካሉ መልካም ሰዎች ጋር ጊዜን በማሳለፍ ረገድ ውስጣችን ውጫዊውን ተጽእኖ ተቋቁሙ ማደግ የሚችልበትን አቅም ያገኛል።

### የአልችልም ጠላት መሆን

ጥንዶቹ ቀለበቱን ከእጃቸው ለማጥለቅ የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ። በስተመጨረሻ ግን በጊዜ ቀለበት ውስጥ ወደቁ፤ ጥንቃቄ በሚፈልገው ጊዜ ላይ ባለመጠንቀቅ ያሰቡትን ማድረግ ሳይችሉ ቀሩ። እችላለሁ ብሎ መነሳት ለብዙ ሰው ይቸግረዋል፤ ምክንያቱም እችላለሁ በማለት ብቻ የሚሆን ነገር ስለሌለ። የአልችልም ጠላት ለመሆን ራስ ላይ መስራት ስለሚገባ። አዲስ አመት በመጣ ቁጥር በአመቱ ውስጥ ምን ማሳካት እንዳሰብን የመዘርዘር ልማድ ይኖረን ይሆናል። ማሳካት የፈለግነውን ማሳካትን ስናስብ አስቸጋሪ የሚሆኑብንን ነጥቦችም እንዲሁ ልንለያቸው እንሞክራለን። ለለውጥ መነሳትን ስንመርጥ አትችልም የሚለን በአካባቢያችን የሚሰማ ድምጽ እግራችን ላይ የታሰረ ገመድ ሆኖ ልናገኘው እንችላለን።

አትችልም፤ አትችይም የሚለው ድምጽ በበረከተበት ከባቢ ውስጥ እየኖረን በእችላለሁ መንፈስ ለለውጥ የሚነሱት ማግኘት አንችልም። ልጆች ሲያድጉ የሚነገራቸው፤ ታዳጊዎ ብላቴና ከውስጧ የመዘገበችው፤ ወጣቱ ለለውጥ ጊዜውን እንዲጠበቅ የሚጠበቅበት ወዘተ በአልችልም መንፈስ ውስጥ ሆኖ ለመስራት የሚነሳው ሁሉ እየጨነገፈበት ቢቸገር እንዴት ሊገርመን ይችላል።

አለመቻልህን በውስጥህ ከምታመላለስ መቻልህን ለራስህ ንገረ። የጊዜ ቀለበት ውብ ሆኖ የሚታየው በመቻል መንፈስ፤ ለመቻል ተግባራዊ እርምጃን በመራመድ ነውና። በዙሪያህ ያለው ሳር ቅጠሉ ስለመቻል የሚናገረው ድምጽ ጎርናነቱ በዝቶ ጆሮህን እስከትይዝ የሚያደርስ ቢሆንም አሁንም መቻልን አስብ። ቀላል አይደለም ከባድ ነው። የምንኖርበት የድህነት ጥግ ይታወቃል። አልጠራ ያለው የፖለቲካ መንገዳችን የፈጠረው ውጥንቅጡ እንዳለ ነው። የትምህርት ጥራቱ አሽቆልቁሎ ባለዲግሪውና ዲግሪው የሌለው መካከል በእውቀት ላይ ልዩነት የሌለው ሆኖም ይታያል። ሁሉም ነገር አለመቻላችንን እየነገረን ባለንበት ዘመን ውስጥ ስለመቻል ማንሳት እብደትም ሊመስል ይችላል። በጊዜ ቀለበት የለውጥ መንገዱ ውስጥ ግን የመቻል መንፈስ ግን የሚይዘው ቦታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። የመቻል መንፈስ ለሁላችን እንዲሆንልን ለጊዜ የምንሰጠው ትርጉም ውስጥ ቦታ ይኑረው። በአንድ ወር ውስጥ ይህን ማድረግ እችላለሁ፤ በአመት ውስጥ፤ በሦስት አመት ውስጥ ብሎ ግብን ለማስቀመጥ የመቻል መንፈስ እጅጉኑ ያስፈልገናል።


በምሥጋና፤ ምሬትን በማስወገድ እና እችላለሁ ብሎ በመነሳት የጊዜ ቀለበትን እናጥልቅ። ጊዜ ዳኛ ይባልስ የለ። ጊዜ የንጉሥ ቀለበት ሲሆን።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ለቢሊዮኖች ዶላር ገቢ እየተንደረደረ ያለው አረንጓዴ ወርቅ

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ቡና በ2014 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ገቢ አስገኝቷል፤

ቡና ለአገር የኢኮኖሚ ዋልታ በመሆን ይታወቃል፤ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ከሚጠቀሱ የኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች መካከል ቀዳሚው ነው፡፡ ባለፉት ዓመታትም ይሁን ዘንድሮ ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ዋልታና ማገር በመሆን የላቀ ድርሻ እያበረከተ ይገኛል፡፡ በተለይም አገሪቷ የውጭ ጫናዎችን ተከትሎ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በውጭ ምንዛሬ እጥረት እየተፈተነች ባለችበት በዚህ ወቅት የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ባለውለታነቱን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የዛሬው የስኬት አምዳችንም ቡና ባስመዘገበው ስኬት ላይ አድርጓል።

መንግሥት ለቡና ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱን ተከትሎ ከቡና እየተገኘ ያለው የውጭ ምንዛሬ በየአመቱ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ የአገሪቱን ኢኮኖሚም ትርጉም ባለው መንገድ እየደገፈ ይገኛል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱትም፤ አገሪቱ ለአመታት ከቡና የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ ሳትሆን የቆየች ስትሆን፣ ከቅርብ አመታት ወዲህ ግን ለውጦች እየታዩ መጥተዋል። ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶች ገቢ ግብርና 20 በመቶውን የሚሸፍን ሲሆን፣ ከግብርና ምርቶችም ቡና ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡

የቡናና ሻይ ባለስልጣን መረጃዎች እንደያስረዱት፤ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ቡና በዓለም ገበያ ተፈላጊና ተወዳዳሪ እየሆነ መጥቷል፤ ከቡና ምርት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግም ቡና አምራች በሆነው አርሶ አደር ላይ ሰፊ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

### የኢትዮጵያ ቡና በዓለም ገበያ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ የቻለችበት ሚስጥር

ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ወቅት በታሪኳ አይታው የማታውቀውንና ታሪካዊ የሆነውን ድል በቡናው ዘርፍ መቀዳጀት ችላለች፡፡ ይህ ስኬት ሊመዘገብ የቻለውም በቡናው ዘርፍ መሰረታዊ የሚባሉ ለውጦችን ማምጣት በመቻሉ ነው፡፡

ባለስልጣኑ በዚህም በ2013/14 ዓ.ም በመጀመ ሪያው ወር ላይ ዘርፉን ውጤታማ ማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት በዕቅድ ይዞ ተንቀሳቅሷል፡፡ በተለይም የውጭ ንግዱን ለማሳለጥ በቡና ልማቱና በግብይቱ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮች ተለይተው እርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡ በቁርጠኝነት ወደ ሥራው መግባት በመቻሉም ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የቡና ገበያ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በበጀት ዓመቱ በአስር ወራት ብቻ አንድ ቢሊዮን 14 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡/ ይህ አሀዝ በበጀት አመቱ መጨረሻ አንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ደርሷል/ ይህ ደግሞ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ባለበት ከቡና ብዙም ተጠቃሚ ሳትሆን ለቆየች አገር ኢኮኖሚ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ገበያ ከምትልካቸው የግብርና ምርቶች መካከል ቡና በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በ2014 በጀት አመት ከቡና የተገኘው የውጭ ምንዛሬ አስር ወራት ውስጥ ብቻ አገሪቷ አጠቃላይ በውጭ ገበያ ካገኘችው ገቢ ጋር ሲነጻጸር 30 በመቶ የሚሆነውን መሸፈን ችሏል፤ ከግብርናው ዘርፍ ጋር ሲነጻጸር ደግሞ 50 በመቶ ያህሉን ሸፍኗል፡፡

ይህን ውጤት ለማስመዝገብም ባለስልጣኑ ከሠራቸው በርካታ የሪፎርም ሥራዎች መካከል በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉትን ችግሮች ነቅሶ ማውጣት አንዱና ቀዳሚው ነበር፡፡ በተለይም በቀጥታ ትስስር አርሶ አደሮችና አቅራቢዎች ምርታቸውን በቀላሉ መቀባባል እንዲችሉ በማድረግ ረጅም ርቀት መጓዝ ውስጥ ተገብቷል፡፡

ጥራቱን የጠበቀ ቡና በመጠን እንዳይባክን አርሶ አደሮች ለአቅራቢዎች፤ አቅራቢዎች ደግሞ በቀጥታ ለላኪዎች ማስረከብ እንዲችሉና ላኪዎችም ዱካውን ተከትለው መለየትና ማወቅ እንዲሁም ምርቱን ለዓለም ገበያ ማቅረብ የሚያስችላቸው ስርዓት ተዘርግቷል፤ ይህም የኢትዮጵያ ቡና በተሻለ ዋጋ በዓለም ገበያ እንዲሸጥና ዳጎስ ያለ ገቢም እንዲገኝ አስችሏል፡፡

በቡናው ዘርፍ የተሰማራ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በቁርጠኝነት መስራት በመቻሉ የተገኘ ውጤት ስለመሆኑም የባለስልጣኑ ኃላፊዎች ይገልጻሉ። በተለይም በግብይት ሥርዓት ውስጥ የነበሩ ለኤክስፖርቱ ማነቆ ሆነው የቆዩ አሰራሮችን በመፈተሽ በማስተካከልና የኮንትሮባንድና ህገወጥ ንግድን በሶፍትዌር በመከታተል ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል። ቡና ጭነው ከመንገድና ከመስመር የሚያወጡ ባለሃብቶች እንዲሁም አሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ በመውሰድ የኮንትሮባንድ መጠኑ እንዲቀንስና ቡና ወደ ዓለም ገበያ በቀጥታ እንዲገባ ተሠርቷል፡፡ በተጨማሪም እምነት በመፍጠር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የተሰራው ሥራ ለተመዘገበው ውጤት የጎላ ድርሻ አለው፡፡

### ያለፉት ሁለት አመታት አፈጻጸም

ወደ ውጭ ከሚላከው ቡና የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በ2013 በጀት ዓመት ኢትዮጵያ በወጪ ንግድ ላይ ለዓመታት ሲታይ የነበረውን የቁልቁለት ጉዞ ከመግታት አልፋ አዲስ ታሪክ አስመዝግባ ነበር። ይህ ታሪክ ከተመዘገበባቸው መካከል ደግሞ ቡና አንዱ ነው። በጀት ዓመት 248 ሺህ 311 ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ 907 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ማግኘቷን ባለስልጣኑን ዋቢ ያደረጉ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ይህም ገቢ በ2009 ዓ.ም ከተገኘው 882 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ የ25 ሚሊየን ዶላር ብልጫ ነበረው። ያለፈውም አመት ኢትዮጵያ በታሪኳ ከቡና ምርት ከፍተኛ የተባለውን የውጭ ምንዛሪ ያገኘችበት ነው፡፡

### የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድና አፈጻጸም

በ2014 በጀት አመት ኢትዮጵያ ቡናን ወደ ውጭ መላክ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በመጠንም ሆነ በገቢ ሪከርድ መስበር ተችሏል። በበጀት ዓመቱ ወደ ተለያዩ የዓለም አገራት የተላከው 300 ሺ ቶን ቡና ሲሆን፣ በዚህም አንድ ነጥብ አራት ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡

299 ሺ 340 ነጥብ 13 ቶን ቡና ወደ ውጭ ለመላክ አቅዶ 299 ሺ 314 ነጥብ 32 ቶን መላክ ተችሏል። ከዚህም አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል። ይህም ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በመጠን 51 ሺ 002 ነጥብ 66 (20.54%) እና በገቢ ደግሞ በ488 ነጥብ 14 ሚሊየን ዶላር (53.82%%) ጭማሪ አስመዝግቧል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት አስራ ሁለት ወራት የተላከው ቡና በመዳረሻ አገራት ሲታይ ደግሞ ጀርመን በመጠን 63,499.74 ቶን (21%) ድርሻ እና በገቢ 250.88 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር (18%) ድርሻ፣ አሜሪካ በመጠን 28,834.33 ቶን (10%) ድርሻ እና በገቢ 177.17 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር (13%) ድርሻ፣ እና ሳውዲ አረቢያ በመጠን 44,676.00 ቶን (15%) ድርሻ እና በገቢ 176.52 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር (13%) ድርሻ አፈፃፀም በማስመዝገብ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃን በገቢ አስመዝግቧል፡፡

የተቀሩት በ2014 በገቢ ቅደም ተከተል 4ኛ ቤልጅዬም፣ 5ኛ ጃፓን፣ 6ኛ ደቡብ ኮሪያ፣ 7ኛ ቻይና፣ 8ኛ ጣሊያን፣ 9ኛ ዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ እና 10ኛ ታይዋን ናቸው፡፡ ከ1 እስከ 10 ያሉት በአጠቃላይ በመጠን 80 በመቶ እና በገቢ 81 በመቶ ይሸፍናሉ።በጥቅሉ የእነዚህ ዋና 10 መዳረሻ አገራት ከ2013 አፈፃፀም ጋር ሲወዳደር በመጠን 26 በመቶ እና በገቢ 59 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

### የኤክስፖርት ግቡን ለማሳካት

የኤክስፖርት ግቡን ለማሳካት ባለስልጣኑ በተለይም ለቡና ኤክስፖርተሮችና አቅራቢዎች የብድር አቅርቦት እንዲመቻች በማድረግ ከባንኮች ጋር በመነጋገር አፋጣኝ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ የቡና ኤክስፖርት ሂደትን ለማሳለጥ እና የሎጂስቲክስ አገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን የተሻለ የውጪ ምንዛሬ አፈጻጸም ለማስመዝገብ በኮንቴነር አቅርቦት፣ በምድር ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እና በአንድ መስኮት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የታዩ ችግሮችን ለመፍታት ባለስልጣኑ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

በዓለም አቀፍ ኢግዝቢሽኖች (በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በዱባይ) እና በበይነ መረብ በሚካሄዱ ዝግጅቶች ላይ በመሳተፍ የኢትዮጵያ ቡና እንዲተዋወቅ ተደርጓል፤ አዳዲስ ገበያን በማፈላለግ በኩል በኤሽያ አገሮች ላይ ትኩረት ተደርጎ ተሰርቷል። በዚህም ቻይና እና ታይዋን ወደ አስር ዋና ዋና ገዥ አገራት ተርታ እንዲገቡ ሆኗል፡፡

ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ እና አገራዊ የገበያ መረጃዎችን በማደራጀት እና በመተንተን በቡና ኮንትራት መረጃ በመሰብሰብ፣ ዝቅተኛ ዋጋን በመተንተን ማሰራጨት ተችሏል፡፡ የመረጃ ጥራትን ከማሳደግ እንዲሁም የቡና ግብይት ቁጥጥርን ዘመናዊ ከማድረግ አንጻር የቡና መረጃ ዳታ ቤዝ እና የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ለመዘርጋት በታቀደው መሰረት ከሸኙት ጣቢያዎች በየዕለቱ የሚሸኝ ቡና በሲስተም እንዲደገፍ የማድረግ ሥራም ሰርቷል፡፡

ግብይቱን ለማዘመንና ቁጥጥሩን ለማጠናከር የዳታ ቤዝ ሶፍት ዌር እና በ13 አገልግሎት ዘርፎች የኦንላይን ለደንበኛ አገልግሎት በመስጠቱ ግብይቱ እንዲሳለጥ ሆኗል፡፡ የኮንትሮባንድ ቁጥጥር ሥራም ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፣ ለሶስተኛ ጊዜ በአገሪቱ የባለ ልዩ ጣዕም ቡና ጥራት ውድድር ተካሂዷል፡፡ ውድድሩም በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አስተባባሪነት በተሳካ ሁኔታ መካሄድ ችሏል፡፡

### የተመዘገበውን ውጤት ለማስቀጠል

የቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ በዘርፉ በተለይም በግብይት ስርዓት ውስጥ የነበሩ ችግሮችና የተለያዩ ማነቆዎችን ነቅሶ ማውጣት ተችሏል፤ ይህን ተከትሎም ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደተቻለ የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ለእዚህም ባለስልጣኑ የተለያዩ አሰራሮችንም መከተሉን ይናገራሉ፡፡

የኢትዮጵያ ቡና ግብይት እጅግ በጣም የተንዛዛና ምንም እሴት የማይጨምሩ በርካታ ተዋንያኖች የነበሩበት መሆኑን ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት ይህንን የግብይት ሥርዓት በማሳጠር ምርቱን በቀጥታ ከአርሶ አደር ወደ አቅራቢ ከአቅራቢ ደግሞ ወደ ላኪ በመድረስ ሲባክን የነበረውን የቡና ምርት በመጠንና በጥራት መታደግ ተችሏል ይላሉ፡፡

ስለሆነም ዘንድሮ ወደ ውጭ ገበያ በተላከው ቡና ካለፈው አመት በመጠን 52 ሺ ቶን ቡና ብልጫ ተመዝግቧል። የጥራት ደረጃዎቻቸውንም ከፍ በማድረግ የኢትዮጵያ ቡና በተሻለ ዋጋ ለዓለም ገበያ እንዲሸጥ ተደርጓል፡፡ ሌላው የቡና ሽኝትን አስመልክቶ ቡና ከወረዳ እስከ ቡና ላኪ መጋዘን ማድረስ የሚያስችል ሶፍትዌር በማበልጸግ መከታተል ተችሏል፡፡ ይህም የህገወጥ ንግድን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት አስችሏል፡፡ በዚህም በህገወጥ መንገድ ከአገር ይወጣ የነበረውን ቡና ወደ ስርዓቱ እንዲገባ ማድረግ መቻሉም ለተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ድርሻ አበርክቷል፤ በወጪ ንግዱ መጠን ላይም ከፍተኛ የሆነ የመጠን ጭማሪ ማሳየት አስችሏል፡፡

ኢትዮጵያ ቡናን ወደ ውጭ ገበያ መላክ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ሶስት መቶ ሺ ቶን ቡና ለዓለም ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝታለች፡፡ ይህ ውጤት መመዝገብ የቻለው ቅንጅታዊ በሆኑ አሰራሮች ምክንያት እንደሆነ የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ ዶክተር አዱኛ፣ ውጤቱን ለማስቀጠል ብሎም የበለጠ ውጤታማ ለመሆን በዋናነት የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶችን በማጠናከር ከቴክኖሎጂ ጋር በማዛመድ እንደሚሠራና በዚህም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የት ቦታ ላይ እንደሚያስፈልጉ መለየቱን ጠቅሰው፣ በተለይም ቡና አቅራቢና ላኪው በኦን ላይን እየተቀባበሉ ግብይቱን ግልጽነት ባለው መንገድ ማከናወን የሚያስችል የአሰራሩ ስርዓት ተዘርግቷል ይላሉ። ነባርና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ባለፈው ዓመት እንደ ክፍተት የታየውን ችግር በማጥራት በቀጣይ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ዝግጅቱ መጠናቀቁንም ነው ያስታወቁት፡፡

በቀጣይ ዓመትም ሶስት መቶ ሃያ ሺ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እየሰራ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡ ባለድርሻ አካላት በተመዘገበው ውጤት ሳይዘናጉ ከባለስልጣኑ ጋር በመሆን ቅንጅታዊ አሰራሮቻቸውን አጠናክረው በማስቀጠል የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ እንዲሰሩም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የቡናና ሻይ ባለስልጣን ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የደረሰውን የአገሪቱን ዓመታዊ የቡና ሽያጭ ገቢ፣ ከአምስት ዓመታት በኋላ 4.6 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ግብ ማስቀመጡን ሪፖርተር ጋዜጣ በቅርቡ ዘገቧል፡፡

በቡናና ሻይ ባለስልጣን ቴክኖሰርቭ በተባለ የጥናት ተቋምና በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ድጋፍ የተዘጋጀው የቡና የ15 ዓመት ስትራቴጂ ይፋ በተደረገበት ወቅት እንደተጠቆመው፤ ስትራቴጂው ከምርት እስከ ግብይት ያለውን የአገሪቱን የቡና አሁናዊ እንቅስቃሴና በቀጣይ ዓመታት ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ውጤት የሚያመላክት ነው፡፡

በቡናና ሻይ ባለስልጣን የግብዓት አቅርቦትና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ገዛኸኝ ዋቢ ያደረገው ዘገባው እንዳመለከተው፤ በስራ ላይ የቆየው ስትራቴጂ ከአጠቃላይ ግብርና ጋር ተዳብሎ ሲሠራበት የቆየ ሲሆን፣ የአገር ውስጥም ሆነ የዓለም አቀፍ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ለቡና ራሱን የቻለ የቡና ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ከስትራቴጂው ዓምዶች አንዱ የሆነው ልማት ሲታይ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሔክታር የሚገኘው የቡና ምርት ከዓለም ጋር ሲገናኝ በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ካልተቻለ ሌሎቹን የስትራቴጂው ዓምዶች ማሳካት እንደማይቻል ተናግረዋል። ስለሆነም የተዘጋጀው ስትራቴጂ ምርትን በተመለከተ አጽንኦት መስጠቱን እንደሚያመለክት ተጠቁሟል፡፡

በስትራቴጂው ከተቀመጡ ግቦች ውስጥ ከቡና ኤክስፖርት አገሪቱ ከአምስት ዓመታት በኋላ ዓመታዊ ገቢዋ 4.6 ቢሊዮን ዶላር ይደርሳል የሚል ዕቅድ ተቀምጧል። ስትራቴጂው በዚህ ወቅት ይፋ ይደረግ እንጂ ከላዩ ላይ እየተቀነሰ ተግባራዊ መደረግ የጀመሩ የተለያዩ ተግባራት ሁለት ዓመታት ማስቆጠራቸው ተጠቁሟል፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## መልካም ተሞክሮዎች የታዩበት የመንገድ ፕሮጀክት

**መሳኩ ኤርሴ**

ለከተሞች ከሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶች መካከል የመንገድ መሰረተ ልማት አንዱ ነው:: የመንገድ መሰረተ ልማቶች ለተሽከርካሪዎችና ለእግረኞች እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል:: እንደ አዲስ አበባ ላሉት በርካታ ተሽከርካሪዎች ለሚርመሰመሱባቸው ከተሞች ደግሞ የትራፊክ ፍሰትን ለማሳለጥና ሁለንተናዊ እድገትን እውን ለማድረግ ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም የመንገድ መሰረተ ልማት ሽፋንን ከፍ ለማድረግ እንዲሁም ለማዘመን እየሰራ ይገኛል:: ይህን ተከትሎም የከተማዋ የመንገድ መሰረተ ልማት ሽፋን እያደገ መጥቷል:: እስካሁን የተገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶች ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየታየ ካለው የከተማዋ መስፋፋት እና እየጨመረ ካለው የከተማዋ የህዝብ ቁጥር እንዲሁም የተሽከርካሪ ብዛት ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም::

ይህን ችግር ለመፍታትም የከተማውን ትራፊክ ፍሰት ለማሳለጥ እና የመንገድ ሽፋኑን ከፍ ለማድረግ የሚሰሩ ስራዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል:: ከተማ አስተዳደሩ የመንገድ ግንባታን ዋናው የርብርብ ማዕከል በማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል:: ከከተማዋ መሰረተ ልማት ጋር የተጣጣመ የመንገድ መሰረተ ልማት ለመዘርጋት ከአገራዊ ለውጡ በኋላ የበርካታ የመንገድ ፕሮጀክቶች ግንባታ በመከናወን ላይ ናቸው:: ከለውጡ በኋላ መገንባት ከጀመሩት የመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዳንዶቹ መጓተት የሚታይባቸው ቢሆንም፣ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ የተጠናቀቁ ለቀጣይ የመንገድ ፕሮጀክቶች ተሞክሮ የተቀሰመባቸው ግንባታዎችም አሉ::

መልካም አፈጻጸም ከታየባቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል ከፑሽኪን አደባባይ - ጎፋ ማዞሪያ - ጎተራ ማሳለጫ የመንገድ ፕሮጀክት አንዱ ነው:: ፕሮጀክቱ ከለውጡ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከተገነቡት የመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ በትልቅነቱ ይጠቀሳል:: በፕሮጀክቶች ጥራትም ሆነ ፍጥነት አዲስ ልምድ እየዳበረ መምጣቱን ያመላከተ ሆኗል::



**በቅርቡ እንደሚመረቅ የሚጠበቀው የሳር ቤት ጎፋ ማዞሪያ ጎተራ ማሳለጫ መንገድ ከፊል ገጽታ**

የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቱ በ2012 በጀት ዓመት መስከረም ወር ላይ ከተጀመሩ ፕሮጀክቶች አንዱ ሲሆን፣ በአጠቃላይ 3 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር ርዝመትና ከ30 እስከ 45 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ነው::

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ምክትል ኃላፊ አቶ ኢያሱ ሰለሞን በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፤ ይህ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ከ1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ነው ግንባታው እየተከናወነ ያለው:: የመንገድ ግንባታው በቻይና ፈርስት ሀይ ዌይ ኢንጂነሪንግ በተባለ ተቋራጭ ድርጅት እየተከናወነ ሲሆን፤ የማማከር ስራውን ደግሞ ቤስት አማካሪ ድርጅት እያከናወነ ይገኛል::

ቀደም ሲል ከፍተኛ የትራፊክ ጫና የነበረበትን የሳር ቤት - ጎተራ እና የጨርቆስ - ጎፋ ማዞሪያ መስመር ከፍተኛ መጠን ያለው የትራፊክ ፍሰት ለማሳለጥ ከፍተኛ ሚና አለው:: በተለይ ከጎተራ ማሳለጫ ወደ አሌክሳንደር ፑሽኪን አደባባይ እና ከዚያ ጋር ከሚጋጠሙ ሌሎች መንገዶች ጋር የመንገድ ኔት ወርኩን ማስፋፋት ያስቻለ ትልቅ ፋይዳ ያለው የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ነው ብለዋል::

እንደ አቶ ኢያሱ ማብራሪያ፤ በተለይ ጎፋ ማዞሪያ ተብሎ የሚጠራው እና በተለምዶ ቄራ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ በሶስት ደረጃዎች የተከፈለ የትራፊክ ማሳለጫ ግንባታ ተከናውኖለታል:: አንደኛው የውስጥ ለውስጥ የመኪኖች መተላለፊያ ዋሻ ነው:: ይህ ዘመናዊ ዋሻ በከተማዋ የመንገድ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነ በሁለቱም አቅጣጫዎች 320 ሜትር ርዝመት ያላቸው የውስጥ ለውስጥ መተላለፊያ ዋሻ ግንባታዎች ተከናውነውለታል::

ይህ ረጅም ዋሻ የአካባቢውን የትራፊክ ፍሰት በማሳለጥ ረገድ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው:: ምክንያቱም ተሽከርካሪዎች ውስጥ ለውስጥ እንዲሁም በላይ ማለፍ ይችላሉ:: ይህ አይነት መንገድ በአዲስ አበባ በሌሎች አካባቢዎች እንዲሁም በመላ አገሪቱ ከተሞች አካባቢ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታየ ያለውን የትራፊክ መጨናነቅ ለመቅረፍ ጥቅም ላይ መዋል አለበት:: መሰል ፕሮጀክቶች የአገራችንን ከተሞች ገጽታ ለመቀየር ከፍ ያለ ፋይዳም ይኖራቸዋል::

እንደዚሁም ደግሞ ከዋሻው በላይ በኩል የሚመጡ ተሽከርካሪዎች ምንም ነገር ሳያውካቸው እንዲያልፉ የሚያስችሉ መንገዶች ተገንብተዋል:: ከጎፋ ወደ ለገሃር አቅጣጫ እንዲሁም በተቃራኒው ከጎፋ ማዞሪያ ወደ ለገሀር አቅጣጫ ለሚሄዱ ተሽከርካሪዎች ደግሞ አደባባይ ውስጥ መግባት ሳያስፈልጋቸው የሚያሻግር የማሳለጫ ድልድይን ጨምሮ በቀጣይ ከአካባቢው የመንገድ መረብ ጋር የተሳሰረ የፈጣን የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት እንደሚሰጥበት የሚጠበቀው መንገድ (Bus Rapid Transit) አካቶ የተገነባ መሆኑን ነው ያብራሩት::

እስከ ሳር ቤት የተሻለ መንገድ እንዲሁም እስከ ጎተራ ድረስ ቀደም ብሎም የተሻለ መንገድ መገንባቱን አስታውሰው፣ ቄራ አካባቢ በጣም መጨናነቅ ይታይበት እንደነበር ተናግረዋል፤ ይህንን መጨናነቅ ለመቅረፍ መንገዱን መገንባት ማስፈለጉን አቶ ኢያሱ ይገልጻሉ፤ ፑሽኪን አደባባይ - ጎፋ ማዞሪያ - ጎተራ ማሳለጫ ሲገናኝ እና ቀጥሎ ሜክሲኮ ድረስ ያለውን በማገናኘት ከተማዋን የማስዋብ ስራ የተሳካ እንዲሆን ስለሚያስችል ነው::

የፑሽኪን አደባባይ፣ ጎፋ ማዞሪያ እና ጎተራ ማሳለጫ የመንገድ ፕሮጀክት ብቻውን ቆሞ የመንገድ ፕሮጀክት አይደለም:: ጎተራ ሲሚንቶ ፋብሪካ የነበረበት አካባቢ የሚሰሩ ብዙ ፕሮጀክቶች አሉ:: ከነዚህ ፕሮጀክቶች አንዱ ይገነባል ተብሎ የሚታሰበው «አዲስ ቱሞሮው» የተሰኘው ዘመናዊ ከተማ ነው:: ያንን ከተማ፣ ቦሌን፣ ቄራን እና ሳር ቤትን የሚያስተሳስር ፕሮጀክት እንደመሆኑ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው::

አቶ ኢያሱ ይህ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት አሁን በመጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ይገኛል ብለዋል:: ከሁለት ሳምንት በፊት ባለስልጣኑ ይፋ እንዳደረገው መረጃም ግንባታው 98 በመቶ ገደማ ተጠናቋል:: የመንገድ ፕሮጀክቱ አሁን ላይ ካልተጠናቀቁ ጥቂት የእግረኛ መንገድ እና ከአንዳንድ የእርማት ስራዎች በስተቀር ሌሎች የግንባታ ስራው ዋና ዋና ተግባራት ተጠናቀው በሁሉም አቅጣጫ ለትራፊክ ክፍት ሆኗል::

የመንገድ ፕሮጀክት ከሌሎች ፕሮጀክቶች አንጻር ሲነጻጸር በፍጥነት የተገነባ ፕሮጀክት ነው ያሉት አቶ ኢያሱ፤ ከፕሮጀክቱ ጋር የተጀመሩ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ግንባታ በሚፈለገው ፍጥነት አለመሄዱን ጠቅሰዋል:: ለዚህም እንደ ማሳያ ያነሱት ከአውቶቢስ ተራ በመሳለሚያ ወደ 18 ቁጥር ማዞሪያ የመንገድ ፕሮጀክትን ነው:: ሁለቱም የመንገድ ፕሮጀክቶች በተመሳሳይ ጊዜ የግንባታ ስራቸው የተጀመረ ቢሆንም፣ ከአውቶቢስ ተራ በመሳለሚያ ወደ 18 ቁጥር ማዞሪያ የሚወስድ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት መጓተት ታይቶበታል ብለዋል::

የፑሽኪን - ጎፋ ማዞሪያ - ጎተራ ማሳለጫ ፕሮጀክት ሲታይ ሰፊ ስትራክቸራል ስራዎች የሚያስፈልጉት ፕሮጀክት ሆኖ እያለ በፍጥነት ወደ መጠናቀቂያ ምዕራፍ ደርሷል። የአውቶቢስ ተራ- መሳለሚያ- 18 ማዞሪያ ፕሮጀክት ግን ከወሰን ማስከበር ጋር የነበሩ ችግሮች እና በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ በሚኖርበት ቦታ ላይ እየተሰራ ያለ የማስፋፊያ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መጓተት ታይቶበታል። የወሰን ማስከበር ችግር የአውቶቢስ ተራ- መሳለሚያ - 18 ማዞሪያ ፕሮጀክት ብቻ ችግር ሳይሆን ለሌሎች ፕሮጀክቶችም መጓተት ምክንያት ሆኖ ቆይቷል::

የፑሽኪን- ጎፋ ማዞሪያ- ጎተራ ማሳለጫ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክትም ከወሰን ማስከበር ችግሮች የጸዳ አልነበረም ይላሉ አቶ እያሱ:: ያጋጠሙትን የወሰን ማስከበር ችግሮች በመፍታት ረገድ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሰፊ ርብርብ ማድረጋቸውን ጠቅሰው፣ ይህም ለግንባታ ስራው በፍጥነት መጠናቀቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ብለዋል::

እንደ አቶ ኢያሱ ማብራሪያ፤ በከተማዋ የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶች በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይጠናቀቁ እንቅፋት ከሚሆኑ መካከል የግንባታ ተቋራጮች ልምድ እና አቅም ማነስ አንዱ ነው:: የፑሽኪን አደባባይ፣ ጎፋ ማዞሪያ ጎተራ ማሳለጫ ፕሮጀክት ግንባታ እያከናወነ የሚገኘው ተቋራጭ በተለያዩ የመንገድ ግንባታ ስራዎች ውስጥ ሰፊ ልምድ ያለው የግንባታ ተቋራጭ መሆኑ ፕሮጀክቱ በተያዘለት



**የዋሻው አንዱ መንገድ፤**

የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል::

ያለ ህዝብ ሁለንተናዊ ተሳትፎ የትኛውንም ፕሮጀክት በፍጥነት በስኬት ማጠናቀቅ የሚታሰብ አይደለም ያሉት አቶ ኢያሱ፤ የፑሽኪን አደባባይ - ጎፋ ማዞሪያ - ጎተራ ማሳለጫ ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲከናወን ከሁሉም በላይ የግንባታው ባለቤትና ዋነኛው ተጠቃሚ የሆነው የግንባታ ስራው በሚከናወንበት አካባቢ ያለው የከተማው ነዋሪ ለግንባታ ስራው መቀላጠፍ የበኩሉን ድርሻ በማበርከት ለስራው መሳካት ትልቅ ድርሻ ማበርከቱንም ጠቅሰዋል::

በከፍተኛ ወጪ ተገንብቶ ወደ መጠናቀቅ ደረጃ እየተቃረበ የሚገኘው ይህ የመንገድ ፕሮጀክት ከተገነባለት ዓላማ ውጭ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራነት እየዋለ መሆኑን ጠቁመው፣ ይህም በትራፊክ ፍሰቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደረ መሆኑን ይገልጻሉ:: በሁሉም የመንገድ አካላት ላይ እንዳይከናወኑ የተከለከሉ እንደ መኪና እጥበትና ጥገና የመሳሰሉ ህገወጥ ተግባራት በመንገድ ወሰኑ ውስጥ እየተፈፀሙ መሆናቸውን አመልክተው፣ ይህም በሂደት መንገዱን ለብልሽት እንደሚያጋልጠው አስገንዝበዋል::

ከፍተኛ መዋለ-ንዋይ ፈሶበት የተገነባው ይህ ዘመናዊ መንገድ ለታለመለት ዓላማ ብቻ ይውል ዘንድ በመንገዱ ላይ ያልተፈቀዱ ተግባራትን የሚያከናውኑ ወገኖች ከህገ ወጥ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከወዲሁ በጥብቅ እንደሚያሳስብ ነው አቶ ኢያሱ የተናገሩት::

የመንገድ ግንባታው ሂደት በመንግስት የቅርብ ክትትል ሲደረግበት የቆየ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንዲሁም የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ አዳነች አቤቤ መጎብኘታቸው ይታወሳል::

ከንቲባዋ ባለፈው ሳምንትም ግንባታውን ተዘዋውረው ጎብኝተው በአካባቢው ችግኝም ተክለዋል።

መንገዱ በተያዘለት ጊዜ እና ወጪ የግንባታ እየተጠናቀቀ መሆኑን ገልጸዋል። ፕሮጀክቱ በተያዘለት ወቅት ምንም አይነት የገንዘብና የጊዜ ጭማሪ ሳይጠይቅ በነበረው ጥብቅ የስራ ክትትል በቅርቡ እንደሚጠናቀቅ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናግረዋል።

መንገዱ የከተማዋን የወደፊት ዕድገት ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተገነባ ነው ያሉት ከንቲባዋ፣ የአካባቢው ነዋሪዎች የመንገድ ልማት ፕሮጀክት በመንከባከብና ለምግብነትም ሆነ ለጥላ የሚሆኑ ችግኞችን በመትከል ፕሮጀክቶቹን በቅንጅት እንዲያስውቡ ጠይቀዋል።

በቅርቡ የሚመረቀው የመንገድ ፕሮጀክት በአካባቢው ሲስተዋል የነበረውን የትራፊክ መጨናነቅ ከመቅረፍ ባሻገር ፈጣን አውቶብስን ጨምሮ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን ደረጃውን ጠብቆ የተገነባለት መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ የመንገዶች ኢንጅነር ሞገስ በመርሀ ግብሩ ላይ ተናግረዋል። በአገራችን ደረጃ የመጀመሪያ የመንገድ ግንባታ መሆኑንም ገልፀዋል።

የፑሽኪን አደባባይ - ጎፋ ማዞሪያ - ጎተራ ማሳለጫ ፕሮጀክት በብዙ መልኩ በአዲስ አበባ እና በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች እየተገነቡ ላሉት እና ወደፊት ለሚገነቡት ፕሮጀክቶች ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ነው:: የከተማዋን የትራፊክ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በሚያስችል መልኩ ዋሻ ያለው የመንገድ ፕሮጀክት መሆኑ አንዱ እንደ ተምሳሌትነት እንዲጠቀስ ያደርገዋል:: ከዚያ ባሻገር ወሰን ማስከበር ችግሮችን በአጭር ጊዜ በመፍታት ረገድ የታየው መልካም ተሞክሮ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶች እንዲሁም በመላ አገሪቱ ለሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶች እንደተሞክሮ መወሰድ ያለበት ነው::

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፍትህ ስርአቱን ከጽንፈኛና አክራሪ አስተሳሰቦች ለመታደግ

ፍትህን ለማምጣትም ሆነ ፍትሀዊ ስርአት ለመገንባት ከሁሉም በላይ ለፍትህ ቀናኢ የሆነ ማህበረሰብ መፍጠርን፣ ጠንካራ የፍትህ ስርአትና ተቋማትን መገንባትን ይጠይቃል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ስለ ፍትህ ማውራት ብዙም ትርጉም አይኖረውም። ማንም ወቃሽ ማንም ተወቃሽ ሊሆን አይችልም። ጉዳዩ ለአንድ አካል ብቻ የማይሰጥ ትልቅ አገራዊ አጀንዳ ነው።

የቀደሙት አባቶቻችን ለህግና ለህጋዊ ስርአት፣ ከዛም አልፎ ለህግ አስከባሪ አካላት የነበራቸው ከበሬታ ከፍ ያለ እንደነበር ይታወቃል። ይህ ለህግ ከነበራቸው ቀናኢነት የመነጨ አስተሳሰብና ከአስተሳሰቡ የመነጨ ድርጊት፣ አገራዊ ሰላምና መረጋጋትን በማስፈን ሂደት ውስጥም ትልቅ አቅም መፍጠር ያስቻለ ነው።

መንፈሳዊም ሆነ ባህላዊ ስሬታቸው ለህግና ከህግ ለሚመነጭ ማህበረሰባዊ ሰላምና መረጋጋት መሰረት ከመሆን አልፎ፤ ሐገር እንደ አገር በተሻለ ሰላምና መረጋጋት እንድትቆም አድርጓል። የህግ የበላይነት የሰፈነበት ማህበረሰብ በመፍጠር ሂደትም ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

ወጥ የሆነ የህግ ስርአትም ሆነ የተጻፈ ህግ ባልነበረበት ዘመን ሳይቀር በህገ ልቦና በመመራት በተሻለ ሰላምና መረጋጋት የመኖር አቅም መፍጠር ችሏል። ይህ እውነታ ረጅም ታሪክ ተሻግሮ መሄድ ቢችልም፤ በዘመናዊው ትውልድ የተዛባ አስተሳሰብና አስተሳሳቡ በወለደው ድርጊት እየተፈተነ ይገኛል።

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገሪቱ እየተስተዋሉ ያሉት ጽንፈኝነትና ኃይማኖታዊ አክራሪነት የህትህ ስርአቱንና ተቋማቱን በአደባባይ እየተገዳደሩ መጥተዋል። ለዚህ ደግሞ ሰሞኑን በጎንደር ከተማና እና በስልጤ ዞን "ኃይማኖትን " መሰረት አድርገው የተፈጸሙ ወንጀሎችን ለማጣራት የተሄደበት መንገድና ያጋጠመውን ተግዳሮት ማየት ተገቢ ነው።

በጎንደር በተፈጠረው "ኃይማኖትን" መሰረት ያደረገ ግጭት ተሳታፊ የሆኑ ግለሰቦችን ወደ ፍርድ ቤት ለማቅረብ በተደረገው ጥረት ከሁለቱም የኃይማኖት ተቋማት አባቶች /ክርስትና እና እስልምና በቂ ድጋፍ ባለመገኘቱ የማጣራት ሂደቱን ሙሉ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ የኃይማኖት ተቋማቱ ለፍትህ ካላቸው መንፈሳዊ ቁርጠኝነት አንጻር ይህ አይነቱ ልምምድ በሂደት በማህበረሰባችን የፍትህ አስተሳሰብ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ መገመት የሚከብድ አይደለም።

ከዚህም ባለፈ ህጋዊ ስርአት በማስፈን ሂደት ውስጥ ወሳኝ ስፍራ አላቸው የሚባሉት በፍትህ መዋቅር ውስጥ የሚገኙ ዳኞች ከወገንተኝነት ነጻ ሆነው ወንጀሎችን መዳኘት ሲገባቸው በችግሩ ራሳቸው ተጠልፈው ባልተገባ መንገድ የመጓዛቸው እውነታ /በስልጤ ዞን / የገቡትን ቃለ መሀላ ያረከሰዋል። ይህ አይነቱ የፍትህ ስርአት አቅም የማሳጣት አካሄድ ማንንም ተጠቃሚ ሊያደርግ የማይችል አደገኛ አካሄድ ነው።

ከዚህ በላይ ወንጀል ሲፈጸም ቀድሞ ደርሶ ይከላከላል የሚባለው የፀጥታ መዋቅር / የፖሊስ ሀይሉ/ በጠራራ ጸሀይ ወንጀል ሲፈጸም ቆሞ ተመልካች የመሆኑ እውነታ /በስልጤ ዞን እንደሆነው / የፍትህ ስርአቱ የቱን ያህል ፈተና ውስጥ እንዳለ ያሳያል። አክራሪነትና ሞራል አልባነት የፍትህ ስርአቱንም ሆነ ተቋማቱን እየተፈታተኑት ስለመሆኑም ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ከሁሉም የሚያሳፍረው ደግሞ የፖለቲካ ስርአቱ ለፍትህ ያለውን ቁርጠኝነት በየአደባባይ እየገለጸ ባለበት ሁኔታ፣ የፖለቲካ ስርአቱ አካል የሆኑ ግለሰቦች /የስልጤ ዞን አስተዳዳሪ አይነት / የፍትህ ስርአቱን በአደባባይ ሲቃወሙ፣ ፍትህ ተፈጻሚ እንዳይሆን በራሳቸው ተግዳሮት ሲሆኑ መስተዋሉ ነው።

አገራዊ የፍትህ ስርአቱ ከመጣበት ረጅም የተበላሸ መንገድ አንጻር ሲታይ ግን ስኬታማ ለመሆን እንዳይችል የሚያደርጉ ብዙ ተግዳሮቶች ሊያጋጥሙት እንደሚችሉም ይታመናል። አገራዊ የፍትህ ስርአቱን አስተማማኝ ለማድረግ የተጀመረውን ርብርብ መንግስት /የፌደራል መንግስት /ህጎችን ከማሻሻል ጀምሮ ተቋማትን በሰው ኃይል እና በቴክኖሎጂ ለማዘመን ሰፊ ስራዎችን እየሰራ ባለበትና ለዚህም የሚሆን የፖለቲካ ቁርጠኝነት እንዳለው በሚያሳውቅበት ወቅት ይህ አይነቱ እውነታ በአደባባይ መታየቱና መሰማቱ በእጅጉ ያሳፍራል።

ይህንን አሳፋሪ ተግባር በማረም ሂደት ውስጥ የሚመለከታቸው አካላት ፈጥነው ሊንቀሳቀሱ ይገባል። ጽንፈኝነት እና ኃይማኖታዊ አክራሪነት በተቋማቱ መሰረት እንዳኖራቸው፣ በዚህም አጠቃላይ የፍትህ ስርአቱ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ መስራት፣ አገርን እንደ አገር ከአደጋ የመታደግ ያህል መሆኑን ወረዳት ይገባል!። የጸጥታውም ሆነ የፍትህ መዋቅሩ በራሱ ከህግ በላይ የሚሆንበት ምንም አይነት አግባብ የለም፤ ራሱን ለፍትህ ተገዥ ማድረግ ይጠበቅበታል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሆድ ለባሰው…

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በብዙ የተከፋ ሰው በሆነው ባልሆነው ሆድ ይብሰዋል። ለበጎ ያሉት እንኳ ለክፋት ይመስለውና ይበልጡኑ ይከፋል። ከብዙ መከፋትና መገፋት በኋላ የሚመጣው ሆድ መባስ ደግሞ ነጭናጫና ፍጹም ተጠራጣሪ ያደርጋል። "የተከፋ ተደፋ " እንዲሉ ታድያ ዛሬ በብዙ የተከፋው ህዝብ ሆድ እየባሰው ነጭናጫና ፍጹም ተጠራጣሪ ሆኗል። በዙሪያው የከበቡት ችግሮችም ለቁጥር በዝተዋል። አንዱን ሲለው ሌላው፤ ሌላውን ሲል ደግሞ ሌላ እየተናደ ሆድ መባሱና መከፋቱ በዝቷል።

ላለፉት በርካታ ዓመታት በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሆነው በሕዝብ ላይ ብዙ በደሎችን ሲያደርሱ የነበሩና ሆድ ያስባሱ አካላትና አሰራሮቻቸውን ቆጥረን አንዘልቀውም። ዛሬም በብዙ ትግልና የሕይወት መስዋዕትነት የመጣውን ለውጥ ለማስቀጠል በብዙ የሚተጉ እንዳሉ ሁሉ የጭቃ ውስጥ እሾ ሆነው ሕዝብን ሆድ የሚያስብሱ ስለመኖራቸው ዕለት ዕለት የሚሰሙ አሳዛኝና አናዳጅ ዜናዎች ምስክሮች ናቸው።

የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ፍላጎቶቹ መካከል መኖሪያ ቤት አንዱ ነው። እንደአለመታደል ሆነና በእኛ አገር ይህን መኖሪያ ቤት ለማግኘት መንገዱ ረጅምና አድካሚ ነው። በማያልቀውና አድካሚ በሆነው ረጅሙ መንገድ ብንጓዝ፤ ብንጓዝ ጫፍ መድረስ አይታሰብም። ዕድል ቀንቶን ጫፍ ብንደርስም እንኳ ነገሩ ሁሉ ‹‹…ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ›› አይነት የልጅ ጨዋታ ይሆናል። ይህ ደግሞ ከመከፋትም በላይ ያስከፋል፤ ሆድ ያስብሳል፤ አመኔታን ያሳጣል።

በተለይም ሕዝብ በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዲያጣ በርካታ አሻጥሮች ከሚሰሩባቸው የመንግሥት ተቋማት መካከል የቤቶች ልማት አስተዳደር አንዱ ነው። የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ያውም የጋራ መኖሪያ ቤት ‹‹ኮንዶሚኒየም›› ለአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ እጅግ አንገብጋቢ ጥያቄ ከሆነ ሁለት አስርት አመታትን ሊደፍን ምንም ያህል አልቀረውም። በእነዚህ ሁሉ አመታት ታድያ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ከጠንካራ ሐሜት ጋር ያስተናገደው ይኸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ኤጀንሲ ‹‹የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም›› እንዲሉ ከ30 አባወራ በላይ ሊይዝ የሚችል ሙሉ የጋራ መኖሪያ ቤት ህንጻ ከነነብሱ ጠፍቶበት እንደነበር እናስታውሳለን።

አንድ የጋራ መኖሪያ ቤት ህንጻ ከነነብሱ መጥፋት የአንድ ሰሞን ሐሜት ሆኖ ቢያልፍም በዕጣ አወጣጡ የሚደረጉ መጭበርበሮችን ጨምሮ ስለመዘረፉ፣ ለሆኑ ቡድኖችና አካላት ስለመተላለፉና በቤተዘመድ ሳይቀር ያልተመዘገቡ አካላት የዕድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል የሚሉ ሐሜቶች የአንድ ሰሞን ጉርምርምታ ሆነው ሳይጣሩ ቀልጠዋል። ችግሩ ዛሬም ቀጥሎ ደሃው ህዝብ አልበላም አልጠጣም በማለት እየቆጠበ በብዙ ተስፋ ከሚጠባበቀው ደሃ ሰርቆ ህዝቡ ሆድ እንዲብሰው ማድረግ እጅግ አሳፋሪና ነውር ነው።

መኖሪያ ቤት ማግኘት የሰማይ ያህል በራቀበት አገር ለአስራ ሰባት ዓመታታ በትዕግስትና በተስፋ መጠበቅ በራሱ አስገራሚ ነው። ከአፉ ጥሬ ነጥቆ መቆጠብ ሲጨመርበት ደግሞ አስገራሚ ከመሆን አልፎ የሕዝቡን ጨዋነት ቢያስመሰክርም ትዕግስቱንም የሚፈታታን ነው። ያም ቢሆን ግን ዛሬ ከትናንት በእጅጉ ይለያል።

አንደኛ ከዚህ ቀደም በማጉረምረም ይሰማ የነበረው ማጭበርበር ዛሬ በገሃድ ሌብነት እንደሆነ መስማት ተችሏል። የጋራ መኖሪያ ቤት መጭበርበሩ ከሐሜት በዘለለ በመረጃ ተደግፎ የዜና ሽፋን ማግኘት በራሱ አንድ እርምጃ ወደፊት እንደማለት ነው። ሌላ የተለየው ነገር ደግሞ ከተማ አስተዳደሩ የችግሩን መከሰት አምኖ ይቅርታ መጠየቁ ነው።

"አካፋን አካፋ ዶማንም ዶማ" እንዲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ‹‹ሌባን ሌባ በሉት›› በማለት ለሌባ ሽፋን እንዳይሰጥ ፈቃድ ሰጥተዋል። በዚህ መሰረት ከተማ አስተዳዳሩ መረጃውን በግልጽ ከመስጠት ጀምሮ ጥፋተኛውን ተጠያቂ ለማድረግ እየሄደበት ያለው ርቀት ሆድ ለባሰው ህዝብ ፈጣን ምላሽ መስጠት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሊያስመሰግነው የሚገባ ጉዳይ ነው።

እርግጥ ነው ከተማ አስተዳደሩ ከሰሞኑ ያወጣውን 14ኛው ዙር የ20/80 እና የ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ አወጣጥ ከሰው እጅ ንክኪ ነጻ እንዲሆን የበኩሉን አድርጓል። ያም ሆኖ ግን ስህተት ከተፈጠረ የማጣራት ሥራ እንሠራለን ብሎ ቃል በገባው መሰረት እነሆ ተፈጠረ የተባለውን ውዥንብር ሊያጠራ ፈቃደኝነቱን ከሙሉ ፍላጎት ጋር እያሰየ ይገኛል። ታድያ ቴክኖሎጂውንም የሚያለማው የሰው እጅ እንደመሆኑ በቴክኖሎጂ ስም የሚሰሩ አሻጥረኞችንም አለመጠራጠር አይቻልምና ሁሉን አቀፍ ማጣራት ቢሆን መልካም ነው።

ህዝቡ በስስትና በጉጉት የሚጠብቀውን የጋራ መኖሪያ ቤት ከእጁ ላይ መዝረፍ ከሌብነትም በላይ ሌብነትና ወራዳነት ነው። ጥሬ ቆርጥሞ መቀነቱን ፈትቶ የሚቆጥበው፤ የነገ ተስፋውም ጭምር የሆነው የጋራ መኖሪያ ቤትን መቀማት ማለት የህዝቡን የደረቀ ቁስል ጭርሱን እንዳይሽር መገሸለጥ ነው። የጋራ መኖሪያ ቤት ጉዳዩ ለዓመታት የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ መዝለቁ ደግሞ ከማንም በላይ በተስፋና በጉጉት የሚጠባበቀውን ህዝብ ሆድ የሚያስብስ ነው።

ሆድ ለባሰው… እንዲሉ ታድያ ህዝቡ በተለያዩ ጉዳዮች በተለይም በሰላምና ጸጥታ፤ በኑሮ ውድነት እየተፈተነ ባለበት በዚህ ወቅት የምጥ ያህል ተጨንቆና ተጠብቦ የሚያገኘውን ጠብታ ዕድል ማክሸፍ የጭካኔ ጥግ የታየበት ጭካኔ ነው። የተከፋ ተደፋ ሆነና ነገሩ በኑሮ ውድነት እየተናጠ በሰላምና ጸጥታ ስጋት እየተሸበበ ለዓመታት በከፍተኛ ትዕግስት የጠበቀውን ተስፋ ማጨለም ሆድ ከማስባስም በላይ በመንግሥትና በህዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሻክርና አመኔታን የሚያሳጣ ነውና በብርቱ ሊወገዝ ይገባል።

ነገን ተስፋ አድርጎ በብዙ እየተፈተነ ያለው ህዝብ መሸሻ መድረሻ ሌላ አገር የለውም። ያለው አንድ አገር ናትና በፍትሃዊነት ተጠቃሚ እንዲሆን እንፍቀድ። ዛሬ በዳታና በዕጣ አወጣጥ መጭበርበር ምክንያት የበርካቶች ደስታ ውሃ ተቸልሶበታል። ያም ቢሆን ተስፋ መቁረጥ ብሎ ነገር አይታሰብም፤ ነገን ተስፋ በማድረግ ዛሬም ነገም ሌቦችን መሞገትና ማጋለጥ የእያንዳንዱ ዜጋ ተግባር ቢሆን መልካም ነው።

"ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል" እንዲሉ ከተማ አስተዳደሩ የጀመረውን የማጣራት ሥራ አጠናክሮ በመቀጠል መረጃውን በጉጉት ለሚጠብቀውና ሆድ ለባሰው ተስፈኛ ህዝብ በፍጥነት ያሳውቅ። የሚያሳውቀውም ለዘመናት በከፍተኛ ጉጉትና ስስት ሲጠባበቅ የኖረውንና ድንገት በህገወጦች የተነጠቀውን ሀቅ ከእጁ ለማስገባት እንጂ ሆድ ለማስባስ እንዳይሆንም እምነታችን ነው።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# አግኝቶ ማጣትን - ከራስ የማስታረቅ ሩጫ

ሰላማዊት ውቤ

አንዳንዴ በሕይወት ዑደት ከፍ ማለት እንዳለ ሁሉ ቆይቶ ዝቅ የማለት እውነታ ሊያገጥም ይችላል። እንዲህ መሆኑ ለሌላው አንዳች ባይመስልም ለባለቤቱ ግን በእጅጉ የሚከብድ ዱብ ዕዳ ነው። ወዲህ መለስ እንበልና ከከባዱ የሕይወት ምዕራፍ አንደኛውን ገጽ እንግለጥ።

ለሦስት አሥርት ዓመታት የአእምሮ ህመምተኛን ሲንከባከቡ መቆየት ዱብ ዕዳውን ከማባስ አልፎ ኑሮን የገሀነም ያህል ያከብዳል ብንል እያጋነነን አይሆንም። ወቅቶች በቀውስ ውስጥ ሲገቡና ስርዓት አልበኝነት ጉልበት በሌላቸውና የቀውሱ አካል ባልሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሲሰለጠን ደግሞ ማንነት በጭንቀት መወጠሩ አይቀሬ ይሆናል። የዚህ አይነቱ ችግር ሰለባ ከሆኑም በተስፋ መቁረጥ የሚይዙ የሚጨብጡትን ቢያጡ ፍጹም አይፈረድም።

እንዲህ ዓይነቱ ዕጣ ፈንታ ግን በወይዘሮ ጀሚላ አሸረቃና ቤተሰባቸው ላይ ደርሷል።

ወይዘሮዋ የተወለዱት ገጠር ቢሆንም ኑሯቸውን መሳለሚያ አካባቢ በሚገኘው በእህል በረንዳ ወረዳ አራት ቀበሌ 26 ያደረጉት ገና በታዳጊነታቸው ነው። ኑሯቸውን በዚህ አካባቢ ለማድረግ ምክንያታቸው ደግሞ ትዳር መመስረታቸው ነበር። ገና ደረታቸው ላይ በወጉ ጡት ሳይኖር አንዲት ፍሬ ልጅ ሆነው ነው አቶ ሁሴን መሐመድን አግብተው ትዳር የመሰረቱት።

ባለቤታቸው አቶ ሁሴን የያኔዋን አንዲት ፍሬ ጀሚላ አሸረቃን ከማግባታቸው በፊት ጥሩ አባወራ ልሆንላት ያስችለኛል ያሉትን ሁሉ አሟልተው ነበር። ያኔ የቆሻሻ መከማቻ የነበረውንና አሁን ላይ በባለቤታቸው ላይ በመፍረሱ በአካባቢው በጎ አድራጊዎች እንደ አዲስ በብሎኬት እየተሰራ ያለውን ቤት አሳምረው ገንብተዋል። በውብና ማራኪ ዕቃዎችም ሲያሟሉት ቆይተዋል።

ትዳሬን ለማጠንከር አቅም ይሆነኛል ያሉትን ገቢ ማስገኛ ንግድም ከፍተው ነበር። ጎጇቸው ከቆመ በኋላ እንዳይናጋ በመስጋትም ንግድ ሥራቸው ሁለት ሦስት እንዲሆን አስችለዋል። አንዱ አሁን ባለቤታቸው እየኖሩበት ካለው መኖሪያ ቤት ጋር የተያያዘው ዳቦ ቤት ነበር። ዳቦ ቤቱ ገበያው የደራ ገቢውም ዳጎስ ያለ እንደሆነ የያኔዎቹ የባለቤታቸው የአቶ ሁሴን መሐመድ ጎረቤቶችና የአካባቢው ነዋሪዎች ዛሬ ድረስ ሲመሰክሩለት ይደመጣል።

በደረታቸው ጡት እንኳን ያልነበረው የያኔዋ ታዳጊ ልጃገረድ የዛሬዋ እናት ወይዘሮ ጀሚላ አቶ ሁሴን መሐመድን ማግባታቸው በእዚህ ሁሉ ሲሳዮች ተከበዋል። ዛሬ ከአርባ ዓመታት በኋላ ወደኋላ ተመልሰው ሁኔታውን ሲያስታውሱት ምኞቱ ያለ ሀሳብ በርካታ ልጆችን በላይ በላዩ እንዲወልዱ አድርጓቸው እንደነበር አይሸሽጉም።

ወይዘሮዋ አምስት ወንድና ሦስት ሴት ልጆቻቸውን ያለአንዳች ሀሳብ ነበር የወለዱት። ዕድሜ ለባለቤታቸው ይሁንና ሌላው ሳይጨመር በዳቦ ቤቱ ገቢ ብቻ ከነልጆቻቸው ድልቅቅ ያለ ሕይወት ይኖሩ እንደነበር አይዘነጉም። ጀሚላ የዛኔ እንደ አቅማቸው ለአካባቢው ሰዎችና ለሥራ አጥ ዘመዶቻቸው የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል። ልጆቻቸውን በዕውቀት ለማነፅም ትምህርት ቤት አስገብተው አስተምረዋል። ልጆቹም የሚፈልጉት ሁሉ ተሟልቶ ደስተኛ ሆነው ነው አድገዋል። ባልና ሚስቱም ቢሆኑ በወቅቱ ችግር ምን እንደሆነ አያውቁትም ነበር።

ሕይወታቸው ግን እንዲህ ተደላድሎ አልዘለቀም። ባልና ሚስቱ ለቅርብ ዘመድ ለቅሶ አገር ቤት ቆይተው ሲመለሱ ያልታሰበ ድንገተኛ ችግር ገጠማቸው። ወቅቱ ወታደራዊው የደርግ መንግስት ስልጣን ላይ የነበረበት ነው። በጊዜው አንድ የቀበሌ አብዮት ጠባቂ በራሱ ይሁንታ ያሻውን የማድረግና ሀይል እንዲኖረው ስልጣን ተሰጥቶታል።



ፎቶ፡- አዮብ ተፈሪ

**ወይዘሮ ጀሚላ አሸረቃ**

አብዮት ጠባቂው ይህን ስልጣኑን ተጠቅሞ በነዋሪው ላይ ግፍና በደል መፈጸሙ የተለመደ ነበር። መደብደብ፣ ማሰር ወጣቶችን በግዳጅ ውትደርና መላክና ሌሎችም የከፋት ተግባራት መገለጫዎቹ ናቸው። አንዳንዴ ደግሞ የቀበሌ ቤቶችን በጉልበት ሰብሮ በመግባት ያሻውን ለማድረግ ከልካይ አልነበረውም።

እነ ወይዘሮ ጀሚላን ከአገር ቤት መልስ ወደመኖሪያቸው ሲገቡ ቤታቸው በአንድ አብዮት ጠባቂ ተሰብሮ ያገኙታል። ሁኔታው ቢያስደነግጣቸው ፈራ ተባ እያሉ ለማጣራት ተጠጉ። ሰውዬው ከነሙሉ ንብረታቸው በቤታቸው መኖር ጀምሯል። ባልና ሚስቱ ማመን አቃታቸው። በጉልበተኛው ባለጊዜ ቤት ንብረታቸው ተነጥቆ ሜዳ መውደቃቸውን አወቁ፡

ከነልጆቻቸው መግቢያ ያጡት ጥንዶች ጎረቤት ዘንድ ተጠግተው ከረሙ። ቆይተውም በህግ ሞግተው አሸነፉት። ሰውዬው በዋዛ አልተዋቸውም ፤ ፍርዱን አስቀልብሶ ዳግም ከችሎት አቆማቸው። በመጨረሻ ከሰውዬው ሲሟገቱ የቆዩት ቤተሰቦች በፍትህ የፍርድ ሚዛናን አገኙ። ቤታቸውን ከጉልበተኛው የአብዮት ጠባቂ አስመለሱ።

በወቅቱ በባልና ሚስቱ የደረሰው በደልና እንግልት ቀላል አልነበረም። ጥንዶቹ በውጣውረድ ጤና አጥተዋል። በብስጭት ተክዘዋል፣ በችግር ደጅ ጠንተዋል። በተለይ አባወራው ሁሴን ከችግሩ በኋላ በጭንቀት ያገጠማቸው ህመም ቀላል አልሆነም። በየደቂቃው «ራሴን » ማለት ያዝወትራሉ። ውሎ አድሮ የሁሴን ችግር የአእምሮ ህመም መሆኑ ታወቀ። ይሄኔ በድንገት የመላው ቤተሰብ ሕይወት ተናጋ ። የወጣችው ጀንበርም መልሳ ጠለቀች።

አቶ ሁሴን መሐመድን የማስታመሙ ሙሉ ሀላፊነት በወይዘሮዋ ጫንቃ ላይ ወደቀ። ለእሳቸው የአእምሮ ህመም ያለባቸውን አባወራ ማስታመም በእጅጉ ከባድ ነበር። አብሮ መሯሯጡ፣ ወዲያ ወዲህ ማለቱ ለእሳቸው ፈታኝ ሆነ። በየዕለቱ በድካም ቁም ስቅላቸውን አዩ። ሙሉ ጊዚያቸውን ባለቤታቸውን ለማስታመም አዋሉት። የግል ጉዳይና ማህበራዊ ሕይወት ይሏቸው ጉዳዮች ለሦስት አስርት ዓመታት ታሪክ እስኪመስሉ ራሳቸውን ሰጡ።

የችግሩ መስፋት ሌሎች ችግሮችን ማስከተሉ አልቀረም። በመኖሪያ ቤታቸው ግቢ የነበረውን ዳቦ ቤት ጨምሮ በየቦታው ያስፋፉት የንግድ ሥራ በልጆች እጅ መግባቱ ገበያውን አቀዛቀዘው። ውሎ አድሮም ሁሉም የገቢ ማስገኛ ንግድ ቤቶችና ሌሎች መተዳደሪያዎች ሥራ አቆሙ። በግቢያቸው የሚገኘው ዳቦ ቤትም ሙሉ ለሙሉ ስራ አቁሞ ተዘጋ።

«እኔ ባለቤቴን ሳስታምም ልጆቼም ትምህርታቸውን አቆሙ። የዕለት ጉርስ እስከ ማጣት በመድረሳችንም በየፊናቸው እየተሯሯጡ ሊደግፉኝ ሞከሩ። እኔም ባለቤቴን ከማስታመም ጎን መኖሪያ ቤቴ ደጃፍ ላይ ሽንኩርትና ድንች እንዲሁም ዕጣንና ሌሎች ጭሳጭሶችን በመሸጥ ኑሯችንን መደጎም ጀመርኩ» ይላሉ። እናት ጀሚላ።

ወይዘሮዋ በወቅቱ ችግር ያስጀመራቸው ሥራ ባለቤታቸውን ከማስታመም ጋር የሚስማማ አልነበረም። ሥራውን ባለቤታቸውን ከማስታመሙ ጋር ለማዛመድ ብዙ ታግለዋል። በከፈሉት መስዋዕትነት እጅግ ተጎሳቁለዋል። የልጆቻቸው አይዞሽ ባይነት ግን ብርታት ሆኖ ዛሬን በጽናት አቁሟቸዋል።

ወይዘሮዋ እንዳወጉን በተለይ ትልቋ ልጃቸው በደጃፋቸው ለሚሸጡት ጉልት የሚሆን ሽንኩርት እና ድንች በጀርባዋ እየተሸከመች በማምጣት ትልቅ እገዛ አድርጋቸዋለች። በየሰው ቤት ልብስ በማጠብና የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራትም ኑሯቸውን እንዲደጉሙ ስታግዛቸው ቆይታለች። እሷ እስከ ስድስተኛ ክፍል እንኳን የደረሰችው ቀን በየሰው ቤት እየሰራችና ለእናቷ ድንችና ሽንኩርት በጀርባዋ እየተሸከመች ማታ በመማር ነው።

እያደር የወይዘሮ ጀሚላ ባለቤት እየተሻላቸው ነበር። ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ምድር ቀውጢ በሆነችበት በምርጫ 1997 የወንዱ ልጃቸው እንደወጣ መቅረትን ሰምተው ከፉኛ መደንገጣቸው ሌላ ችግር መዘዘ። ድንጋጤው የአእምሮ በሽታቸውን ይበልጥ አባባሰው።

ወይዘሮ ጀሚላም ባለቤታቸውን ማስታመሙ ከልጃቸው ሀዘን ተደርቦ ጭንቀት ውስጥ ገቡ። ችግሮቹም እያደር አቅም አሳጣቸው። ዛሬም ይህ ውስጣዊ ድካምና ሀዘን አብሯቸው ዘልቋል «ልጄ እስከ አሁን እምጥ ይግባ ስምጥ አላውቅም። በረብሻው ጊዜ እንደወጣ ነው የቀረው» የሚሉት ወይዘሮ ጀሚላ በዚሁ ሰበብ ባለቤታቸው የአእምሮ ህመማቸው ተባብሶ ለሞት መብቃታቸውን ያስታውሳሉ።

ጀሚላ የዛኔ ችግሩ ሲጠና በቤቱ የሚበላ እስከማጣት መድረሳቸውን በትዝታ ያወሳሉ። እንዳይሰሩ ወገባቸው በሽተኛ በመሆኑ በእጅጉ መቸገራቸውንም አይዘነጉትም። ሆኖም «ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም» እንዲሉት ተረት «በሽተኛ ነኝ» ሲሉ ዝም አላሉም። ጉሊት መቸርቸርን ጨምሮ ያገኙትን ሲሰሩ ኖረዋል፤ በሥራና በትምህርት ገፍተው ራሳቸውን መቻልና እናታቸውን የመጦር ዕድል ያላገኙ ልጆቻቸውም የቻሉትን እየሰሩ ሕይወታቸውን አሰንብተዋል።

እናት ጀሚላ አለባበሳቸው ፅዓዳ ፤ ሰውነታቸው ድንቡሽ ቡሽ ነው። ይህን ላስተዋለ ምንም ችግር ያያቸው አይመስሉም። በተለይ በዘመነ ኮሮና በቤታቸው የሚላስ የሚቀመስ በመጥፋቱ በእጅጉ ሲቸገሩ ከርመዋል ። እንደ እሳቸው ላሉ ችግርተኞች ድጋፍ የሚያደርጉ ደጋግመው በአካባቢያቸው ቢመጡም ሊጎበኙዋቸው አልፈቀዱም። ውስጣቸውን ሳያዩ አለባበሳቸውን ብቻ አይተው ያለ አንዳች ድጋፍ በምዝገባ ብቻ አልፈዋቸዋል። ጀሚላ ይህንንም አይረሱትም።

ወይዘሮ ጀሚላ በ1997 ዓ.ም ከጠፋው የበኩር ልጃቸው በቀር ሁሉም ልጆቻቸው ከእሳቸው ጋር እየኖሩ ነው። ዛሬም ያልተለወጠው ሕይወታቸውና ከእጅ ወደ አፍ የሆነው ኑሯቸው ግን አሁንም እየፈተናቸው ይገኛል።

ያኔ አብዮት ጠባቂው ሰብሮ የገባው ቤት ጉዳይም በየወቅቱ እየተነሳ ሰላም ሲያሳጣቸው መኖሩንም ያስታውሳሉ። አብዮት ጠባቂው ቤቱን ሰብሮ ሲገባ ኪራይ ቀመስ አድርጎና የግል ቤት የሚል ፋይል ስላጠፋባቸው በዚሁ ጉዳይ እግራቸው እስኪቀጥን ቀበሌ ሲመላለሱ ኖረዋል።

ልጆቻቸው አባታቸውን በሽተኛ አድርጎ ለሞት ያበቃው ችግር የቤቱ ጉዳይ መሆኑን ያውቃሉ። ይህ መዘዝ ለእናታቸው ሰላም ማጣት ሰበብ ሆኖም እንዲጎዳቸው አይሹም። በዚህ ሳቢያም ስለሰላማቸው መኖር ቤቱ በቀበሌ ይዞታ እንዲቀጥል ፈቅደዋል። ያም ሆኖ በወቅቱ ሰውዬው በየወሩ ያስተመነው የ10 ብር ኪራይ ተጠራቅሞ ውዝፍ ባለ ዕዳ አድርጓቸው ቆይቷል።

‹በየጊዜው ጉዳዩ ሲነሳ ለመከራከር የገንዘብም ሆነ የዕውቀትና የጊዜ አቅም ስለሌለን የግላችንን ቤት ወድደንና ፈቅደን የቀበሌ አድርገነዋል› የሚል ማመልከቻ ማስገባታቸውንም አውግተውናል። ሆኖም ይሄው ቤት ከጊዜ ብዛት በማርጀቱ በየክረምቱ ሲያፈስ መቆየቱንም አልሸሸጉንም። እጃቸውንና መዘፍዘፊያ ደቅነው ቆመው የሚያድሩበት ጊዜም የበረከተ ነበር። በቅርቡ ደግሞ በእርጅና እና በዝናብ ምክንያት መፍረሱን ገልጸውልናል።

እኛ ወደ ወይዘሮዋ ቤት በሄድንበት ጊዜ በበጎ ፈቃደኛ ሰዎች ትብብር ቤቱ ፈርሶ በብሎኬት ሲሰራላቸው ነበር። እሳቸውም ደጃፉ ላይ ኑሯቸውን ለመደጎም እያገለበጡ ያኖሩትን የጉሊት ሥራ አቁመው ቤታቸውን ማሰራቱን ይዘዋል። ዛሬ አሮጌው ቤታቸው በአዲስ መተካቱ አስደስቷቸዋል። ያልሞላው ኑሯቸው ግን ከነጎዶሎ እንደቀጠለ ተጉዟል።

ብርቱዋ ሴት እናት ጀሚላ መልካም ዓይኖች ቢጎበኙዋቸው ይሻሉ። ትናንትን አልፈው ዛሬ ላይ ሲቆሙ በአይቀጠሬ የመከራ መንገዶች እየተሻገሩ ነው። ነገ ግን ለእሳቸው ሁሌም ሌላ ቀን ነው። ማንም ከጎናቸው ቆሞ ጨለማውን ቢገፍ ብሩህ ተስፋ ከጎናቸው ይገኛል።

# ስፖርት




# ወጣቶቹ የመካከለኛና ረጅም ርቀት የሜዳሊያ ተስፋዎች


ብርሃን ፈይሳ

በፖርትላንድ ኦሪገን ትናንት በተጀመረው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና እየተካፈለች የምትገኘው ኢትዮጵያ ውጤታማ እንደምትሆን ከምትጠበቅባቸው ርቀቶች መካከል የወንዶች 3ሺ ሜትር መሰናክል እና የሴቶች 1ሺ500 ሜትር ተጠቃሾች ናቸው።በዚህ ርቀት አገራቸውን የሚወክሉት ወጣት አትሌቶች በተለያዩ ውድድሮች ላይ ብቃታቸውን ያስመሰከሩ ሲሆን፤ በዚህ ቻምፒዮናም ከወርቅ ጀምሮ ሌሎች ሜዳሊያዎችን እንደሚያስመዘግቡ ተስፋ ተጥሎባቸዋል።

በቻምፒዮናው የ3ሺ ሜትር መሰናክል የወንዶች ውድድር የሰሜን እና ምስራቅ አፍሪካውያን ትንቅንቅ የሚታይበት እንደሆነ በበርካታ የአትሌቲክስ ቤተሰብ ዘንድ ግምት አግኝቷል።ኢትዮጵያዊው አትሌት ለሜቻ ግርማ እና ሞሮኳዊው ሶፊያን ኤል ባካሊ ደግሞ የወርቅ ሜዳሊያውን ለማጥለቅ የሚፋለሙ አትሌቶች ናቸው።ሁለቱ አትሌቶች ባለፈው ቶኪዮ ኦሊምፒክ ባደረጉት አስደናቂ ፉክክር ኤል ባካሊ የወርቅ ሜዳሊያ ሲያጠልቅ ለሜቻ ብሩን የግሉ አድርጓል።ባለፈው የዶሃ 2019 የዓለም ቻምፒዮናም ሁለቱ አትሌቶች ተገናኝተው ለሜቻ የብር ሜዳሊያ ሲያጠልቅ ሞሮኳዊው አትሌት የነሐስ ሜዳሊያ ነበር ማሸነፍ የቻለው።ይህም የሁለቱን አትሌቶች ፉክክር በጉጉት እንዲጠበቅ ያደረገ ሲሆን ርቀቱ ባህላቸው እንደሆነ ደጋግመው ያሳዩ ኬንያውያንም የተዳከሙ ቢመስሉም አዲስ ነገር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ይታመናል።

ኢትዮጵያ ከጥቂት ዓመታት በፊት ብዙም በማትታወቅበት 3ሺ ሜትር መሰናክል ውጤታማ ጊዜን እያሳለፈ የሚገኘው ወጣቱ አትሌት ለሜቻ በቤልግሬድ የቤት ውስጥ ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ባለቤት መሆኑ ይታወሳል። በዚህም የዓለም አትሌቲክስ በዓመቱ የምርጥ ወጣት አትሌት ምርጫ ውስጥ በእጩነት ያካተተው ተስፈኛው አትሌት ያለፉትን ውድድሮች የሚያስታውሳቸው በቁጭት ነው።በዶሃው የዓለም ቻምፒዮና ለጥቂት በሽርፍራፊ ማይክሮ ሰከንዶች ተቀድሞ የወርቅ ሜዳሊያ ያጣው ለሜቻ፤ የፊታችን ሰኞ በኦሪገን በወርቅ ሜዳሊያ ለመጀመሪያ ጊዜ የመድመቅ እድል እንደሚኖረው በርካታ የስፖርት ቤተሰቦች ተስፋ አድርገውበታል።




**አትሌት ለሜቻ ግርማና ጉዳፍ ፀጋይ በመጪው ሰኞ ለኢትዮጵያ ሜዳሊያዎችን እንደሚያስመዘግቡ ይጠበቃል፤**

በውድድር ዓመቱ በግሉ እንዲሁም አገሩን ወክሎ በበርካታ ውድድሮች ላይ በመካፈል አንፀባራቂ ውጤቶችን ማግኘት የቻለው ለሜቻ፣ ያለፈውን ቻምፒዮና ቁጭት ለመወጣት ኦሪገንን በጉጉት ሲጠብቅ ነበር። በመሆኑም ጥሩ ውጤት በማስመዝገብ ዓመቱን ለማጠቃለል መልካም ሁኔታ ላይ እንደሚገኝም ነው ወደ ኦሪጎን ከማ ቅናቱ በፊት ለአዲስ ዘመን የተናገረው፡፡

ለሌሎች ውድድሮች የሚያዘጋጀውና የሩጫ እቅድም የሚያወጣለት አሰልጣኙ ተሾመ ከበደ በዓለም ቻምፒዮናው ብሄራዊ ቡድኑን በርቀቱ እንዲያሰለጥን መመ ረጡ ይታወቃል። ይህንንም ተከትሎ የዝግጅት ጊዜውን አብረው በማሳ ለፋቸው እንዲሁም አብረውት በውድድሩ ላይ ከሚሳተፉት አትሌቶች ጋር እንደ ቡድን በጋራ በመዘጋጀታቸው ከፍተኛ ጥቅም አስገኝቶላቸዋል።ይህም ባለፈው ቻምፒዮና በርቀቱ ለጥቂት ያመለጠውን የወርቅ ሜዳሊያ ለማጥለቅ መልካም አጋጣሚን እንደሚፈጥርለት አሰልጣኙ አስተያየቱን ሰጥቷል።

ከነገ በስቲያ ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት ያገኙበት ሌላኛው ርቀት የሴቶች 1ሺ500 ሜትር ውድድር ነው።በዚህ ርቀት በመላው ዓለም በርካታ ተፎካካሪዎች ያሉ ሲሆን፤ በኢትዮጵያዊቷ ጉዳፍ ጸጋይ የሚመራው ቡድን ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።በዓለም ቻምፒዮና ታሪክ እጅግ ስኬታማዋ አትሌት ኬንያዊቷ ፌዝ ኪፕዬጎን ብትሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሌላኛዋ ሆላንዳዊት ጠንካራ አትሌት ሲፋን ሃሰን ተቆጣጥራዋለች።ይሁንና ወጣቶቹ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በዚህ ዓመት በተለያዩ ውድድሮች ባሳዩት አስደናቂ አቅም የአሸናፊነት ግምት እንዲሰጣቸው አድርጓል፡፡

ኬንያዊቷ አትሌት ከጉዳት እያገገመች ያለች በመሆኑ እንዲሁም ሆላንዳዊቷ ሲፈንም በጾምና ሌሎች ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ልምምዷን እንደወትሮው አለመቀጠሏ ምናልባትም በውጤታቸው ላይ ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ተሰግቷል።ይህም ለኢትዮጵያውያኑ አንድ መልካ አጋጣሚ ሊሆን ይችላል።መልካም የውድድር ዓመት እያሳለፈች የምትገኘው ጉዳፍ በዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በዚሁ ርቀት የወርቅ ሜዳሊያ ማጥለቅ ችላለች።ይህም አትሌቷ ሌላኛውን የርቀቱን ስኬት በኦሪጎን ታጣጥማለች በሚል ተስፋ እንዲጣልባት ያደረገ ሲሆን፤ እአአ 2015 ቤጂንግ ላይ በፈጣኗ አትሌት ገንዘቤ ዲባባ የተወሰደውን የበላይነት በድሏ ትደግመዋለች በሚል ቅድመ ግምቱን ልታገኝ ችላለች።

ከአትሌቷ ጋር በመሆን አገራቸውን ወክለው ውድድሩ ላይ የሚሳተፉት ወጣቶቹ አትሌቶች ሂሩት መሸሻ እና ፍሬወይኒ ኃይሉም ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም።ሂሩት ቤልግሬድ ላይ ጉዳፍን ተከትላ በመግባት የነሃስ ሜዳሊያውን ስትወስድ፤ ፍሬወይኒ ደግሞ በዚሁ ውድድር ላይ የ800 ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ነበረች።በዳይመንድ ሊግ ውድድሮች ላይም ጥሩ አቋም ላይ እንደሚገኙ ማስመስከራቸውን ተከትሎም የስፖርት ቤተሰቡ ለተፎካካሪዎቻቸው ፈተና ከመሆን ባለፈ የሜዳሊያ ዝርዝር ውስጥም የመግባት ተስፋ እንዳላቸው ነው የሚጠብቀው።


የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

Commercial Bank of Ethiopia

እንኳን ደስ አለን !

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ብዛት 1826 ደረሰ !!

በመላ አገሪቱ በከፈትናቸው 1826 ቅርንጫፎቻችን አማካኝነት የባንክ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናችንን ስንገልፅ በደስታ ነው፡፡ ከእነዚህ ቅርንጫፎቻችን መካከል ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎትን የሚሰጡ ቅርንጫፎች ብዛት 113 ደርሰዋል፡፡ በሁሉም የባንካችን ቅርጫፎቻች ደግሞ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎትን የሚሰጡ መስኮቶች ተከፍተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

ባንካችን በአራተኛው ሩብ ዓመት (እ.አ.አ ከአፕሪል 1 ቀን 2022 እስከ ጁን 30 ድረስ 2022 ) የከፈታቸው ቅርንጫፎች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው።

| ተ.ቁ | የቅርንጫፍ ስም | ዲስትሪክት | የሚገኝበት ክልል (መስተዳደር) | ከተማ / ክ.ከተማ | ወረዳ | ቅርንጫፍ / የባንክ አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተውሂድ | አራዳ | አዲስ አበባ | አራዳ | ወረዳ 01 | ሲ.ቢ.ኢ. ኑር (ወለድ አልባ) |
| 2 | ይድነቃቸው ተሰማ | ቦሌ | አዲስ አበባ | ቂርቆስ | ወረዳ 06 | መደበኛ |
| 3 | ዘምዘም | ቂርቆስ | አዲስ አበባ | ንፋስ ስልክ | ወረዳ 06 | ሲ.ቢ.ኢ. ኑር (ወለድ አልባ) |
| 4 | አራብሳ ገብርኤል ማዞሪያ | መገናኛ | አዲስ አበባ | ለሚ ኩራ | ወረዳ 06 | መደበኛ |
| 5 | ደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪያል ፓርክ | ደብረ ብርሃን | አማራ ክልል | ደብረ ብርሃን | ቦሰና | መደበኛ |
| 6 | አዬዎቹ | ጎንደር | አማራ ክልል | ጎንደር | አዘዞ አየር ማረፊያ | መደበኛ |
| 7 | ደገሃቢ | ጅግጅጋ | ሶማሌ ክልል | ፋፈን | ጉርሱም | መደበኛ |
| 8 | ሂዳያ | አሰላ | ኦሮሚያ ክልል | ሳጉሬ | ዲገሉና ጢጆ | ሲ.ቢ.ኢ. ኑር (ወለድ አልባ) |
| 9 | ጢጆ | አሰላ | ኦሮሚያ ክልል | ጢጆ | ዲገሉና ጢጆ | መደበኛ |
| 10 | ማሪ ማንሳ | ጅማ | ደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል | ማሪ | ዳውሮ | መደበኛ |
| 11 | ተውፊቅ | ነቀምቴ | ኦሮሚያ ክልል | አንገር ጉቴ | ጊዳ አያና | ሲ.ቢ.ኢ. ኑር (ወለድ አልባ) |
| 12 | አቦቦ | መቱ | ጋምቤላ ክልል | አቦቦ | አቦቦ | መደበኛ |
| 13 | ቤሮ | መቱ | ደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል | ጀባ | ቤሮ | መደበኛ |

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ሁሌም የሚተማመኑበት ባንክ!